## የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስለሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ሕዝብና ፡ ስለ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ዝርዝር ፡ ማብራሪያ ፦

ከቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ ፡*

"ባንዳንዱ ፡ የሰሜኑ ፡ ክፍል ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ 'መሬት ፡ አለህ ?' የሚ ለው ፡ ተራ ፡ የሚመስለው ፡ ጥያቄ ፤ በቀላሉ ፡ እንደስድብ ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ። ጥያ ቄው ፡ የተሠነዘረለትም ፡ ኩሩ ፡ ሰው ፡ ትሁት ፡ ለመሆን ፡ ከመረጠ ፤ ፈገግ ፡ በማለት ፡ 'ድሃም ፡ ብሆን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ እኮ ፡' ሲል ፡ ይመልስ ፡ ይሆናል ። ማንም ፡ ሰው፡ ቢሆን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ---መሬት ፡ ይኖረዋል ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ይህም የማንም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለመሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ያለው ፡ መሠረ ታዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ ይህ ፡ ነው ። የመሬት ፡ ባለቤትነትም ፡ የሚፈለገው ፡ ለሚያስከ ትለው ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለባለቤቱና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሊያስገኝለ ትም ፡ ስለሚችለው ፡ ስምና ፡ ክብር ፡ ጭምር ፡ ነው ። መሬት ፡ መያዝም ፡ የመከበር ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የክብርና ፡ የኩራት ፡ ምልክት ፡ ነው ። ስለዚህም ፤ በመሬት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ባላቸውና ፡ ---በሌላቸው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ አይወሰንም ። መሬት ፡ የሌለው ፡ መሆን ፡ የሰው ፡ የበታች ፡ መሆን ፡ ነው።"[1]

### መግቢያ ፤

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ዓላማችን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከቱትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ማለት ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱-፩ሺ፭፪ ፡ ያሉትን ፤ በዝርዝር ፡ ለማብራራት ፡ ሲሆን ፤ ይህንንም ፡ የምናደርገው ፡ ቁጥሮቹ ፡ በወጡበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ሁኔታና ፡ አቋም ፡ በመመራት፡ ነው ። እንዲያውም ፡ ሊያስተዳድሩ ፡ የታቀዱትን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍል ፡ ሁኔታና፡ ሊያስወግዱ ፡ የታሰቡትንም ፡ ችግር ፡ ሳላወቀ ፡ የተባሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ምንም ፡ ስሜት፡ የሚሰጡ ፡ አይመስልም ።

መግቢያ ፡ ቁጥሩን ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ን[2] ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያነበበ ፡ ሊረዳው ፡ እንደሚችለው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ምዕራፍ ፡ ባህልንና ፡ ልማድን ፡ የሚ

---

* ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ዩ. ፲፱፻፷፩ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ ከፍተኛ ፡ የጥናት ፡ ጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ለፕሮፌሰር ፡ ሃሪስን ፡ ዳኒንግ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ።

1. መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤ ሳም ፡ አስፔክትስ ፡ ኦፍ ፡ ላንድ ፡ አውነርሺፕ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (ለኢት ዮጵያ ፡ ጥናቶች ፡ ስብሰባ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በቅድሚያ ፡ የቀረበ ፡ ጽሑፍ ፤ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ- ም-) (ያልታተመ) በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ ገጽ ፡ ፩ ።
2. "ሀብትነታቸው ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ (የደሽ) ፡ እንደ ፡ ጕሣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ በኅ ብረት ፡ መሠራታቸው ፡ የኅብረቱን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የተከተሉ ፡ መስሎ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረት ፡ የሚሠሩ ፡ ይሆናሉ ።"

ጠብቅ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ምዕራፉ ፡ በትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ አዲስ ፡ ሐሳብን ፡ ያዘለ ፡ ሳይሆን ፤ የነበረውን ፡ ባህል ፡ በግልጽ ፡ የሚወስንና ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለተባለው ፡ ባህል ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚሰጠው ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ የጥንቱ ፡ ረቂቅ[3] ፡ ሊያስተዳድራቸው ፡ አቅዶ ፡ የነበረው ፡ ሁለት ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የተከፈሉት ፡ በሃይማኖትና ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገርም ፡ "የሕዝቡ ፡ የአኗኗር ፡ ዘዴ ፡"[4] በሚሉት ፡ መንታ ፡ መመሪያዎች ፡ ነበር ።

በረቂቁ ፡ እንዲተዳደር ፡ የታቀደው ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፤ ማለት ፡ በአክለ ፡ ጉዛይ ፤ በሰራዬና ፡ በሐማሴን ፡ ያለው ፡ ክርስቲያንና ፡ በትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ዘላን ፡ ያልሆነ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደር ፡ ሲሆን ፤ የሚበዛው ፡ መሬትን ፡ እንደ ፡ "ቤተ ፡ ሰብ ፡" ወይም ፡ "መንደር ፡" ንብረት ፡ የሚገምት ፡ ነው ።

በረቂቁ ፡ እንዲተዳደር ፡ የታቀደው ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ሕዝብ ፡ በተለይ ፡ በአዳልና ፡ በሱማሌ ፤ እንዲሁም ፡ ቆላ ፡ በሆነው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት፡ ውስጥ ፡ ተበታትኖ ፡ የሚገኘው ፡ ክርስቲያን ፡ ያልሆነው ፡ ዘላኑ ፡ ሕዝብ ፡ ነበር ።[5] ይህ ፡ ሕዝብ ፡ መሬትን ፡ እንደ ፡ "ጎሣ ፡" ንብረት ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

ከላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ክፍሎች ፡ ባንዱ ፡ በሚመደበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ እንኳ፡ በየቀበሌው ፡ በባህልና ፡ ልማድ ፡ ልዩነት ፡ መኖሩን ፡ አርቃቂው ፡ ቢያውቁም ፤ ሁለቱን ፡ ዓይነት ፡ ሕዝብ ፡ የሚያስተሳስር ፡ በቂ ፡ ተመሳሳይ ፡ ልማድ ፡ መኖሩን ፡ በማመን ፡ ዘላኑንና ፡ በእርሻ ፡ የሚኖረውን ፡ ሕዝብ ፡ በአንድ ፡ የሕጉ ፡ ክፍል ፡ በሆነ፡ ምዕራፍ ፡ ስር ፡ ሊያስተዳድሯቸው ፡ ወስነው ፡ ነበር ።[6]

"አግሪካልቸራል ፡ ኮሚውኒቲስ ፡" (በፈረንሣይኛው ፡ "ሌ ፡ ኮሙናውቴ ፡ አግሬር ፡") የሚለው፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ በተለመደ ፡ ትርጉሙ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደር ፤ ዘላን ፡ ያልሆነን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያመለክት ፡ ቢሆንም ፤ የምንመረምረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ በእንግሊዝኛው ፡ "አግሪካልቸራል ፡ ኮሚውኒቲስ ፡" ሲል ፡ ከላይ ፡ የጠቀስናቸውን ፡ ሁለቱንም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ በማጠቃለል ፡ ነው ። በዚህም ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ ተርጉመን ፡ የምንጠቀምበት ፡ በዚሁ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፷፪ና ፡ በተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ከታቀዱት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ

3. አር ፡ ዳቪድ ፤ ደ ፡ ሌክስፕሎይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቮ ፡ ዲዚመብል ፤ ቻፒትር ፡ ፕረምየር ፤ ዴ ፡ ኮሙናውቴ ፡ አግሬር ፤ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፶፩ ፤ (፲፱፻፵፱ ፡ ዓ· ም· ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ።

4. አር ፡ ዳቪድ ፤ ኤክስፖዜ ፡ ዴ ፡ ሞቲፍ ፡ ኤ ፡ ከማንቴር ፡ ዴ ፡ ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፶፱ ፡ ኤ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፶፩ ፡ ሬለቲፍ ፡ ደሜን ፡ ፑብሉክ ፤ አ ፡ ሌ ፡ ክስፕሮፕሪያሲዮን ፡ ኤታ ፡ አሌክስፕሎይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡ ዴ ፡ ቢያን ፤ ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፳፫ ፤ (፲፱፻፵፱ ፡ ዓ· ም· ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ ፤ ገጽ ፡ ፫) ፡

5. ለክቡር ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንትና፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ አባል ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ· ም· ከተደረገ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ።

6. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ።

የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ እንደ ፡ መመሪያ ፡ የተጠቀሙባቸውን ፡ ሕዝቦች ፡ ሁኔታ[7] ፡ በዝርዝር፡ እንመረምራለን ። በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በአንዳንድ ፡ ቀበሌዎች፥ ፡ የሚገኙ ፡ ሕዝቦችን ፡ ባህል ፡ በዝርዝር ፡ ለመመርመር ፡ የተገደድነውም ፤ ረቂቅ ፡ አውጪው ፡ ለሚያዘጋጁት ፡ ሕግ ፡ መመሪያ ፡ ያደረጉት ፡ የእነዚህን ፡ ባህል ፡ የሚመለከቱ ፡ ጽሑፎችን ፡ ስለነበር ፡ ነው[8] ። ስለነዚህ ፡ ቀበሌዎች ፡ ባህል ፡ የሚገልጹ ፡ ጽሑፎች ፡ እጅግ፡ ጥቂት ፡ ቢሆኑም ፥ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ የልማዳዊ ፡ ሕጎቻቸውን ፡ ግልባጮች በማግኘቱ ፡ ጥናቱን ፡ የተሟላ ፡ ሊያደርግለት ፡ ችሏል ። የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የሚገኙባቸውን ፡ ቀበሌዎች ፡ ሕዝብ ፡ ባህል ፡ ዓይነተኛ ፡ መልክ ፡ አስቀድመን ፡ ከመረመርን ፡ በኋላ ፤ ቀጥለን ፡ የጥንቱን ፡ ረቂቅ ፡ እንመለከታለን ። የጥንቱ ፡ ረቂቅ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ባይኖረውም ፤ ደራሲው ፡ ረቂቁን ፡ ሲያዘጋጁ ፡ በመግለጫ፡ መልክ ፡ የጻፉትን ፡ ሐተታ ፡ ያህል ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የወጣውን ፡ ቃል ፡ ለማስረዳት ፡ እጅግ ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ለማንኛውም ፡ የሕግ ፡ ረቂቅና ፡ የሕግ ፡ ቃል ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ቢሆንም ፤ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ እርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፡ የጥንቱ ፡ አንድ ፡ አስረኛ ፡ ብቻና ፡ የተቆራረጠ ፤ ለመረዳትም ፡ የሚያዳግት ፡ መሆኑን ፡ ስንመለከት ፡ የጥንቱን ፡ ረቂቅ ፡ ጠቃሚነት ፡ ይበልጥ ፡ እንገነዘበዋለን ።

የጥንቱን ፡ ረቂቅ ፡ ከመረመርን ፡ በኋላ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ትርጉም ፡ የሌላቸው ፤ አስቸጋሪ ፡ መስለው ፡ ከሚታዩት ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱—፩ሺ፭፻፪ ፡ ካሉት ፡ ቃሎች ፡ አብዛኞቹን ፡ አንባቢው ፡ ሊረዳ ፡ ስለሚችል ፤ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ማብራሪያ ፡ የምንሰጥበት ፡ ሕጉን ፡ በመመርመር ፡ ልንጠይቃቸው ፡ ስለምንችል ፡ አንዳንድ ፡ ከባድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ነው ፤ ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ አግባብ ፡ ባላቸው ፡ ቁጥሮች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የሚመስለው ፡ አለመስማማት ፡ አለመኖሩን ፡ ለማሳየት ፡ እንሞክራለን ።

ደራሲው ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ሳለ ፤ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክፍል ፡ ጉድለት ፡ ሳይኖርበት ፡ አይቀርም ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ አድሮበት ፡ ነበር ። ሕጉ ፡ በአንዳንድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ "በኅብረት ፡ (ማለት ፡ በተራድዖ ፡) የሚታረስ ፡" መሬት ፡ አለ ፤ በሚል ፡ አስተያየት ፡ የተመራ ፡ ስለመሰለው ፤ ሕጉ ፡ እንዲያስተዳድራቸው ፡ ስለታቀዱት ፡ አንዳንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ለመረዳት፡ ባደረገው ፡ ጥናት ፡ ስለነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ መረጃ ፡ አጋጥሞታል ። ይህም መረጃ ፡ በቀላሉ ፡ የማይገኝ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ጽሑፍም ፡ ውስጥ ፡ ተገቢ ፡ ቦታውን ፡ ይዞ ፡ መገኘት ፡ ያለበት ፡ በመሆኑ ፡ ደራሲው ፡ ጨምሮት ፡ ይገኛል ። በተጨማሪም ፡ ይህ ፡ መረጃ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ና ፡ ተከታዮቹ ፡ ሊሻሻሉ ይገባል ፤ ሲል ፡ በጽሑፉ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ ደራሲው ፡ ለሚያቀርበው፡ አስተያየት ፡ እጅግ ፡ የሚጠቅም ፡ ስለሆነ ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል ።

ከላይ ፡ እንደተናገርነውም ፡ ሁሉ ፤ በአንዳንድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ የሚገኘውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍል ፡ ሁኔታ ፡ ላላወቀ ፡

---

7. ከዚያው ።
8. እነዚህም ፡ ኤፍ ፡ አስቲኒ ፤ ዲሪቶ ፡ ኮንሲዌቱዲናሪዮ ፡ ዴል ፡ ኤሪትሪያ ፡ (፲፱፻፶፮ ፡ ዓ- ም- ) ፡ እና ፡ ሲ ፡ ሮሲኒ ፤ ዲሪቶ ፡ ኮንሱዌቱዲናሪዮ ፡ ዴል ፡ ኤርትሪያ ፡ (፲፱፻፲፮ ፡ ዓ- ም- ) ናቸው ።

ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፶፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡ ትርጉም ፡ የማይሰጡ ፡ በመሆናቸው[9] ፤ ይህ ንኑ ፡ ሁኔታ ፡ አስቀድሞ መመልከት ፡ ይገባል ።

## ክፍል ፩

## የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስለሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ሕዝብ ፡ ዓይነተኛ ፡ ባህል ፤

በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የምንመረምረው ፤ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የኅብ ረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ከሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ የዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ሕዝ ቦች ፤ ማለትም ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ በሰራዬ ፤ በሐማሴንና ፡ በአክለ ፡ ጉዛይ ፡ የሚኖሩ ፤ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ክርስቲያኖችንና ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በስተምሥራ ቅና ፡ በስተምዕራብ ፡ የሚገኙ ፤ ክርስቲያን ፡ ያልሆኑ ፡ ዘላኖችን ፤ ባህል ፡ ዓይነተኛ ፡ መልክ ፡ ነው ። በየመንደሩ ፡ ሊኖር ፡ የሚችለውን ፡ የባህል ፡ መለያየት ፡ ወደጐን ፡ ጥለን ፤ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮችን ፡ ብቻ ፡ እንገልጣለን ።

የኤርትራ ፡ መልክዓ ፡ ምድርና ፡ የአየር ፡ ጠባይ ፡ ሁኔታ ፡ ጥንት ፡ ከላይ ፡ በጠቀስ ናቸው ፡ በዘላኖቹና ፡ ሰፍረው ፡ በሚኖሩት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ የወ ሰን ፡ ክልል ፡ ሆነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ "--- ተመሳሳይ ፡ መልክዓ ፡ ምድር ፡ ባላቸውና ፡ በእምነታቸው ፡ በለጥ ፡ ብለው ፡ በሚታዩት ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሰፈረው ፤ የጋራ ፡ ቋንቋ ፡ (ትግርኛ) የተስፋፋ ፡ ሃይማኖት ፡ (አርቶዶክስ ፤) እና ፡ ሲወ ርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያለው ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደር ፡ ሕዝብ ፡ ነው ። በስተምሥራቅና ፡ በስተምዕራብ ፡ የሚገኙት ፡ በረሀ ፡ ቀመስ ፡ ቀበሌዎች ፡ ግን፡ በብዛትና ፡ በአቋቋም ፡ ቢለያዩም ፡ ዘላንነትና ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ በሆነው ፡ ኑሯቸውና ፡ በጋራ ፡ እምነታቸው ፡ በእስልምና ፡ የተሳሰሩ ፡ የብዙ ፡ ጎሳዎች ፡ መኖሪያዎች ፡ ናቸው።"[10]

ስለዚህም ፤ "---በደጋው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙት ፡ የሐማሴን ፤ የአክለ ፡ ጉዛይና ፡ የሰራዬ ፡ ቀበሌዎች ፡ በትክክለኛ ፡ አነጋገር ፡ የተለዩ ፡ 'ሀገሮች ፡' ሲሆኑ ፤ በታሪክ ፡ በጠ ባይ ፡ በባሕል ፡ እንኳን ፡ ከሌላው ፡ የማይገጥሙ ፡ ናቸው ፤ ሕዝቡም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ እንዳለ ፡ ያውቀዋል ።"[11]

---

9. "የኤርትራ ፡ ልማዳዊ ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ከሕዝቡ ፡ ታሪክ ፡ አኗኗርና ፡ ባሕል ፡ ጋር ፡ የተወሳሰበ ፡ ነው። የነዚህ ፡ የተያያዙ ፡ ጉዳዮች ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነጥቦች ፡ ተዛምደው ፡ ካልተመረመሩ ፡ ሁኔታው ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ አይታይም ።" አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ላንድ ፡ ቴኒዩር ፡ ኢን ፡ ኤሪትሪያ ፤ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ- ም-) ገጽ ፡ ፩ ።

10. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ሬስስ ፡ ኤንድ ፡ ትራይብስ ፡ እፍ ፡ ኤሪትሪያ ፡ (፲፱፻፴፩ ዓ- ም-) ገጽ ፡ ፩ ።

11. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፴ ።

# ምዕራፍ ፡ ፭

## በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፡ ስለሚገኙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋምና ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፤

### ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡

### ስለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋማቸው ፡-

የኤርትራን ፡ የክርስቲያን ፡ ሕዝቦች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም ፡ ከመሬት ፡ ስሪታቸው ፡ ነጥሎ ፡ ማጥናት ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ አይመስልም ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የማይነጣጠሉ ፡ ተደራራቢ ፡ ጉዳዮች ፡ ስለሆኑ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ መታየት ፡ ይገባቸዋል ። በቅርቡ ፡ እንደምናመለክተው ፡ ሁሉ ፤ በእነዚህ ፡ ቀበሌዎች ፡ የሚገኘው ፡ ሕዝብ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮው ፡ "የተመሠረተው ፡" በመሬት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፤ የሕዝቡ ፡ መብትና ፡ ግዴታም ፡ የሚወሰነው ፡ "መሬት ፡ ባለውና ፡ በሌለው ፡" በሚል ፡ ክፍያ ፡ መሠረት ፡ ነው። ሆኖም ፡ ጉዳዩን ፡ ግልጥ ፡ አድርገን ፡ ለማስረዳት ፡ ቀጥለን ፡ ስለሕዝቡ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ብቻ ፡ አንዳንድ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦችን ፡ እናመለክታለን ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በትክክል ፡ እንደተገለጠው ፤ "---በኤርትራ ፡ በሚገኙ ፡ ደጋ ፡ አውራጃዎች ፡ (ሐማሴን ፤ አክለ ፡ ጉዛይና ፡ ሰራዬ ፡) ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ የሆኑ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ የሀበሻ ፡ ሕዝቦች ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ሁለት ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ ነበራቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ባንድ ፡ በኩል ፤ በየመንደሩ ፡ የሚገኙ ፡ የመንግሥት ፡ መልክ ፡ ያላቸው ፡ አቋሞች ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በኤርትራ ፡ 'መንግሥቲ ፡' የሚባለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ማዕከላዊ ፡ መንግሥት ፡ (ናቸው) ።[12]"

"ለገበሬው ፡ ሕዝብ ፡" ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የፖለቲካ ፡ አቋሞች ፤ የመንደሩ ፡ (አነስተኛው) እና ፡ የቀበሌው ፡ (ከፍተኛው ፡) ናቸው[13] ። የመጀመሪያው ፡ የሚተዳደረው ፡ በጭቃ[14] ፡ ነው ። ብዙ ፡ መንደሮች ፡ የሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ደግሞ ፡ ኃላፊያቸው በሆነው ፡ በምስለኔ ፡ ስር ፡ ይተዳደራሉ ።

በብዙዎች ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ ጭቃው ፡ ማዕከላዊውን ፡ መንግሥትና ፡ መንደሩን ፡ የሚያገናኝ ፡ ሹም ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል ፤ ግብር ፡ ይሰበስባል ፤ የመንግሥትንም ፡ ትእዛዝ ፡ ለሕዝብ ፡ ያስተላልፋል ።[15] የዕለት ፡ ተግባራቸው ፡ ክርክር ፡ ሰምቶ ፡ መወሰን ፡ የሆነ ፡ ዳኞች ፡ ቢኖሩም ፡ ጭቃው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በዳኝነት ፡ መልክ ፡ አንዳንድ ፡ አነስተኛ ፡ ወንጀሎችን ፡ ይመለከታል ።[16] በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ ጭቃው ፡ በልማድ ፡

---

12. ዲ ፡ ዱንካንሰን ፤ "ስራት ፡ አድከመ ፡ ምልጋ ፤ ኤ ፡ ኔቲቭ ፡ ኮድ ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ኤሪትሪያ" ፤ አፍሪካ ፤ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ቁጥር ፤ ገጽ ፡ ፩፻፵፩ ።
13. ኤስ ፡ ናዴል ፤ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ኦን ፡ ኤሪትሬያን ፡ ፕላቶ ፡ (፲፱፻፴፮ ፡ ዓ- ም- ፡ ፎቶ ፡ ኮፒ ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መዝገብ ፡ ቤት) ፤ ገጽ ፡ ፳ና ፡ ተከታዮቹ ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ አፍሪካ ፤ በሚለው ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ በ፯ኛው ፡ ቮልዩም ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፳፪ ፤ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ- ም- ታትሞ ፡ ነበር ።
14. ገብረ ፡ ወልድ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፤ "ኢትዮፒያስ ፡ ትራዲሽናል ፡ ሲስተም ፡ ኦፍ ፡ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ኤንድ ፡ ታክሴሽን ፤" ኢትዮፒያ ፡ ኦብዘርቨር ፤ ፭ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፱ ዓ- ም- ) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፪ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፡ ጋር ፡ ይወዳድሯል ።
15. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፩ ።
16. ከዚያው ።

ባለው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚያስተላልፉቸውን ፡ ትእዛዞች ፡ መንደረተኞች ፡ ሁሉ እንዲቀበሉ ፡ ይገደዳሉ ።[17]

"የዘር ፡ (ወይም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡) ርስት" በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሕዝቡ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የተመሠረተው ፡ በዝምድና ፡ ላይ ፡ ነው ።[18] መሠረታዊው ፡ አቋም ፡ "እንዳ ፡" ይባላል ፤ በውስጡም ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ተወላጆች ፡ ይገኙበታል ። "በታሪክ ፡ መሠረት ፡ እንግዲህ ፣ እንዳ ፡ ካንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፣ ማለት ፡ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ ተነስቶ ፡ ያደገ ፡ ሲሆን ፣ ከደረጃም ፡ በኋላ ፡ በቁጥር ፡ በጣም ፡ የሚለያዩ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይኖሩበታል ። እነዚህ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ የኢኮኖሚና ፡ የዕለታዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም፡ ናቸው ፤ ማለትም ፡ በውስጣቸው ፡ የሚገኙት ፡ አብረው ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፣ አብረው ፡ የሚሠሩና ፣ የጉልበታቸውንም ፡ ፍሬ ፡ የሚካፈሉ ፡ በቁጥር ፡ አነስ ፡ ያሉ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ቤተሰብ ፡ አባሎች ፡ (ወላጆችና ፡ ልጆች ፡) ናቸው ።"[19] ምንም፡ እንኳ ፡ ሚስተር ፡ ናዴል ፡ የተባሉት ፡ ጸሐፊ ፡ እንዳ ፡ የመንደርን ፡ የሚመስል ፡ መሪ ፡ ወይም ፡ አለቃ ፡ የለውም ፡[20] ቢሉም ፣ የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ እንዳዎች ፡ አለቆች ፡ አሏቸው ።

የሰራዬ ፡ ጭቃ ፣ ባለመሬት ፡ (ባላባት ፡) የሆነ ፣ ጥንትም ፡ አያት ፡ ቅድመ ፡ አያቶቹ፡ ጭቃ ፡ ከነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ዘር ፡ የወረደ ፡ መሆን ፡ አለበት[21] ። አያት ፡ ቅድመ ፡ አያቶቹ ፡ ጭቃ ፡ የነበሩ ፡ ሰው ፡ ለጭቅነት ፡ የታጣ ፡ እንደሆነ ፣ ሹመቱ ፡ የሚሰጠው ፡ በውርስ፡ የተላለፈ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ለማንኛውም ፡ ባለመሬት ፡ ነው ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፣ ጭቃ፡ ለመሆን ፣ በውርስ ፡ የተላለፈ ፡ ርስት ፡ ባለቤት ፡ መሆን ፡ ያሻል ፤ ምክንያቱም ፡ "ጭቅነት ፡ በውርስ ፡ የተላለፈ ፡ መሬትን ፡ ይመስላልና ።"[22]

እዚህ ፡ ላይ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ "ባለ ርስት" ፣ "ርስት ፡ የሌለው ፡" የሚባሉትን ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ክፍሎች ፡ አንባቢ ፡ መገንዘቡ ፡ አይቀርም ። ይህ ፡ በኅብረ ፡ ሰብእ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ የሚታየው ፡ ልዩነት ፡ "የመንደር ፡ ርስት ፡" ይገኝባቸዋል ፡ በሚባሉት ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥም ፡ ያለ ፡ ነው ።

የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ "(እያንዳንዱ ፡) እንዳ ፡ የተሰጠው ፡ የመሬት ፡ መብት ፤ ---በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ጥንት ፡ የነበረውን ፡ የማኅበራዊ ፡ አቋም ፡ ልዩነት ፡ የሚያስታውስ ፣ የአቋሙ ፡ መሠረትም ፡ የተጣለበት ፡ ነው ። በዚህም ፡ ልዩነት ፡ መሠረት ፣ ባንድ ፡ በኩል ፡ የሀገሪቱ ፡ ጥንታውያን ፡ ነዋሪዎች ፡ ተብለው፡ የሚገመቱ ፡ ሰዎች ፡ ሲኖሩ ፣ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ መጦች ፡ ይገኛሉ" ።[23]

17. ሥርዓት ፡ አድከመ ፡ ምዕልጋ ፡ (በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ እየተባለ ፡ የሚጠቀሰው ፣ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የተረጐመው ፡ ተስፋ ፡ ጽዮን ፡ መድኃኔ ፤ ያልታተመ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ) ፣ "የየመንደረተኛው ፡ ግዴታዎች ፡" በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
18. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፫ ።
19. ከዚያው ።
20. ከዚያው ።
21. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፣ "ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡" በሚል ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
22. ከዚያው ።
23. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፴፰ ። ከጊዜ ፡ ማለፍና ፡ መሬት ፡ የመግዛት ፡ እድልም ፡ ከመኖሩ ፡ ይህ ፡ ልዩነት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄዷል ።

የመጀመሪያዎቹ ፡ ባለርስቶች ፡ ሲሆኑ ፣ የኋለኞቹ ፡ ግን ፡ ርስት ፡ የላቸውም ። ከዚህም፡ ልዩነት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተከትሎ ፡ ይገኛል ።

የባለርስተኞች ፡ ተወላጅ ፡ መሆን ፡ (ሪም ፡ የሚባሉ[24]) ፡ መብቶችንና ፡ ጥቅሞችን ፣ የኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ መሪ ፡ መሆንንም ፡ ጭምር ፣ ያስገኛል ። በአክለ ፡ ጉዛይ ፣ በሰራዬና ፡ በሐማሴን ፡ ውስጥ ፣ ለሽምግልና ፡ ሊመረጡ ፡ የሚችሉት ፡ ባለርስቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። "(ሽምግልነትም ፡) የየመንደሩን ፡ የአስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ያጠቃልላል። ለምሳሌም ፡ ያህል ፡ ሕዝቡን ፡ በማኅበር ፡ ለማሠራት ፡ ማደራጀትና ፡ ሥራውንም ፡ መቆጣጠር ፣ ለመንደሩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተገቢው ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ መቆጣጠር ፣ የመንደሩን ፡ ማሳዎችና ፡ ግጦሽ ፡ የሚጠብቁ ፡ ዘበኞችን ፡ መሾም ፣ የርስት ፡ ክርክር ፡ ሲነሣ ፡ በእርቅ ፡ አይቶ ፡ የመወሰን ፡ መብት ። እነዚህ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች፡ ከሹመት ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፣ ሹመቱ ፡ በየተራና ፡ ከተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፣ ይበልጡንም ፡ ጊዜ ፡ ባመት ፣ ለየቤተሰቡ ፡ ይተላለፋል ።"[25]

ሆኖም ፡ መታወስ ፡ ያለበት ፡ የባለመሬቶች ፡ ወገን ፡ መሆን ፡ "--- ከመሬት ፡ ይልቅ ፡ ዘላቂና ፡ በሌላም ፡ ሰው ፡ ሊወሰዱ ፡ የማይችሉ ፡ መብቶችን ፡ የሚያስጥ ፡ መሆኑን ፡ ነው ። የዘር ፡ ርስት ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይዞታውን ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ሊያከራይ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ከዘመናት ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ መያዙ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አይረሳም ። በተጨማሪም ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚቆይ ፣ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፣ "አዲስ ፡ መጦችን ፡" በዝቅተኛ ፡ አስተያየት ፡ የሚመለከት ፡ የከበርቴዎች ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ ያደርገዋል ።"[26] ስለዚህም ፡ አንዳንዴ ፣ መሬት ፡ ከመያዝ ፡ ይልቅ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ መሆን ፡ ይበልጥ ፡ ተፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

"ዝቅተኛ ፡" ወይም ፡ "አዲስ ፡ መጥ ፡" ከሚባሉት ፡ መካከል ፡ በየክርስቲያኑ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ እስላሞች ፡[27] ይገኙበታል ። ሰራዬ ፡ ውስጥ፡ ባሮች ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩ ፡ ሰዎች፣ ቀጥቃጮችና ፡ መለከት ፡ ነፊዎች ፡ እንደ፡ "ውጭ ፡" ሕዝብ በመቆጠር ፡ መሬትና ፡ ከመሬት ፡ የሚገኙ ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ይነፈጋቸዋል ። ይህንንም ፡ እገዳ ፡ የሰራዬ ፡ ሕግ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በትህትና ፡ ይገልጸዋል ፣ ቀጥቃጮችና፡ መለከት ፡ ነፊዎች ፡ ከግብር ፡[28] "ነፃ" ፡ ናቸው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነትን ፡ ማሳየቱን ፡ ይገነዘቧል። ይህ ፡ አባባል ፡ በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል።[29] የሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ በከፊል ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ። "በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ግዛት ፡

---

24. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታረሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፫ ።
25. ከዚያው ።
26. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፬ ።
27. በቤገምድር ፣ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ መካራ ፡ የሱስ ፡ በሚባል ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ በዘርና ፡ በሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ ፈላሻዎች ፡ (ቤተ ፡ እስራኤላውያን) ፡ እና ፡ እስላሞች ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነት ፡ አይሰጣቸውም ። ደበበ ፡ ወርቁ ፣ ዘ ፡ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ሲስተም ፡ ኢን ፡ መካራ ፡ የሱስ ፡ ኮሚውኒቲ ፡ ኤንድ ፡ ኢትስ ፡ ኢፌክትስ ፡ ኦንዘ ፡ አግሪካልቸራል ፡ ሌበር ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያልታተመ ፣ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ ፣) ገጽ ፡ ፫ - ፬ ።
28. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ "ባለእጆች" ፣ በሚል ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
29. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ (ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የተረጐመው ፡ ዮሐንስ ፡ ሃብተ ፡ ሥላሴ ፣ ያልታተመ፣ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያለ ።)

ክልል ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ እያረሰ ፡ ለንጉሥ ፡ ግብር ፡ የማይከፍል ፡ ሰው ፡ ባለመሬት፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ሊሰይም ፡ መብት ፡ የለውም ። ግብር ፡ ሳይከፍል ፡ አርባ ፡ ዓመታት ፡ ቢያልፉ ፡ ግን ፤ --- ግብር ፡ ለመክፈል ፡ ለሚችል ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ መሬቱ ፡ ይሰጥበታል ። ---ሰውየው ፡ ነፃ ፡ ነው ፤ መሬቱ ፡ ግን ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ አይደለም ።”

ይህ ፡ የግብር ፡ ጉዳይ ፤ አንድ ፡ ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ ያሳስበን ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፤ ማዕከላዊው ፡ መንግሥት ፡ በየመንደሩ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ተጽዕኖ ፡ ምንድነው ? የሚለው ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በቀደም ፡ እንደቀረበው ፡ አስተያየትና ፡ ይህንንም ፡ አስተያየት ፡ እንደሚደግፉት ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ የማዕከላዊው ፡ መንግሥት ፡ ተጽዕኖ ፡ እጅግ ፡ ያነሰ ፡ ነው ። “ጥንቱንም ፡ በነዚህ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ በየመሪዎቻቸው ፡ ይተዳደሩ፡ ነበር ። ከሚገዙት ፡ ቀበሌ ፡ ያልተወለዱት ፡ የማዕከላዊው ፡ መንግሥት ፡ ሹማምንቶች ፡ እንደ ፡ ግብር ፡ ሰብሳቢ ፡ ብቻ ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።”[30]

አስቀድመን ፡ እንደገለጥነው ፤ ማዕከላዊውን ፡ መንግሥት ፡ በየመንደሩ ፡ ይወክሉ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ የባለመሬት ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ጭቃዎች ፡ ነበሩ ። መሬት ፡ ለማግኘት ፡ ተወላጅነት ፡ ያን ፡ ያህል ፡ አስፈላጊ ፡ በማይሆንበት ፤ “የመንደር ፡ መሬት ፡” እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ ስሪት ፡ ባለበት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥም ፡ እንኳ ፤ ጭቃ ፡ ለመሆን ፤ ጥንት ፡ መሬት ፡ ከነበራቸው ፡ ሰዎች ፡ መወለድ ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ።[31]

የሕዝቡን ፤ ጉዳይ ፡ በኃላፊነት ፡ እየተከታተሉ ፡ የሚያስፈጽሙት ፡ ሰዎች ፤ ከተራው ፡ ሰው ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ መታየታቸው ፡ ባንዳንድ ፡ ለነሱ ፡ ብቻ ፡ በተጠበቀ ፡መብታቸው ፡ ይታያል ። በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ ላም ፡ የሚያርድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ምላሱን ፡ (ልሳን ፡ ማንቃ ፡) ለጭቃው ፡ መስጠት ፡ አለበት ።[32] በሰራዬም ቢሆን ፡ “ተዝካር ፡ ወይም ፡ ሠርግ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፤ ለቀበሌው ፡ አለቃ ፤ ለሕግ ፡ ጠባቂውና ፡ ለመንደሩ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ እንስራ ፡ ጠላ ፤ አንድ ፡ ድስት ፡ ወጥና ፡ አምስት ፡ እንጀራ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።”[33] ፡ ይህን ፡ በማይፈጽም ፡ ላይ ፡ ተገቢው ፡ መቀጫ ፡ ይጣልበታል ።

ዳግመኛም ፡ በሰራዬ፡ ውስጥ ፤ ጭቃው ፡ የየመንደሩን ፡ ሠርገኛ ፡ ለመመረቅ ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ አለው ፤ ይህም ፡ መብት ፡ ጭቃው ፡ ሁልጊዜ ፤ በተለይም ፡ በሠርግ ጊዜ ፤ ከመንደሩ ፡ እንዳይጠፉ ፡ ያስገድደዋል ።[34]

ለጭቃዎች ፡ ከሚሰጡት ፡ መብቶች ፡ ከፍተኛውን ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ የሚገኘው ፡ ግን ፡ የየመንደሩ ፡ አባል ፡ በመሆን ፡ ከሚያገኙት ፡ መሬት ፡ ሌላ ፤ በጭቅነታቸው ፡ መሬት ፡ ሊያስገኝላቸው ፡ የሚችለው ፡ መብታቸው ፡ ነው ።[35]

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎችን ፡ ላንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ በመጥቀሳችን ፡ የምንመረምራቸው ፡ ልማድን ፡ አጥብቀው ፡ የሚከተሉ ፡ ሕዝቦች ፡ የየራሳቸው

---

30. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፴፯ ።
31. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፴፯ ።
32. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፭፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፰ ። የአንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ አርእስት ፡ “የመሬት ፡ ግብር” ፡ ማለቱ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ።
33. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፭፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፶፩ ።
34. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፮ ፡ የተጠቀሰው ፤ “ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች” ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
35. ከናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲፫ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከናዴል ፤ ጽሑፍ ፡ ከገጽ ፡ ፷—፷፩ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

የሆኑ፡ሕጐች ፡ እንዳሉዋቸው ፡ መገመታችን ፡ ግልጥ ፡ ነው። በአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ይበልጡኑ ፤ "ምዕን ፡ መሐዛ ፡" የተባለውን ፤ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ሲከተል፤ በሰራዬ ፡ የሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ የሚከተለው ፡ "አድከመ ፡ ምዕልጋ ፡" የተባለውን ፡ (በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሰራዬ ፡ ሕግ ፡ እየተባለ ፡ የሚጠቀሰውን ፡) ሕግ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የሐማሴንና ፡ የአክለ ፡ ጉዛይ ፡ አንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ የየራሳቸው ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ አላቸው ።[36] ለምሳሌም ፡ ያህል ፡ ገሚስ ፡ ጐኑ ፡ በሐማሴን ፡ የቀረው ፡ ደግሞ ፡ በሰራዬ ፡ አውራጃ ፡ የሚገኘው ፡ የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ቀበሌ ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ አለው ።

እነዚህ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ኑሮ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ለመቆጣጠር ፡ የታቀዱ ፤ በጣም ፡ ለተሳሰሩ ፡ የቤት ፡ ሰብም ፡ ሆነ ፡ የመንደር ፡ አቋሞች ፡ እጅግ የተስማሙ ፡ ናቸው ።[37] የወንጀለኛ ፡ መቅጫን ፤ የፍትሐ ፡ ብሔርንና ፡ የአስተዳደርን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦችን ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አጠቃለው ፡ የያዙ ፡ ሲሆን ፤ በዝርዝር ፡ የተደነገጉ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደንቦችም ፡ አሏቸው ።

የሚያስደንቀው ፡ ነገር ፤ እነዚህ ፡ ሕጐች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ካህናቶቻቸው ፡ የሚያገኙትን ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ መቆጣጠራቸው ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ መንፈሳዊና ፡ ዓለማዊ ፡ ጉዳዮችን ፡ እንደሚያስተዳድረው ፡ እንደፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሳይሆኑ ፤ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አባሎችም ፡ ሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባውን ፡ አንዳንድ ፡ ሃይማኖታዊ ፡ መመሪያ ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ የሏቸውም ።

ከላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈሩት ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ነው ።[38] ጥንት ፡ "---በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የየመንደረተኛውን ፡ ጉዳይ ፡ ለመቆጣጠር ፡ አነስተኞቹ ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ ይገለገሉበት ፡ የነበረው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተገልጦ ፡ ይገኝ ፡ የነበረው ፡ በምሳሌያዊ ፡ አነጋገር ፡ ሲሆን ፡ ---ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በጽሑፍ ፡ እንዳልዋለ ፡ ሕግ ፡ ይቆጠር ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለበት ፡ የእያንዳንዱ ፡ ምሳሌያዊ ፡ አነጋገር ፡ ምንጭ ፡ በመታወቁ ፡ ነበር ። "[39]

እነዚህ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈሩበትን ፡ ምክንያት ፡ መገመት ፡ አያዳግትም ። ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ "ስርዓት ፡ አድከመ ፡ ምዕልጋ ፡" (በ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ፡) ስለተባለው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ሲጽፉ ፡ ጥቂቶ

---

36. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፴፮ ። የእንግሊዝ ፡ የሚሊታሪ ፡ አስተዳደር ፡ እነዚህን ፡ ሕጐች ፡ ኮድስ ፡ (የተቀናጁ ፡ ሕጐች) ፡ በማለት ፡ ይጠራቸዋል ።

37. የነዚህን ፡ ቋሞች ፡ ቍጥር ፡ የሚገልጥ ፡ ሰነድ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም ። ሆኖም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ታቅደው ፡ የነበሩት ፡ በትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኙ ፡ ተመሳሳይ ፡ መንደሮች ፡ ከ፪፻ - ፭፻ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚገኙባቸው ፡ ደራሲው ፡ አረጋግጧል ። በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለአቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ከተደረገ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ። በቄስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ እና ፡ ሌሎች ፡ ይግባኝ ፡ ባዮችና ፡ በግራዝማች ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፤ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ (የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፹፱/፶፱ ፡ (ያልታተመ) ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በትግሬ ፡ የሚገኝ ፤ የምንመረምራቸውን ፡ ክፍሎች ፡ የሚመስል ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ ፩፻፹፰ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚኖሩበትና ፤ "የሚተዳደረውም ፡" በሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ መሆኑን ፡ ይገልጣል ።

38. ኤፍ ፡ ራስል ፤ "ኤሪትሪያን ፡ ከስተማሪ ፡ ሎው ፤ " ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ አፍሪካን ፡ ሎው ፤ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፤ (፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፤ ገጽ ፡ ፩፻፪ ። ከነዚህ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈሩት ፡ ከሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ነው ።

39. ዱንካንሰን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፴፩ ።

ቹን ፡ ምክንያቶች ፡ ገልጠዋቸዋል ። "የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ ማደግ ፣ ከጠላት ፡ ወረራ ፡ (ከ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ካለው ፡ ዘመን) ፡ ወዲህ ፡ የከተማ ፡ ኑሮ መደርጀትና ፡ የኢጣሊያም ፡ ወታደር ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መሸነፍ ፡ በኤርትራ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ላይ ፡ ያስከተለው ፡ ውጤት ፡ ሁሉ ፡ ተደምሮ ፡ በደጋው ፡ የሚኖረውን ፡ ሕዝብ ፡ የመንደር ፡ ኑሮ ፡ አቃውሶት ፡ ነበር ። ተስማሚ ፡ ሆነው ፡ ያልተገኙትም ፡ ከሀበሻ ፡ ባህል ጋር ፡ እጅግ ፡ የተወሳሰቡት ፡ ውርስን ፣ የመንደር ፡ ሹመትንና ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ማከፋፈልን ፡ የሚመለከቱት ፡ ልማዳዊ፡ ሕጐች ፡ ነበሩ ። ልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ ሕዝብ ፡ በሚያውቀውና ፡ በሚቀበለው ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠ ፡ ባለመሆኑ ፡ ክርክርና ፡ ጭቅጭቅ ፡ እጅግ ፡ እየበዛና ፡ ለመወሰንም ፡ እያዳገተ ፡ ሄደ ። አነስተኛው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ የሀበሻው ፡ ሕዝብ ፡ ባህል ፡ የፈረንጆች ፡ አስተሳሰብና ፡ ባህል ፡ ተቀይጦበት ፡ እንዳይለወጥና ፡ ጨርሶም ፡ እንዳይጠፋ ፡ ራሱን ፡ ሊያስታውቅና ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ያደረገው ፡ ሙከራ ፡ ነበር ።"[40]

"አድገና ፡ ተገለባ ፡" (በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ሕግ ፡ እየተባለ ፡ የሚጠቀሰው ፡) በጽሑፍ ፡ እንዲሰፍር ፡ ያደረጉት ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ እርምጃ ፡ የወሰዱበትን ፡ ምክንያት ፡ ጥሩ ፡ አድርገው ፡ በሕጉ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ ገልጠውታል ።[41] ያልተስተካከለ ፡ ትርጉም ፡ ላለመስጠት ፡ ስንል ፡ ይህንኑ ፡ ምክንያት ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ቀጥለን ፡ ጠቅሰነዋል ።

"የሁሉ ፡ ፈጣሪና ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ እግዚአብሔር ፡ በስነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚተዳደር ፡ ስለሆነ ፣ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ በስነ ፡ ሥርዓት ፡ ፈጥሮ ፣ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በመልክ ፡ በመልካቸው ፡ በየቦታው ፡ መድቦ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ በተወሰነው ፡ ደንብ ፡ እንዲኖሩ ፡ አደረገ ።

እነሆም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጡራን ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ይኖራሉ ።

ይህ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ አክባሪነት ፡ የማሰብ ፡ ችሎታ ፡ ላለው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ተሰጥቷል ፣ (የሕጉ ፡ መግቢያ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የአዳምንና ፡ የሔዋንን ፡ አፈጣጠር ፡ ይተርካል ፡) ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ከአዳም ፡ ውድቀት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ድረስ፡ የተጻፈ ፡ ሕግ ፡ ስላልነበረው ፡ ሕሊናው ፡ ባመለከተው ፡ ብቻ ፡ ሲተዳደር ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ በጽሑፍ ፡ ባልሰፈረ ፡ ሕግ ፡ ሊተዳደር ፡ አልቻለም ፣ ምክንያቱም ፣ በሕሊና ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ የሰውን ፡ ችግር ፡ ለመቋቋም ፡ በቂ ፡ አልነበረምና ፣ ስለ ዚህም ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ ፡ ሕግ ፡ በሙሴ ፡ ተጀመረ ። (የሙሴ ፡ ታሪክ ፡ ይቀጥላል). . .

ከክርስቶስም ፡ ወዲህ ፣ ለየጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ ማስፈለጉን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተረድቶት ፡ ነበር ። . . . ቆስጠንጢኖስ ፡ እንኳ ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ሊቃውንት ፡ ያዘጋጁት ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተባለ ፡ ሕግ ፡ ነበረው ።

ሕግ ፡ ማለት ፡ በእግዚአብሔር ፣ መኳንንትና ፡ በተራው ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ሰላምና ፡ ስምምነት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ የሚያደርግ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ።

---

40. ከዚያው ፣ ገጽ ፡ ፩፻፵፪ ።
41. የአድና ፡ ተገለባ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ (በትግርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፣ ያልታተመ ፣ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፣ የዚህን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መግቢያና ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ በመተርጐም ፡ ለረዳው ፡ ለመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ለአቶ ፡ ዓለምሰገድ ፡ ተስፋዬ ፡ ደራሲው ፡ ምስጋናውን ፡ ያቀርባል ።)

ይህ ፡ በጽሑፍ ፡ ያሰፈርነው ፡ ሕግ ፤ አባቶቻችን ፡ ያቋቋሙት ፡ በቃል ፡ የነበረው ፡ ደንብ ፡ ሲሆን ፤ አሁን ፡ ለገጠመን ፡ ችግር ፡ እንዲስማማ ፡ በማሰብ ፡ የተዘጋጀ ፡ ከእውነተኛ ፡ ፍላጐት ፡ የመነጨና ፡ የብዙዎችም ፡ ድጋፍ ፡ የተጨመረበት ፡ ነው ። የተመሠረተውም ፡ ለቅዱሳን ፡ መጻሕፍትና ፡ ለፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ባለን ፡ አክብሮት ፡ ላይ ፡ ነው ።

በስነ ፡ ሥርዓት ፡ ተቀናብሮ ፡ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ ፡ ሕግ ፡ አለመኖሩ ፤ የሕግ ፡ አቋማችንን ፡ በሚያሳዝንና ፡ በሚነቀፍ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ጥሎት ፡ ይገኛል ። የጊዜያችንን ፡ ችግር ፡ ለመቋቋም ፡ እንድንችል ፤ ሕጋችንን ፡ በጽሑፍ ፡ ማስፈር ፡ እንዳለብን ፡ ተረድተነዋል ። ሌላውም ፡ ዓላማችን ፡ ሕጉ ፤ በተለይም ፡ የማስረጃን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፤ የተለያየ ፡ የግል ፡ ትርጉም ፡ እንዳይሰጠውና ፡ ሕጉም ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። . . .” (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።)

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ቃል ፡ የ ጊያነብ ፡ ሁሉ ፡ ቤተክርስቲያንንና ፡ ካህናቶቿ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ተጽዕኖ ፡ በቀላሉ ፡ ይረዳዋል ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ስለ ፡ ካህናቶችዋ ፡ ቀጥለን ፡ ባጭሩ ፡ እንመለከታለን ።

በጽሑፋችን ፡ ውስጥ ፡ በምንነጋገርባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፤ ማለት፡ በሰራዬ ፡ በአክለ ፡ ጉዛይና ፡ በሐማሴን ፤ እንደ ፡ መንደር ፡ ሹማምንት ፡ ሁሉ ፡ ቄሶችም ፡ በሹመታቸው ፡ በሕብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ፤ ዓለማዊ፡ ጥቅምም ፡ ያገኙበታል ።

የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ በሠራዬ ፡ ውስጥ ፡ “---የየመንደሩ ፡ አድባራትና ፡ ካህናቶቻቸው ፡ ከግብር ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ የተለየ ፡ መሬት ፡ አላቸው ።”[42] የመንደር ፡ መሬት ፡ በሚገኝበት ፡ በአንዳንድ ፡ የአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ቀበሌም ፡ ውስጥ ፡ “---ለየመንደሩ ፡ ካህናት ፡ የሚሰጠው ፡ መሬት ፡ ለሕዝቡ ፡ ከሚከፋፈለው ፡ መሬት ፡ የተለየ ፡ ሲሆን ፤ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ከሚደረገውም ፡ ክፍያ ፡ ነፃ ፡ ነው ። ”[43]

ካህናት ፡ እነዚህንና ፡ ሌሎችንም ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅሞች ፡ የሚያገኙት ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ የአገናኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አለን ፡ በማለት ፡ ለሚያበረክቱት ፡ አገልግሎት ፡ ነው ። ክርስትና ፡ ማንሳት ፤ የጋብቻና ፡ የቀብር ፡ ስነ ፡ ስርዓት ፡ ማከናወን ፤ ፍትሐት ፡ መፍታትና ፡ የተዝካር ፡ ጸሎት ፡ ማድረስ ፡ ከተለዩ ፡ ተግባሮቻቸው ፡ ጥቂቶቹ ፡ ናቸው ።[44]

ካህናት ፡ ያለ ፡ አቅማቸውን ፡ ሁሉ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንዲያውሉ ፡ ለማድረግ ፡ ያለው ፡ ፍላጐት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ሕግ ፡ (ራሳቸውንና ፡ ልጆቻቸውን ፡ በሚመለከት ፡ ክርክር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር) ፡ ካህናትን ፡ ጥብቅና ፡ እንዳይቆሙ ፤ ወኪል ፡ እንዳይሆኑና ፡ ጭቅነት ፡ እንዳይሾሙ ፡ ያግዳቸዋል ። “(የነሱን ፡ የሚመስል) ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ስለሌለ ፡ (ካህናት) የክህነት ፡ ሥራቸውን ፡ ብቻ ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ፤ ስለዚህም ፡ በዓለማዊ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ መግባት ፡ አይገባቸውም”[45]--- ፡ የዚህ ፡ እገዳ ፡ ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ግልጥ ፡ ነው ፤

42. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷፩ ፡ ፷፪ ።
43. ከዚያው ።
44. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ “ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እና ፡ ካህናት” ፡ በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
45. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

ካህናት ፡ የተማሩና ፡ ሀሳባቸውንም ፡ በቀላሉ ፡ የመግለጥ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ የኅብረ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ አባል ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ።

ካህናት ፡ የሚያገኙት ፡ ዓለማዊ ፡ ጥቅም ፡ የግል ፡ እንጂ ፡ ተወራራሽ ፤ ተላላፊ ፡ አይደለም ። “(ዝሙት ፡ በመፈጸም ፡ ወይም ፡ ሚስቱን ፡ በመፍታት ፡) ማዕረጉን ፡ ያጣ ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ መንደረተኞች ፡ ይረዱኛል ፡ ብሎ ፡ እርዳታቸውን ፡ መጠበቅ ፡ አይገባውም ፤ ምክንያቱም ፡ (ቅዳሴ ፡ መቀደስ ፡) አይቻለውምና ። ---ቅዳሴ ፡ ለመቀደስ ለሚችል ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ግን ፡ መንደረተኛው ፡ አውጣጥቶ ፡ እርዳታ ፡ ሊያደርግለት ፡ ይገባል ። (የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ማዕረጋቸውን ፡ ያጡ ፡ ቀሳውስት ፡ ቅዳሴ ፡ መቀደስ ፡ ባይቻላቸውም ፡) ከሌሎች ፡ ካህናት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ለመዘመር ፡ ለመጸለይ ፤ ለመቆምና ፡ ፍትሐት ፡ ሲደረግም ፡ ለመፍታት ፡ ስለሚችሉ ፤ ለዚሁ ፡ ‘የከንፈር ፡ ዋጋ’ ፡ ይከፈላቸዋል ።”[46]

ከዚህ ፡ በፊት ፡ በጨረፍታ ፡ ስለጠቀስናቸው ፡ ሽማግሌ ፡ “ዓዲ ፡” ስለሚባሉት ፡ ሽማግሌዎች ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ እንናገራለን ። ቁጥራቸው ፡ ከመንደር ፡ መንደር ፡ የሚለያየው ፡ እነዚህ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በደርግ ፡ በደርግ ፡ በመከፋፈል ፡ “. . . ለኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ የሚበጀውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይወስናሉ ። ክርክሮችንና ፡ ጠቦችን፡ በእርቅና ፡ በግልግል ፡ መልክ ፡ ይቆርጣሉ ፤ (እተራው) ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ቀርበው ፡ ቃላቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ሊገደዱ ፡ አይችሉም ። በየመንደሩና ፡ በየተከራካሪው መካከል ፡ የሚገኘውን ፡ ወሰን ፡ ወስነው ፡ ምልክት ፡ ያስደርጉበታል ።”[47] ባንዳንድ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ፡ የሽማግሌዎች ፡ ደርግ ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፤ ከዘመናትም ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ መሬት ፡ ከነበረው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ተወላጅ ፡ መሆን፡ አለባቸው ።[48] የተባሉት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ በምንመረምራቸው ፡ የመንደር ፡ መሬት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ እንዳላቸው፡ እናመለከታለን ።

## ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡

## ስለመሬት ፡ ስሪታቸው ፤

በደጋው ፡ የኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ እንደሚገኝ ፡ ይነገራል ፤ የግል ፡ ርስት[49] ፡ በቤተ ፡ ሰብ ፡ መሪዎች ፡ እጅ ፡ የሚገኘውን ፡ ጨምሮ ፤ የዘር ፡ ርስት ፡ (“በትክክለኛው ፡ አነጋገር ፡ የእንዳ ፡ ርስት---”) እና ፡ የመንደር ፡ ርስት[50] ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ አመዳደብ ፡ በግልጥ ፡ የተለያየና ፡ ራሱ

---

46. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፡የተጠቀሰው ፡ “ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ካህናት” በሚለው ፡ አርእስት ፡ ሥር ።
47. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፯ ።
48. ኦስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፹፰—፺፬ ። ደራሲው ፡ የተጠቀመባቸውን፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከገጽ ፡ ፹፰—፺፬ ፡ ያሉትን ፡ ጥቅሶች ፡ የተረጐመው ፡ ተስፋ ፡ ጽዮን ፡ መድኃኔ ፤ የሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ነበር ።
49. የግል ፡ መሬት ፡ ስሪት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይበልጥ ፡ ተስፋፍቶ ፡ እንደሚገኝ ፡ ይነገራል ። ደምሴ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፤ አግሬሪያን ፡ ሪፎርም ፡ ኤ ፡ ፕሮፖዛል ፡ ቱ ፡ ኮንቲሪቢውት ፡ ቱ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ዴቨሎፕሜንት ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (፲፱፻፶፮) ፡ ዓ- ም- ያልታተመ ፤ በዩኒቨርሲቲው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት፡ የሚገኝ) ፡ ገጽ ፡ ፵፯ን ፡ ይመለከቷል ።
50. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፵፭ ።

ንም ፡ የቻለ ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ በውርስና ፡ መልሶ ፡ መላልሶ ፡ በመከፋፈል ፣ የዘር ፡ ርስት ፡ የነበረው ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ የግል ፡ ርስት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[51]

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ "የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን" ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት፡ ስለሆነ ፣ ስለ ፡ ግል ፡ ርስት ፡ የምናደርገው ፡ ምርምር ፡ አይኖርም ።

ከዚህም ፡ ቀደም ፡ እንደተገለጠው ፤ "---ከኢትዮጵያ ፡ በስተሰሜናዊ ፡ ምዕራብ፡ ክፍል ፣ ማለትም ፡ ሐማሴን ፣ ሰራዬንና ፡ አክለ ፡ ጉዛይን ፡ ከኤርትራ ፤ የትግሬን ፡ የቤጌ ምድርንና ፡ የጐጃምን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ በሙሉ ፤ የላስታንና ፡ የዋግ ፡ አውራጃዎ ችን ፡ ከወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በሚያጠቃልለው ፡ ሀገር ፡ ውስጥ፣ የሚገኘው ፡ የመ ሬት ፡ ስሪት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የጋርዮሽ ፡ ወይም ፡ የኅብረት ፡ ስሪት ፡ (ኮሙናል ፡ ቴን የር) ነው ።"[52] "የኅብረት ፡ ስሪት" (ኮሙናል ፡ ቴንየር) ሲባልም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ባለመብትነት ፡ የግል ፡ አለመሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ ሲሆን ፣ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ መሠረታዊ ፡ ልዩነት ፡ ቢኖርም ፡ የዘርንና ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪቶችን ፡ ያጠቃል ላል ።

በዘርና ፡ በመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ስር ፡ ያሉት ፡ መብቶች ፡ የተለያዩ ፡ ስለሆኑ፣ ለየብቻ ፡ እንመረምራቸዋለን ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮችን ፡ መጥ ቀስ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ቢገኝበትም ፤ በሰ ራዬ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ ተስፋፍቶ ፡ የሚታየው ፡ የዘር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ነው ። እንዲ ሁም ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ቢገኝም ፡ በአክለ ፡ ጉዛይና ፡ በሐማሴን ፡ ውስጥ፡ በብዛት ፡ ተስፋፍቶ ፡ የሚታየው ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ነው[53] ። ሁለተኛም ፤ የዘ ርንና ፡ የመንደር ፡ ርስትን ፡ የሚያዋህደው ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳብ ፡ መዘንጋት ፡ የለበ ትም ፤ ሁለቱም ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ዓይነቶች ፡ መታየት ፡ ያለባቸው ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅ ላይ ፡ ግዛት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፣ በተለይም ፡ ተስፋፍቶ ፡ በሚታየው ፡ "የመሬት ፡ ችግር ፡" አንጻር ፡ ነው[54] ። ይህ ፡ የመሬት ፡ ችግር ፡ ነው ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገ ኙትን ፡ የመሬት ፡ ስሪቶች ፡ በሚገባ ፡ ለመረዳት ፡ የሚያስችለው።

(ሀ) <u>ስለዘር ፡ ርስት ፤</u>

(፩) <u>አመጣጡ ፤</u>

ጉዳዩን ፡ የመረመሩት ፡ ሊቃውንት ፡ ሁሉ ፣ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የዘር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ጥንት ፡ በይዞታ ፡ ብቻ ፡ ከተገኘ ፡ የግል ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ እን ደመነጨ ፡ ይናገራሉ ።

ስለዚህም ፡ "--- (የዘር ፡) ርስት መሠረታዊ ፡ ሀሳብ ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ ታሪክን ፡ በመመልከት ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፣ ይህም ፡ ስሪት ፡ ጥንት ፡ አንድ ፡ ሰው ፣ ወይም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፣ ሰው ፡ ያልሰፈረበትን ፡ መሬት ፡ በመያዝ ፡ ከመሠረተውና ፡ ከጊዜ ፡ በኋ ላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ በመያዝ ፡ ከተለዋወጠው ፣ በግልጽ ፡ የተወሰነ ፡ ትርጉም ፡ ከነበረው ፡ የግል ፡ ባለቤትነት ፡ እንደመጣ ፡ ታሪክ ፡ ያስረዳናል ። ጥንት ፡ መሬቱን ፡

---

51. ከዚያው ።
52. ሎውረንስ ፡ ኤንድ ፡ ማን ፣ "ኮሙናል ፡ ላንድ ፡ ቲኒየር ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡" <u>ኢትዮጵያ ፡ ኦብዘርቨር ፤</u> ፱ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ቍጥር ፡ ፩ ፤ ገጽ ፡ ፻፶፲፬—፻፶፲፭ ።
53. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፰ ።
54. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፮ ።

የያዘው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባሎች ፡ በተፈጥሮ ፡ ሲባዙ ፣ የመሬቱ ፡ ባለቤትነት ፡ ከግል ፡ ወደጋርዮሽነት ፡ ተለወጠ ።"[55]

ይህ ፡ ለውጥ ፡ የመጣበትን ፡ ሁኔታ ፡ ሲኖር ፡ አስቲኒ ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይገልጡታል ። "ያንድ ዘር ፡ ወይም ፡ ጐሣ ፡ መሥራች ፡ አባት ፡ በአንድ ፡ ምክንያት ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ መሬት ፡ ይይዛል ። ልጆቹም ፡ በወራሽነት ፡ መብታቸው ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ሲመስላቸው ፡ ያን ፡ መሬት ፡ ቆራርጠው ፡ ይከፋፈሉታል ። በመጀመሪያ ፡ አንድ ፡ የነበረው ፡ መሬት ፡ ከመሥራች ፡ አባቱ ፡ ለተወለዱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ይከፋፈላል ። ለመሥራች ፡ አባቱ ፡ የመጀመሪያም ፡ ተወላጆች ፡ ተከፋፍሎ ፡ የነበረው ፡ መሬት ፡ በመከታተል ፡ (እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ እየተቆራረጠ ፡) ለተወላጆች ፡ ይከፋፈላል[56] ።" እንደዚህም ፡ እያለ ፡ ጥንት ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ የነበረው ፡ መሬት ፡ በተወላጆቹ ፡ መካከል ፡ ተቆራርጦ ፡ ይከፋፈላል ፤ ሲሉ ፡ አስቲኒ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ይደመድማሉ ።

በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፡ የሚገኙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ታላቁ ፡ አቋም ፡ የሆነው ፡ እንዳ ፡ ("---በውስጡ ፡ የሚገኙት ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ ትልልቅ ፡ የግል ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ሲሆኑ ፣ እንዳውም ፡ በዚያው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የሚታወቅ ፡ ነው ፡ ---") እንደ ፡ አንድ ፡ ቀበሌ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ፡ ተብሏል ። "(በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ) ፡ ዋነኛ ፡ የሆነው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ዓይነት ፣ ማለትም ፡ ፍጹም ፡ የሆነው ፡ (የቤተ ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ ርስት) --- ከእንዳው ፡ ጋር ፡ የተማሠረ ፡ በመሆኑ ፣ እንዳው ፡ (የቤተ ፡ ሰብ ፡ ስም ፡ ቢሆንም) ባንድ ፡ ወገን ፡ የተወሰነ ፡ ቀበሌ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። የእንዳ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ በግል ፡ ባለሀብትነቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስተዳድረው ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ የግለኛ ፡ መብት ፡ ተገኘ ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ እንዳው ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖረው ፡ ጥንት ፡ በይዞታ ፡ ከተገኘው ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ ነው ። ይህም ፡ አስተሳሰብ ፡ የመሬት፡ ክርክር ፡ በተነሣ ፡ ቁጥር ፡ በግልጥ ፡ ከመታየቱም ፡ በቀር ፡ እንዳውን ፡ ከሚያስተሳስሩት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ነው ።"[57]

እንዳ ፡ ሲባል ፡ "ተለዋዋጭ" የሆነ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ይገነዘቧል ። "አንድ እንዳ ፡ ---በግልጽ ፡ ተለይቶ ፡ የታወቀ ፡ ቢሆንም ፣ ብዙ ፡ ክፍልፋዮች ፡ ስላሉት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲለዋወጥ ፡ በሱና ፡ በውስጡም ፡ ባሉት ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ማየት ፡ ያዳግታል ። ምክንያቱም ፡ በእንዳው ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት፡ ቤተሰቦች ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹ ፡ እጅግ ፡ ትላልቅ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። በሦስት ፡ ወይም ፡ በአራት ፡ ትውልድ ፡ የሚለያዩ ፡ ተወላጆች ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በመባባል ፡ ተዋህደው ፡ በመገኘት ፡ ከእንዳው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ ፣ ወደፊትም ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ እንዳ ፡ ለማቋቋም ፡

:

---

55. ከዚያው ፣ ገጽ ፡ ፳ ።
56. አስቲኒ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፹፰ ፡ እና ፡ በሚከተሉት ፡ ገጾች ።
57. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፴፮ ። ከአምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ ከተጠቀሰው ፣ ከገጽ ፡ ፫ ጋር ፡ ያወዳድሯል ። በስህተት ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እየተባለ ፡ በሚተረጐመው ፡ እንዳ ፡ በሚባለው ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ በመቶ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ሊገኙበት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ አጥብቆ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። ከእንዳ ፡ በለወይ ፡ በለዛ ፡ (ሐማሴን) ፤ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ እንዳ ፡ ጕመራ ፡ (ሰራዬ) ፤ መልስ ፡ ሰጭ ፡ (ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ- ም- የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፶፯/፰ ፡ (ያልታተመ) ፤ ዘጠኝ ፡ ትውልድ ፡ ወይም ፡ ከ፭፻፶ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ይኖር ፡ ከነበረ ፡ ሰው ፡ ተወላጅ ፡ ነኝ ፡ በሚል ፡ ክርክር ተወላጆች ፡ ከሚካፈሉት ፡ መሬት ፡ ድርሻዬ ፡ ይሰጠኝ ፡ የሚል ፡ ክስ ፡ ከቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

የሚችል ፡ ክፍል ፡ ሆነው ፡ ይኖራሉ ።"[58] አንድ ፡ እንዳ ፡ እጅግ ፡ ከበዙ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ በብዙ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፋፈልና ፡ እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ በየ ራሱ ፡ ስም ፡ መጠራት ፡ ይጀምራል ።[59]

(፪) <u>ስለቃላት ፡ አገባብ ፤</u>

በምንመረምራቸው ፣ የዘር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ በእርሻ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ መብቶችን ፡ ለማመልከት ፡ ሕዝቡ ፡ የሚጠቀምባቸውን ቃላት ፡ አገባብና ፡ ትርጉም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ከአንባቢው ፡ ማስተዋወቅ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው።

በጣም ፡ የሚዘወተረው ፡ ቃል ፡ "ርስቲ" የሚለው ፡ ነው ። "ይህም ፡ ቃል ፡ ረስተ ፡ ከሚለው ፡ ከግዕዙ ፡ ቃል ፡ የመጣ ፡ ነው ። በብዙ ፡ ስሜትና ፡ ትርጉም ፡ ስለሚ ገባ ፡ መሬት ፡ ገብቶ ፡ መያዝን ፣ (የመሬትን ፡ ይዞታንና ፡ ባለቤትነትን ፡) ያመለክታል።"[60] በጠቅላላ ፡ አነጋገርም ፡ ሲገባ ፡ "---ከግል ፡ ባለቤትነት ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ባለቤትነት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነት"[61] ሁሉ ፡ ያመለክታል ። ሚስተር ፡ ናዴል ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ "ርስቲ" ፡ የሚለው ፡ ቃል "የዘር፡ወይም፡የቤተ፡ሰብ ፡ ርስትን ፡" የሚያመለክት ፡ ተደርጐ ፡ የሚገባ ፡ ሲያስመስሉት ፣ አቶ ፡ አምባዬ ፡ የተባሉ፡ ደራሲ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ትክክል ፡ አለመሆኑን ፡ ይገልጣሉ። "ቃሉ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ያለን፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ የሚያመለክት ፡ አጠቃላይ ፡ ቃል ፡ ነው ። የመብቱ ፡ ዓይነት ፡ ሊለይ ፡ ሲፈልግ ፣ ይህ ፡ ቃል ፡ በቅጽል ፡ መልክ ፡ ይገባል ።"[62]

ስለዚህ ፡ <u>ርስቲ ፡ ዴሳ ፡</u> (የመንደር ፡ ርስት) ፡ <u>ከርስቲ ፡ ጽልሚ ፡</u> (የግላዊ ፡ ርስት) <u>እና ፡ ከርስቲ ፡ ጉልቲ ፡</u> (ከርስት ፡ ጉልት) ይለያል ። እንደ ፡ አቶ ፡ አምባዬም ፡ አስተ ሳሰብ ፡ ርስቲ ፡ የሚያመለክተው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ማንኛውንም ፡ መብት ፡ ነው[63] ።

በሰራዬ ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፣ ርስቲ ፡ ማለት ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ የተወረሰ ፡ ወይም ፡ ለደም ፡ ዋጋ ፡ የተከፈለ ፡ ወይም ፡ በግገር ፡ የተገኘ--- ወይም ፡ ጫካን ፡ መንጥሮ ፡ በማ ልማት ፡ የተያዘ ፡ <u>መሬት</u>[64] ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

በንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ የጠቀስናቸው ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ይዘው ፡ የሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ርስተኛ ፡ (በነጠላ) ወይም ፡ ርስትኛታት (በብዙ) ተብለው ፡ ይጠራሉ ። የዘር ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበ

58. ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፫ ።

59. ከዚያው ።

60. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፳ ። ከሚቀጥለው ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ፤ "ርስቲ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በየቀበሌው ፡ ከሚገኙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህሎች ፡ ጋር ፡ የተወሳ ሰበ ፡ በመሆኑ ፣ አንድ ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ የሚችል ፡ ቃል ፡ አይደለም ። ምናልባትም ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ የቅርብ ፡ ተመሳሳዩ ፡ ከጭሰኝነት ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጋር ፡ የሚቃረነው ፡ አሎድ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ።"

61. ዱንካንሰን ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፬ ፣ ማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፭ ። ናዴል ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፯ ።

62. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፳ ።

63. ከላይ ፡ በጠቀስነው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ አቶ ፡ አምባዬ ፡ "ንብረት" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ "መብት፡" በሚል ፡ ስሜት ፡ እንዳገቡት ፡ ይገነዘቧል ።

64. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ "<u>የርስቲ</u> ፡ ደንቦች" ፡ በሚል፡ አርእስት ፡ ሥር ።

ሌ ፡ ውስጥ ፡ ርስተኛ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻውን ፡ የመ ቀበል ፡ መብት ፡ ያለውና ፡ መሬት ፡ መያዝም ፡ የሚያስከትላቸውን ፡ መብቶችና ፡ ጥቅ ሞች ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችል ፡ ነው ። የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ርስተኛ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ተወላጅነቱ ፡ ከጥንት ፡ የባለርስቶች ፡ ወገን ፡ የሆነ፡ ነው ።

(፫) <u>በእርሻ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ስላሉ ፡ ግላዊ ፡ መብቶች ።</u>

የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ባሳየው ፡ ለውጥ ፡ ከሁለት ፡ መልኮች አንዱን ፡ እንደሚይዝ ፡ ታውቋል ። "የጋራ ፡ ባለቤትነት ፡ ተጠብቆ ፡ ይቆይና ፡ እያን ዳንዱ ፡ ተወላጅ ፡ የባለአላባ ፡ መብቱን ፡ የሚያስከብርበት ፡ መንገድ ፡ ይፈጠራል ፤ ወይም ፡ ርስቱ ፡ በውርስና ፡ በተወላጆች ፡ መካከል ፡ በሚደረግ ፡ መከፋፈል ፡ ጥንት ፡ የነ በረውን ፡ የግል ፡ ባለቤትነት ፡ መልክ ፡ መልሶ ፡ ይይዛል ።"[65] የመጀመሪያው ፡ እንዲሁ ፡ "ርስቲ" ተብሎ ፡ ሲጠራ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ "ጽልሚ" ተብሎ ፡ ይጠራል ።

በአንዳንድ ፡ የርስቲ ፡ ስሪት ፡ (ከጽልሚ ፡ ጋር ፡ በተነፃፃሪነት ፡ ሲገባ) በሚገኝ ባቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ ባልና ፡ ሚስትና ፡ ያላገቡ ፡ ልጆቻቸው ፡ የሚገኙ በት ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አንድ ፡ ማሳ ፡ ያርሳል[66] ። የማሳውም ፡ ስፋት ፡ የሚወስ ነው ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ፍላጎት ፡ ነው[67] ። ማሳውም ፡ "ግራት" ማለትም ፡ እርሻ ፡ ወይም ፡ የእርሻ ፡ ቦታ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል[68] ። የሟች ፡ ተወላጆች ፡ ድርሻ ፡ ለጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ ተመላሽ ፡ ይሆንና ፡ አዲስ ፡ ለተጋቡ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይከፋፈላል ። እዚህ ፡ ላይ፡ መታወስ ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ማሳ ፡ በውርስ ፡ ሊተላለፍ ፡ ባይችልም ፡ እንኳ ፡ ከጎብረተ ፡ ሰብኡ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡ ድርሻን ፡ የማግኘቱ ፡ መብት ፡ በውርስ ፡ ሊተ ላለፍ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ነው[69] ።

ማሳ ፡ ሊያገኙ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ አግብተው ፡ ትዳር ፡ የያዙ ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። በአጠቃላይ ፡ አነጋገር ፡ ሴቶችና ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ በተላ ለፈ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ የላቸውም[70] ።

ማንኛውም ፡ ድርሻውን ፡ ማሳ ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ሊያርሰው ፡ ሊሸጠው[71] ፡ ወይንም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ለሌላ ፡ ለውጭ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ሊሰጠው ፡ የሚችለው ፡ የእንዳው ፡ አባሎች ፡ ወይም ፡ የመንደሩ ፡ ሰዎች ፡ ማሳውን ፡ ለመግዛት ፡ ወይንም ፡ ለመውሰድ ፡ ፈቃደኛ ፡ ሳይሆኑ ፡ ሲቀሩ ፡ ነው ።

ጽልሚ[72] ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቤተ፡ ሰብ ፡ የአንድ ፡ የተወሰነና ፡ የታወቀ ፡ ማሳ፡ ባለቤት ፡ ነው ። በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡

65. ናዴል ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷ ።
66. የዘር ፡ ርስት ፡ ሲባል ፡ የሚታረስ ፡ መሬት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። "(የአንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡) <u>ርስቲ</u> ፡ ስፋት፡ የሚታወቀው ፡ የሚታረሰውን ፡ መሬት ፤ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ ጫካንና፡ የውሃ ፡ ኩሬንና ፡ የቤት ፡ መሥ ሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ ስፋት ፡ በመደመር ፡ ነው ።" ፡ አስቲኒ ፤ ከላይ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀ ሰው ፤ ገጽ ፡ ፻፰ ።
67. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷ ።
68. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፷ ።
69. ከዚያው ።
70. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፰ ።
71. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፷ ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ እናትትበታለን ።
72. አቶ ፡ አምባዬ፡ ርስቲ፡ ጽልሚን ፡ "ፍጹም ፡" የግል ፡ ንብረት፡ በማለት ፡ ገልጸውታል ። አምባዬ ፡ ዘካር ያስ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷ ።

ከአባት ፡ ወገን ፡ በመጣ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ርስትም ፡ በአገቡ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የሚከፋፈለው ፡ በአ ባትየው ፡ ነው ። ባለመብቶች ፡ ብዙ ፡ በሚሆኑበትም ፡ ጊዜ ፡ ርስቱ ፡ የሚከፋፈለው ፡ አባትየው ፡ በመረጣቸው ፡[73] ሽማግሎች ፡ አማካይነት ፡ ነው ።

በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻውን ፡ የሚያገኘው ፡ በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ "ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ በመሆን ፡ የኢ ኮኖሚ ፡ ነፃነት" በሚያገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።[74] እንዲያውም ፡ ሙሽራው ፡ ሊያገኝ ፡ የሚገባው ፡ አንድ ፡ ማሳ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ አባቱ ፡ የሠራውን ፡ አንድ ፡ ቤት ፤ የእርሻ ፡ መሣሪያዎችን ፤ ከማግባቱ ፡ በፊት ፡ በእርሻው ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ካስገኘው ፡ ሰብል፡ በተወሰነ ፡ ልክ ፡ ተሰፍሮ ፤ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ እንስሳትንና ፡ ከአባቱ ፡ የቤት ፡ ዕቃ ፡ ዎች ፡ አንድ ፡ ሦስተኛውን ፡ ወይንም ፡ አንድ ፡ አራተኛውን ፡ ጭምር ፡ ነው ።[75]

ሴቶችና ፡ (ጓል) ተወላጆቻቸው ፡ (ደቂ ፡ ጓል) ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ በመጣ ፡ ርስትም፡ ሆነ ፡ ጽልሚ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ድርሻ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ተነፈጉ ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ በአእምሮአችን ፡ ይጉላላ ፡ ይሆናል ። ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ የተባሉ ፡ ጸሐፊ ፡ መልስ ፡ ይሆናል ፡ ያሉትን ፡ አንድ ፡ አስተያየት ፡ አቅርበዋል ። "በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚፈ ጸመው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ (ቃል ፡ ኪዳን) መሠረት ፡ የሴቷ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ለወንዱ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ የሚሰጠው ፡ ጥሎሽ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቿ ፡ ከሚኖርባቸው ፡ ግዴታ ፡ ቤተሰ ቦቿን ፡ ነፃ ፡ ያደርጋቸዋል ። በሁለቱ ፡ አባቶች ፡ መስማማትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ አለመ ስማማት ፤ ወጣት ፡ ሠርገኞቹ ፡ ነፃ ፡ ሆነው ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ ቢሰጣቸውና ፡ የወንድየው አባት ፡ በሕይወት ፡ እስካለም ፡ ድረስ ፡ በጥሎሹ ፡ ላይ ፡ የይዞታ ፡ መብት ፡ ቢሰጣቸ ው ፤ ከግዴታ ፡ ነፃ ፡ መውጣታቸው ፡ እንደጸና ፡ የሚቆይ ፡ ነው ።"[76] በተጨማሪም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻ ፡ እውነተኛ ፡ ትርጉሙ ፤ "ጥሎሽ ፡ ጥሎ ፡ ቤተ ፡ ዘመድን ፡ ነፃ ፡ ማውጣት" መሆኑን ፡ ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ ይናገራሉ ።

ይህም ፡ በአንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚታየው ፡ ሴት ፡ ልጆችንና ፡ ተወላ ጆቻቸውን ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ የመጣ ፡ እርስትን ፡ አለማካፈል ፡ "ለወንዶች ፡ ልጆች ፡ ውርሳቸውን ፤ ለሴቶች ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ጥሎሻቸውን ፡"[77] በሚለው ፡ ምሳሌያዊ ፡ አነጋ ገር ፡ ይገለጻል ።

ይህ ፡ እገዳ ፡ በሌለበት ፡ ቀበሌ ፡ ደግሞ ፤ የሴቶች ፡ ልጆችና ፡ የተወላጆቻቸው ፡ መብቶች ፡ አንዳንድ ፡ ወሰን ፡ ይደረግባቸዋል ። ይኸውም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የሆ ነውን ፡ መሬት ፡ ሊሸጡ ፡ ወይንም ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ርስትነት ፡ ሊለውጡት ፡ አይች ሉም ። በወንዶች ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ተመሳሳይ ፡ የመብት ፡ ወሰን ፡ ተጥሎ ፡ አይገ ኝም ።[78] ሆኖም ፤ (እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የዘመን ፡ አቆጣጠር) ከ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ርስቱን ፡ እንዳይሸጥ ፡ ታግ ዷል ።[79] "ርስትን ፡ መሸጥ ፡ አይቻልም ። ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አንድ ፡

---

73. ኦስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፹፫—፺፬ ።
74. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፳፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ በ"ኢኮኖሚ ፡ ነፃነት" ፡ ስር።
75. ከዚያው ።
76. ዱንካንሰን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፺፬ ።
77. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፯ ።
78. የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
79. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፳፭ ፡ ፳፪ ።



001624

ሰው ፡ ድኅነት ፡ ቢሜነው ፤ መሬቱን ፡ ሸጦ ፡ ተወላጆቹን ፡ ርስቲ ፡ እንዳያገኙ ፡ ማድረግ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ አይደለምና ። በሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ማንኛውም ፡ የተራበ ፡ ወይም ፡ የተጠማ ፡ ሰው ፡ እህል ፡ እና ፡ ውሀ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ከሱ ፡ ላይ ፡ ርስት ፡ መግዛት ፡ የለበትም ። ምክንያቱም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ልጆቹንና ፡ ሚስቱን ፡ ሊረሳ ፡ ብዙ ፡ ስሕተትም ፡ ሊሠራ ፡ ይችላልና ፤"[80] ሲል ፡ ሕጉ ፡ ይደነግጋል ።

ይህ ፡ ርስቲንም ፡ ሆነ ፡ ጽልሚን ፡ የመሸጥ ፡ ጉዳይ ፡ ሌላ ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ጉዳይን ፡ ያስታውሳል ። ይኸውም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ የሆነን ፡ ርስት ፡ ይዞታ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእጅ ፡ በማድረግና ፡ ግብሩንም ፡ በመክፈል ፡ ባለቤትነቱን ፡ በይርጋ ፡ የማግኘት ጉዳይ ፡ ነው ።

በሰራዬ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ "ባዕድ" የሆነ ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ ማሳ ፡ ሊያርስ ፡ የሚችለው ፡ በባለርስቶቹ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ "በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ለሚደርሱ ፡ የነፍስ ፡ ግድያዎች ፡ ዘረፋዎች ፤ ወይም ፡ ቅሚያዎች ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖር ፡ ተጠያቂዎቹ ፡ ባለርስቶቹ ፡ እንጂ ፡ ባዕዳኑ ፡ ስላልሆኑ ፡ "[81] ነው ። አስፈላጊው ፡ ፈቃድ ፡ ከተገኘ ፤ ባዕድ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ "ለም ፡ መሬት"፤ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ "ጠፍ ፡ መሬት" የማረስ ፡ መብት ፡ ያገኛል ። (ሕጉ ፡ እዚህ ፡ ላይ፡ በግልጥ፡ ባይናገርም) በአምስተኛው ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ መሬቱን ፡ ይዞ ፡ ለማቆየት ፡ ሲፈልግ ፡ እንደገና ፡ አዲስ ፡ ፈቃድ ፡ መጠየቅና ፡ ማግኘት ፡ ያሻዋል ።

ባዕዳኑ ፡ "ምንም ፡ እንኳን ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ እዚያው ፡ ቢኖሩም" በሚያርሱት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ ሊያገኙበት ፡ አይችሉም ።[82] እንዲያውም ፡ በባለርስቶቹ ፡ ፈቃድ ፡ ያገኙት ፡ ማሳ ፡ ከመንደሩ ፡ ወጭ ፡ (ከበረካ) የሚገኝ ፡ በባለ ፡ ርስቶቹም ፡ ታርሶ ፡ የማያውቅ ፡ ሲሆን ፤ ባዕዳኑ ፡ ዋስትና ፡ በሌለው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ። ይህን ፡ የያዙትን ፡ ማሳ ፡ ባለርስቶቹ ፡ እራሳቸው ፡ ለማልማት ፡ በሚወስኑበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለቀው ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ይገደዳሉ ።[83]

በርግጥ ፡ አንድ ፡ ባዕድ ፡ አንድን ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ ለመግዛትና ፡ ባለርስትም፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። (ርስቱም ፡ ምድሪ ፡ ወርቂ ፤ በገንዘብ ፡ የተገዛ ፤ ተብሎ ፡ ይጠራለታል ።) ሆኖም ፡ ሺያጩ ፡ የሚጸናው ፡ በሀገሩ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ መፈጸም ፡ የሚገባቸው ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ ሁሉ ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ፎርማሊቴዎች ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ እንዳይሸጥ ፡ ለማድረግና ፡ ተስፋ ፡ ለማስቆረጥ ፡ የታቀዱ ፡ ብዙ ፡ ጣጣ ፡ ያለባቸው ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ በሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ ተመልክተው ፡ ይገኛሉ ። ሲኞር ፡ አስቲኒም ፡ በመጽሐፋቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደሚከተለው ፡ ባጭሩ ፡ ይገልጿቸዋል ፦

"አንድ (የቤተ ፡ ሰብ ፡ የሆነ) ርስት ፡ ሺያጭ ሊጸና ፡ የሚችለው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

80. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ ፳፩ ።
81. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ "የውጭ ፡ ሰዎች" ፡ "በሀገር ፡ ተቀማጭ ፡ ስለመሆንና ፡ ሀገርን ፡ ስለመልቀቅ" ፡ በሚል ፡ ስር ።
82. ከዚያው ።
83. ከዚያው ።

፭/ ሽያጩ ፡ በገዢና ፡ በሻጭ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ በተመረጠ ፡ ዳኛ ፡ (የመንደር ፡ ዳኛ) ፊት ፡ ተከናውኖ ፡ እንደሆነ ፤

፮/ ሻጩ ፡ የሚከተሉትን ፡ ነገሮች ፡ በማረጋገጥ ፡ ዋስ ፡ የሚሆነው ፡ (አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ) ሰው ፡ ለማቅረብ ፡ ይችል ፡ እንደሆነ ፤

ሀ/ ሻጩ ፡ ለሚሸጠው ፡ (ርስት ፡ እርግጠኛው) ባለቤት ፡ መሆኑን ፥

ለ/ በቅድሚያ ፡ ለመግዛት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ተጠይቆ ፡ ሊገዛ ፡ አለመፍቀዱንና ፥

ሐ/ የሺያጩ ፡ ውል ፡ ወደፊት ፡ የፈረሰ ፡ እንደሆነ ፡ ዋጋው ፡ ተመላሽ ፡ መሆኑን ፤

፯/ ገዢው ፡ ለሻጩ ፡ በያመቱ ፡ የሚያበረክተው ፡ የምግብ ፡ ወይም ፡ የጥራጥሬ ልክ ፡ ተገልጾ ፡ እንደሆነ ፤

፰/ ዋሱ ፡ ዋስ ፡ በመሆኑ ፡ በየዓመቱ ፡ የሚከፈለው ፡ የጥራጥሬ ፡ መጠን ፡ ተገልጾ ፡ እንደሆነ ፤

፱/ ሁለቱ ወገኖች የሺያጩን ፡ ውል ፡ ሲዋዋሉ ፡ ከዳኛውና ፡ ከዋሱ ፡ ሌላ ፡ ከአምስት ፡ ያላነሱ ፡ ምስክሮች ፡ ተገኝተው ፡ እንደሆነ ፤"[84]

ሕፃናት ፡ ምስክር ፡ ለመሆን ፡ ቢችሉም ፤ ሊመሰክሩ ፡ የሚችሉበት ፡ "ትልቅ ፡ ሰው ፡ ሲሆኑ" ብቻ ፡ ነው ።[85] በአንዳንድ ፡ ሥፍራዎች ፡ ውስጥ ፡ ለመሬት ፡ ሺያጭ ፡ ውል ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑት ፡ ቄስ ፤ እስላምና ፡ ባለእጅ ፡ ናቸው ። የመጨረሻዎቹ ፡ ሁለቱ ፡ በምስክርነት ፡ መገኘት ፡ "በርስት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጥቅም ፡ የሌላቸውን ፤ ሊቃወሙት ፡ የማይቻል ፡ የእውነተኞች ፡ ሰዎችን ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ . . ."[86] ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የቤት ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ የሆነን ፡ ርስት ፡ የመሸጥ ፡ ጉዳይ ፡ ተራ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ገዢው ፡ ለሻጩ ፡ በያመቱ ፡ ሊያከብረው ፡ የሚገባው ፡ ቃል ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ይገነዘቧል ። ይህ ፡ ልማድ ፡ ከዘመናት ፡ በፊት ፡ ሻጩ ፡ የመሬቱ ፡ ባለቤት ፡ እንደነበረ ፡ ሲያስታውስ ፡ ይኖራል ።

ለሻጩ ፡ ዘመዶችም ፡ የተደረጉትን ፡ ልዩ ፡ የመከላከያ ፡ ዘዴዎች ፡ እዚህ ፡ ላይ፡ መግለጽ ፡ ይገባል ። አንድ ፡ የሻጭ ፡ ወንድም ፡ ከሌላ ፡ ሀገር ፡ በመኖሩ ፡ ሽያጩን ፡ ሳያውቅ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ "በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የራሱን ፡ ርስት" ፡ ከገዢው ፡ ላይ ፡ ሊያስመልስ ፡ ይችላል ።[87] ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ "ወንድም ፡ ወይም ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ ፡ ርስቱ ፡ ሲሸጥ ፤ (በገዢው) ሲታረስና ፡ ሲለማ ፡ እያየ ፡ ሳይቃወም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የማስመለስ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።"[88]

---

84. አስቴኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፻፰ ፡ ጀምሮ ።

85. ከዚያው ።

86. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፬ ።

87. የሠራዊ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "የርስቲ ፡ ደንቦች"፡ በሚለው ፡ ስር ። ይህም ፤ "ርስት ፡ በሺህ ፡ ዓመቱ ፡ ለባለቤቱ፡" ከሚለው ፡ የአማራ ፡ ምሳሌያዊ፡ አነጋገር ፡ በግልጽ ፡ ይታያል ። "አንድ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡" ሲባልም ፡ "እስከ ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ" ለማለት ፡ ነው ።

88. ከዚያው ።

አንድ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ የመሬቱን ፡ ይዞታ ፡ ጥንት ፡ በግዢ ፡ መልክ ፡ በእጁ ፡ ካገባ ፡ በኋላ ፡ በስሙ ፡ በመገበር ፡ በይርጋ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የሆነውን[89] ፡ መሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ፡ ቢባልም ፤ አንድ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ በስሙ ፡ ግብር ፡ በመክፈል ፡ የዘመዶቹ ፡ ድርሻ ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ሊይዝና ፡ ባለ ቤት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ይህም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደ ተገለጸው ፡ የአንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የሚይዘው ፡ "ቤተ ፡ ሰቡ" ፡ ባለው ፡ መብትና ፡ የዚህም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይዞታ ፡ ከሌለው ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ፡አባል ፡ የሚበልጥ ፡ መብት ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ የለውም ፤ ሊኖረውም ፡ አይችልም ።

ሆኖም ፡ በየሥፍራው ፡ የሚገኘውን ፡ የልማድ ፡ ልዩነት ፡ መግለጽ ፡ ይገባል ። በሎጐ ፡ ጭዋ ፤ ከመንደር ፡ ውስጥ ፡ አለመኖር ፡ በርስት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መብትን ፡ እስከ ማሳጣት ፡ ያደርሳል ።[90] ይህንንም ፡ በሚቀጥለው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ እንመለከተዋለን ።

ጽልሚና ፡[91] ርስቲ ፡[92] በሚገኙባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አስሃባ ፡ የተባለ ፡ ስርዓት ፡ ሲሠራበት ፡ ይታያል ። አንዱ ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማው ጥቅምን ፡ ማደላደል ፡ ሲሆን ፤ በዚህም ፡ መሠረት ፡ ማሣዎች ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ይከፋፈላሉ ። ይህም ፡ የሚሆነው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከሌሎች ፡ የሚበልጥ ፡ ማሳ ፡ ይዘው ፡ ሲገኙ ፡ (ለምሳሌ ፡ በሎጐ ፡ ጭዋ) ወይንም ፡ "ለአዲስ" ጠያቂ ፤ ድርሻ ፡ ለመስጠት ፡ ከሚገኙት ፡ ማሳዎች ፡ ውስጥ ፡ ማዋጣት ፡ ሲያ ስፈልግ ፡ (ለምሳሌ ፡ በሰራዬ ) ነው ።

## (ለ) ስለመንደር ፡ ርስት ፤

### ፩/ አመጣጡ ፤

"የመንደር ፡ የርስት ፡ ባለቤትነት" እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ፡ የሚገኘው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፤ ርስቲ ፡ ከሚባለው ፡ ከዘር ፡ ርስት ፡ ስሪት ፡ የመጣ ፡ ለመሆኑ ፡ ደራሲዎች ፡ ተመሳሳይ ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣሉ ።[93] ይህም ፡ አስተያየት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስትን ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ርስት ፡ መለወጥ ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ በሚቀ በሉት ፡ በሎጐ ፡ ጭዋና ፡[94] በሰራዬ ፡[95] የልማድ ፡ ሕጐች ፡ የተደገፈ ፡ ነው ።

---

89. ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ርዕስ ፡ ነው ። ግርማ ፡ ሥላሴ ፡ አርአያ ፤ ዩሱካፕሽን ፡ አፍ ፡ ፋሚሊ ፡ ላንድ ፡ አንደር ፡ ኢትዮፕያን ፡ ሎው ፤ (፲፱፻፷፰ ፡ ዓ. ም. ያልታተመ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ መጻ ሕፍት ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፤ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።)
90. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
91. ከዚያው ።
92. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "የርስቲ ፡ ደንቦች ፡" በሚለው ፡ ስር ።
93. ኦስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ ጀምሮ ። አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ የተጠቀሰውን ፤ ገጽ ፡ ፲፫ ፡ ይመለከቷል ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የስሪት ፡ ለውጥ ፡ በትግሬ ፡ ውስጥም ፡ ታይቷል ። ዘገየ ፡ አስፋውና ፡ ጠዓመ፡ በየነ ፤ ሪፖርት ፡ ኦን ፡ ትግሬ ፡ ፕሮ ቪንስ ፡ (፲፱፻፷፯ ፡ ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ፡ ገጽ ፡ ፫ - ፬ ።
94. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
95. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "የርስቲ ፡ ደንቦች ፡" በሚለው ፡ ሥር ። ይህ ፡ የመንደር ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ በሐማሴንና ፡ ሰራዬ ፡ "ዴሳ" ፡ ተብሎ ፡ ሲጠራ፤ በአካለ ፡ ጉዛይ ፡ ደግሞ ፡ "ሸኸና" ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ጥንት ፡ ባለርስት ፡ ከነበረ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በመወ ለዳቸው ፡ ድርሻ ፡ ማሳ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ርስተኛታት ፡ ተብለው ፡ ሲጠሩ ፡ አዲስ ፡ መጭዎቹ ፡ ግን ፡ ማዕከላይ ፡ አልየት ፡ (ሲተረጐም ፡ ባዕዳን ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡) ተብለው ፡ ይጠራሉ።

ይህ ፡ የስራት ፡ ለውጥ ፡ የተደረገበትን ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማ ፡ በትክክል ፡ ለማወቅ፡ ስለማይቻል ፤ ግምት ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ ግድ ፡ ይሆናል ። ሲኞር ፡ ኦስቲኒ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ የተጀመረው ፡ "የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስሜ ትን" ፡ ለማጠንከርና ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖርም ፡ ለማድረግ ፡ በማቀድ ፡ ነው ፤ ሲሉ ፡ አስተያ የት ፡ ሰጥተዋል ።[96] ይህም ፡ በመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ውስጥ ፡ ለርስተኛታት ፡ የተ ለየ ፡ መብት ፡ የተሰጠበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚያስረዳ ፡ ይመስላል ። እንዳጋጣሚ ፡ ሆኖ ፤ ርስተኛታት ፡ የሚለውም ፡ ስያሜ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ ከዘር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ለመመንጨቱ ፡ አንድ ፡ ድጋፍ ፡ ይሆናል ።

ይህን ፡ የሲኞር ፡ ኦስቲኒን ፡ አስተያየት ፡ እንደ ፡ አጠቃላይ ፡ መግለጫ ፡ አድርጎ ለመቀበል ፡ የሚያስቸግር ፡ አንድ ፡ እንቅፋት ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ አንይ ፡ ባዕድ ፤ ማለ ትም ፡ የመንደር ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ ከመንደሩ ፡ ርስት ፡ ተገቢ ፡ ድርሻውን ፡ ሊያገኝ ፡ መቻሉን ፡ ስናስታውስ ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ አቋም ፡ የሆነውን ፡ የቤተ ፡ ሰብን ፡ ስሜት ፡ የማጠንከሩ ፡ ጉዳይ ፡ ቦታ ፡ እንደሌለው ፡ እንገነዘባለን ። እር ግጥ ፡ በሲኞር ፡ ኦስቲኒ ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፤ በቅርቡ ፡ አንዳንድ ፡ መንደሮ ች ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ ዘመዳሞች ፡ በስምምነት ፤ ይተዳደሩበት ፡ የነበረውን ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ ስሪት ፡ ወደመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ የለወጡት ፡ ነው ። ከዚህ፡ ላይ ፡ ሳንጠቅሰው ፡ የማናልፈው ፤ ኢጣሊያኖች ፡ ኤርትራን ፡ ይገዙ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ የነበሩትን ፡ የአንዳንድ ፡ ቀበሌ ፡ ስሪቶች ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ የለወጡትን ፡ ነው ።[97] እንግዲህ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፤ የዘርን ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ሲለውጡት ፡ የነበራቸው ፡ ዓላማ ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ ባይታወቅም ፤ የመንደር ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ አሁን ፡ የምንመረምራ ቸው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ዋነኛ ፡ የስሪት ፡ ዓይነት ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

<u>፪/ ስለእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የአከፋፈል ፡ ሥርዓትና ፡ ግለ ፡ ሰቡም ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ የመብት ፡ ዓይነቶች ፤</u>

የመካፈል ፡ መብት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚፈጸመውን ፡ የእርሻ ፡ መ ሬት ፡ የማደላደል ፡ ስርዓትን ፡ የሚያህል ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ምናልባት ፡ አይኖር ፡ ይሆናል ። ምናልባት ፡ ከዚህ ፡ በየጊዜው ፡ ከሚደረገው ፡ የመሬት ፡ ማከፋፈል ፡ ስር ዓት ፡ ይበልጥ ፡ የ"አንድነትን" ፡ ስሜት ፡ የሚገልጽ ፡ ነገር ፡ አይኖርም ። የሎጎ ፡ ጭዋን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መመሪያ ፡ በማድረግ ፡ ይህን ፡ ሥርዓት ፡ ቀጥለን ፡ እናስረዳ ለን ።

የመንደሩን ፡ መሬት ፡ ለመንደረተኞቹ ፡ የማከፋፈሉ ፡ ተግባር ፡ የሚከናወነው ፡ ከያንዳንዱ ፡ <u>ማርቤት</u> ፡ (ቤተሰብ) ፡ በተውጣጡ ፡ በስድስት ፡ አዋቂ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሲሆን ፤ የሚሰየሙት ፤ የሚመረጡትም ፡ በመንደሩ ፡ ዳኛ ፡ ነው ።[98] ሽማግሌዎቹ ፡ በሁለት ፡ ቡድን ፡ ተከፍለው ፡ ተግባራቸውን ፡ ያከናውናሉ ።

---

96. ኦስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ ጀምሮ ።

97. ወደፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ ሁሉ ፤ ይህ ፡ እርምጃ ፡ የተወሰደው ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ ባላቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ነበር ። ቀደም ፡ ሲል ፤ ኢጣሊያኖችን ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የማስፈር ፡ እቅድ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ስለነበር ፡ የማስፈሩን ፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ መሬት ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። የተባለውን ፡ መሬት ፡ ለማግኘት ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ በኤርትራ ፡ እንዲሁም ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፤ የነበረውን ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ሁኔታ ፡ በተሳሳተ ፡ መልክ ፡ በመመልከት ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አር ፡ ፓንክርስት ፡ "ኢታ ሊያን ፡ ሴትልሜንት ፡ ፖሊሲ ፡ ኢን ፡ ኤርትሪያ ፡ ኤንድ ፡ ኢትስ ፡ ሪፐርከርሽንስ ፡ ፲፰፻፹፱-፲፰፻፺፮" ፡ <u>ቦስቶን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፔፐርስ ፤ ፩ኛ</u> ፡ እትም ፤ ከገጽ ፡ ፩፻፴፩ ፡ ጀምሮ ፡ ይመለከቷል ።

98. <u>የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ</u> ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፱ ።

ጊላፎ ፡ (አጣሪዎች) የሚባለው ፡ የመጀመሪያው ፡ ቡድን ፡ ተግባር ፡ በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ የመካፈል ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ መለየትና ፡ ከዚህ ፡ በፊትም፡ ተገቢ ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ መሬት ፡ ይዞ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ ምንም ፡ እንዳይሰጠው ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ አቋሮ ፡ (ጠባቂ ፡) ወይም ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ አቋሮ ፡ መሬት ፡ (የመሬት ፡ ጠባቂ ፡) ተብሎ ፡ ይጠራል ።[99] ክፍያ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ቡድን ፡ የመንደሩን ፡ ማሳዎች ፡ በሙሉ ፡ በቁጥጥሩ ፡ ሥር ፡ በማ ድረግ ፡ ሁለት ፡ ነገሮችን ፡ ይፈጽማል ። አንደኛ ፡ "መጠባበቂያ ፡ "የእርሻ ፡ መሬትንና፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ ለይቶ ፡ ማስቀመጥ ፤ መጠባበቂያ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ መቀመጡም ፡ የመሬቱ ፡ ክፍያ ፡ ከተከናወነ ፡ በኋላ ፡ ለሚመጡ ፡ የመንደሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሲሆን ፤ ሌላ ፡ ክፍያ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ የመሬት ፡ ችግር ፡ እንዳይገጥማቸው ፡ ለማድረግ ፡ነው ። ሁለተኛም ፡ የመንደሩን ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ በማሳ ፡ በማሳ ፡ እያደ ረጉ ፡ በሚከፈለው ፡ ሰው ፡ ቁጥር ፡ በማከፋፈል ፡[100] ዕጣ ፡ እያወጡ ፡[101] እያንዳንዱን ፡ ማሳ ፡ ዕጣ ፡ ለወጣለት ፡ ሰው ፡ ማደል ፡ ነው ።

የዚህም ፡ የማሳ ፡ ማከፋፈል ፡ ስም ፡ ዋርየዳ ፡ (ቀጥተኛ ፡ ትርጉሙ ፡ ግመታ) ፡ ሲሆን ፤ የሚፈጸመውም ፡ በየስምንቱ ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። "ክፍያው ፡ በየስ ምንት ፡ ዓመት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፤ ምክንያቱም ፡ ገበሬዎች ፡ የእርሻ ፡ መሬታቸውን በሚገባ ፡ ለማልማት ፡ የስምንት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ይበቃቸዋልና ፡ ነው ።"[102] ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ማከፋፈል ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ የተዘጋጁ ፡ ማሳዎች ፡ ለሰነፎች ፡ ሊሰጡ ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ። ገበሬው ፡ "የዝ ናሙ ፡ ጊዜ ፡ ሳያልፍበት" የእርሻ ፡ መሬቱን ፡ ለማዘጋጀት ፡ እንዲችል ፡ ዋርየዳ ፡ የሚ ፈጸመው ፡ ከነሐሴ ፡ ፲፯ ፡ እስከ ፡ ነሐሴ ፡ ፳፩ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።"[103]

ለዚህ ፡ ክፍያ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ሕግ ፤ ትዳራቸውን ፡ በሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ያቋ ቋሙ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ማሳ ፡ ያገኛሉ ፤ የሚለው ፡ ነው ። ይህም ፡ ሕግ ፡ በተለይ ፡ ተፈ ጻሚነት ፡ ያለው ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ለመቋቋም ፡ የፈ ለገ ፡ እንደሆን ፤ በመጀመሪያ ፡ መኖሪያ ፡ የሚሆነው ፡ ጐጆ ፡ ለራሱ ፡ መሥራት ፡ አለ

99. ከዚያው ።

100. "የሚከፋፈለው ፡ ማሳ ፡ ቍጥር ፡ የሚወሰነው ፤ የኢኰኖሚ ፡ ነፃነት ፡ ባገኙት ፡ ሰዎች ፤ ሕጋዊ ፡ ልጆች፡ ባሏቸውና ፡ ባሎቻቸው ፡ በሞቱባቸው ፡ ሴቶች ፤ የአባቶቻቸውን ፡ መኖሪያ ፡ መንደር ፡ ለቀው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ በመመለስ ፡ ኗሪነታቸውን ፡ በዚያው ፡ ባደረጉ ፡ ሴቶችና ፡ ከርስቱ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲ ያገኙ ፡ በተፈቀደላቸው ፡ ማዕከላይ ፡ አልየት ፡ (ባዕዳን) ፡ ቍጥር ፡ ነው ።" አስቲኒ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ቍጥሮች ፡ የተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፹፰ ፡ ጀምሮ፤ አንድን ፡ ድርሻ ፡ በጭሰኝነት ፡ ወይንም ፡ በሌላ ፡ መልክ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይቻላል ። የሚች ፡ ድርሻ ፡ ግን ፡ ለሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል ።

101. በትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ የዕጣ ፡ ማውጣት ፡ ሥርዓት ፡ የሚታየው ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ነው ። የመንደር ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ርስት ፡ (እንደተገነዘብነውም ፡ በአንዳንድ ፡ ቀበሌዎች ፡ የሚታደለው ፡ በዕጣ ፡ ነው፡) በተከፋፋዮቹ ፡ ቁጥር ፡ ልክ ፡ በማሳ ፡ በማሳ ፡ ከተሸነሸነ ፡ በኋላ ፡ የመንደሩ ሽማግሌዎች ፡ ትናንሽ ፡ ስንጥሮችን ፡ ሰብስበው ፡ በመያዝ ፡ በየማሳው ፡ ይሰይሟቸዋል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በሁለት ፡ እጆቹ ፡ ለመያዝ ፡ የሚችለውን ፡ ያህል ፡ ከስንጥ ሮቹ ፡ አንስቶ ፡ ከፍ ፡ ያደርግና ፡ "የሐዋርያት ፡ ዕጣ ፤ ለእውነተኛው ፡ ባለቤት ፡ ውጣ፡" ብሎ ፡ በመናገር፡ ለያንዳንዱ ፡ ተካፋይ ፡ አንዳንድ ፡ ስንጥር ፡ ይሰጣል ። እያንዳንዱም ፡ ተካፋይ ፡ ባገኘው ፡ ስንጥር ፡ የተሰ የመውን ፡ ማሳ ፡ ይወስዳል ። በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ- ም- የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪ ፡ ለነበረው ፡ ለአቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከቀረበ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ።

102. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።

103. ከዚያው ።

በት ። ጐጆ ፡ ለመሥራትም ፡ የሚችለው ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ ለማደላደል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ሦስቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የፈቀዱለት ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ኗሪ ፡ ሆኖ ፡ "ተቋቋሚል ፡" ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተባለው ፡ "ለራሱ ፡ ቤት ፡ በመሥራት ፡ ብቻ ፡" አይደለም ።[104] የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ካላቸው ፡ ሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ (እነዚህም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዘመን ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ የሕዝቡ ፡ ቁጥር ፡ በማደጉ ፡ የውጭ ፡ ሰዎችን ፡ የመቀበል ፡ ፍላጐታቸው ፡ እየተቀነሰ ፡ ሄዷል ።)"[105] በተጨማሪም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እውነተኛ ፡ መንደረተኛ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ። "በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ኗሪ ፡ ሆኖ ፡ መቋቋም ፡ ማለት ፡ ጐጆ ፡ ሠርቶ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ከውስጡ ፡ መቀመጥ ፡ አይደለም ። ከዚያ ፡ መኖርና ፡ መንደረተኛ ፡ የሚጠበቅበትንም ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ይገባል ። የአንድ ፡ መንደረተኛ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ርስት ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ከመንደሩ ፡ ዳኛ ፡ ወይንም ፡ ከዘመዶቿ ፡ ፈቃድ ፡ ሳታገኝ ፡ ከመንደሩ ፡ መውጣት ፡ የለባትም ።[106]

ይህንንም ፡ ግዴታ ፡ አለማክበር ፡ በዋርየዳ ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜ ፡ በተካፈሉት ፡ ማሳ ፡ ላይ ፡ የተገኘን ፡ መብት ፡ እስከ ፡ ማሳጣት ፡ ያደርሳል ።[107]

ሲኞር ፡ አስቴኒ ፡ እንደገለጡት ፡ "የማዕከላይ ፡ አልየት ፡ (የውጭ ፡ ሰዎች ፡) አቋም ፡ በጣም ፡ አስደናቂ ፡ ነው - - - ። ለብዙ ፡ ትውልድ ፡ ያህል ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ የኖሩና ፡ ለብዙ ፡ ዘመናትም ፡ ያህል ፡ የርሻ ፡ መሬት ፡ የያዙ ፡ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ራሳቸውን ፡ ከርስተኞች ፡ (ማለትም ፡ ቤተሰቦቻቸው ፡ ባለርስቶች ፡ ከነበሩ ፡ ሰዎች) ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ አይገምቱም ። ---ከብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በኋላም ፡ እንኳ ፡ ከመንደሩ ፡ የተለየ ፡ አኗኗር ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ።"[108] አስቴኒ ፡ ይህን ፡ ሲናገሩ ፡ የተባሉት ፡ "የውጭ ፡ ሰዎች" በመንደሩ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የመሪነት ፡ ሥልጣን ፡ እንደሌላቸው ፡ ለማመልከት ፡ ነው ። መዘንጋት ፡ የሌለበት ፡ ለብዙ ፡ ትውልድ ፡ በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ የኖረ ፡ "የውጭ ፡ ሰው ፡" ልጅ ፡ እንኳን ፡ ለርሻ ፡ የሚሆን ፡ ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ አስቀድሞ ፡ ራሱን ፡ የመንደሩ ፡ ኑዋሪ ፡ አድርጐ ፡ ማቋቋም ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ነው ።

ይህ ፡ የመቋቋም ፡ ግዴታ ፡ ግን ፡ ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ እጩ ፡ በመሆን ፡ ሊቀርቡ ፡ በሚችሉ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፡ ማለትም ፡ በቅርቡ ፡ የተጋቡ ፡ የመንደሩ ፡ ርስተኞች ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።[109] የአባቶ

---

104. ሠይፉ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ኮንሶሊዴሽን ፡ ኦፍ ፡ ፍራግሜንትድ ፡ ሆልዲንግስ ፡ ኢን ፡ ከሚውናል ፡ ቴንየር ፡ ኤርያስ ፡ (፲፱፻፷፯ ፡ ያልታተመ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት) ።
105. ከናዴል ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፲ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።
106. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።
107. ከዚያው ።
108. ኦስቴኒ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፹፰-፺፬ ።
109. "አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ የተለየ ፡ የራሱን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በሚያቋቁምበት ፡ ጊዜ ፡ ማሳ ፡ ይሰጠዋል ። ጭቃውና ፡ ሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ በሚገኙበት ፡ የልጁ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ለመቋቋሚያው ፡ የሚሆነውን ፡ ይሰጡታል ፤ (ያደርጉለታል) ፡" ከሚለው ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ። የአከለ ፡ ጉዛይ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፵፪ ።

ቻቸው ፡ "መቋቋም" ፡ ለእነርሱም ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ ይመስላል ።[110] ስለዚህም ፡ ሚስት ፡ ካገቡ ፤ ከመንደሩ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ማሳዎችን ፡ ለማግኘት ፡ ይችላሉ ። "የውጭ ዎቹም ፡ ሰዎች ፡" ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲሁ ፡ ሚስት ፡ ማግባት ፡ ይኖርባቸዋል ።

የሴት ፡ ልጅ ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ተወላጆቻቸው ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ልጆችና ፡ ተወላጆቻቸው ፡ ሁሉ ፡ በመንደር ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ በመሆን ፡ "ሊቋቋሙ ፡" የሚችሉ መሆናቸውን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መጥቀስ ፡ ይገባል ።[111]

ዋርየዳ ፡ ሲደረግ ፡ መመሪያው ፡ "እኩልነት ፡" እንጂ ፡ ከኢኮኖሚ ፡ የሚገኘው ፡ ሀብትና ፡ ብልጽግና ፡ አይደለም ። "በሂሳብ ፡ ረገድ ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ (የርስት ፡) መከፋፈል ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ የመንደሩ ፡ ማሳ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ለምነቱ ፡ በዓይነት ፡ በዓይነቱ ፡ ተሸንሽኖ ፡ ይመደባል ። በብዛት ፡ በሚሠራበት ፡ ስነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ የመሬት ፡ አመዳደብ ፡ እናገኛለን ፤ (ለም ፤ ለም ፡ ጠፍና ፡ ጠፍ) ዕጣም ፡ የሚወጣው ፡ ለያንዳንዱ ፡ የመሬት ፡ ዓይነት ፡ ሲሆን ፤ ገበሬውም ፡ ከየዓይነቱ ፡ አንዳንድ ፡ ማሳ ፡ ይቀበላል ።"[112]

ይህ ፡ በየጊዜው ፡ የሚደረገው ፡ የርስት ፡ ማከፋፈል ፡ ሥርዓት ፡ የርስት ፡ ሽያጭን ፡ እንደሚያግድ ፡ በትክክል ፡ ከዚህ ፡ በቀደም ፡ ተገልጿል ።[113] ነገር ፡ ግን ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ ሊሸጥ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ከመናገር ፡ ይልቅ ፤ ጥንት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስላል ተገኘ ፡ የመሬት ፡ ሺያጭ ፡ አይታወቅም ፤ ብሎ ፡ መናገሩ ፡ ትክክል ፡ ይመስላል ።[114] ሆኖም ፡ መሬት ፡ በኪራይ ፡ ሊሰጥ ፡ መቻሉን ፡ መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ። ለምሳሌም ፡ አንዲት ፡ ከመንደር ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ድርሻ ፡ የተቀበለች ፡ ሴት ፡[115] ራሷ ፡ ለማረስ ፡ ስለማትችል ፡ "ጉልበትና ፡ በሬ ፡"[116] ላለው ፡ ሰው ፡ በኪራይ ፡ አሳልፋ ፡ ልትሰጥ ፡ ትችላለች ።

ሐ/ <u>በሌሎች ፡ የቤተ ፡ ሰብና ፡ የመንደር ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ስላሉ ፡ ግላዊ ፡ መብቶች፤</u>

፩/ <u>በመንገዶች ፤ በቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችና ፤ ለመጠባበቂያ ፡ በተወሰኑ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ መብት ።</u>

የስራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡[117] የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግም[118] ፡ የትላልቅ ፡ መንገዶችን ፡ (<u>መንገድ ፡ አርብዓ</u>) ፡ ስፋት ፡ ወስኖ ፡ ይደነ

110. ነገር ፡ ግን ፡ የሚከተለውን ፡ ይገነዘቧል ። "(ዱሳ ፡ ወይንም ፡ ሸኽና ፡ ከሚለው ፡ የርስት ፡ ስሪት፡ ውስጥ፡) ድርሻ ፡ ማሳ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ በመንደር ፡ ውስጥ ፡ በመኖር ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ እንደተወላጅነት ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ ከግምት ፡ አይገቡም" ። (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው) ፡ አምኃ ፡ ጽዮን ፡ ዶሚኒኮ ፤ <u>አሎኬሽን ፡ አፍ ፡ ኮንሶሊዴትድ ፡ ዩኒትስ ፤ ኢንዲቪጁያል ፡ አርኰሚውናል)</u> ፤ ፲፱፻፷፯ ፤ ያልታተመ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ገጽ ፡ ፩። ጥንት ፡ ባለርስት ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ ተወላጅ ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚጠቅም ፡ ቀደም ፡ ስንል ፡ ተመልክተናል ።

111. ከአምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፲፭ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

112. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፤ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፲፫ ።

113. ላውረንስና ፡ ማን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፭ ።

114. ከቢንቲ ፡ ኢንቺል ፡ "ዱ ፡ አፍሪካን ፡ ሲስተምስ፡አፍ፡ላንድ፡ቴንየር፡ሪኳየር፡ኤ፡ስፔሺያል ፡ ተርሚኖሎጂ?" <u>ጆርናል ፡ አፍ ፡ አፍሪካን ፡ ሎው</u> ፤ ቮልዩም ፡ ፱ ፡ (፲፱፻፷፭) ፤ ከገጽ ፡ ፩፻፴፯-፩፻፴፱ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

115. <u>የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ</u> ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ።

116. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፱ ። "ነዋሪ" ፡ የመሆኑ ፡ ግዴታ ፤ ሁለት ፡ ማሳዎችን ፡ በስውር ፡ በተለያዩ ፡ በሁለት ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ ከመያዝ ፡ ማገዱን ፡ ማስተዋል ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ይህ ፡ ግዴታ ፡ ከሁለት ማሳዎች ፡ አንዱን ፡ ለመሸጥ ፡ ሲኖር ፡ የሚችልን ፡ ምኞት ፡ ይቀንሰዋል ።

117. የስራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰ ፤ "መንገዶችን ፡ የሚመለከቱ ደንቦች ፡" በሚለው ፡ ሥር ።

118. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፷፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፷፯ ።

ግጋል ። መንገዶችን ፡ በሚገባ ፡ ለመያዝና ፡ ለመጠገን ፡ ኀላፊዎቹ ፡ መንደረተኞቹ ፡ ብቻ ፡ ቢሆኑም ፡ የውጭ ፡ ሰውም ፡ ሆነ ፡ መንደረተኛ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ ይችላል ።[119] በሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ መንገዶችን ፡ ማረስ ፣ ቋጥኝ ፡ ድንጋዮችን ፡ ወይንም ፡ ግንዲላ ዎችን ፡ በመንገዶች ፡ ላይ ፡ ማስቀመጥ ፡ ወንጀል ፡ ነው ።[120]

ከመንደር ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ማሳ ፡ ለማግኘት ፡ ቤት ፡ መሥራትና ፡ ባለቤትም ፡ መሆን ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፣ ቤቶችንና ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎችን ፡ የመቆጣጠሩ ፡ ጉዳይ ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ነው።

ስለዚህም ፡ የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎች ፡ አቀማመጥ ፣ ለየሰዉ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ቦታ ፡ ልክ ፣ ስለ ፡ አማካይ ፡ የወሰን ፡ አጥሮች ፡ ስለቤት ፡ ውርስና ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ የቤቶች ፡ ፕላን ፡ ሰፋ ፡ ያሉ ፡ ደንቦችን ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። “ከስድስት ፡ መደዳ ፡ ቤቶች ፡ በኋላ ፡ መንገድ ፡ መኖር ፡ አለበት ።”[121]

አስፈላጊውን ፡ ፈቃድ ፡ ሳያገኝ ፡ በአንድ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ቤት ፡ የሰራ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፣ መቀጫ ፡ ከፍሎ ፡ እንዲለቅ ፡ ይገደዳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቤቱን ፡ የሠራው ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብሎ ፡ ከሆነ ፡ በርስተኛታት ፡ እንዲለቅ ፡ ሲገደድ ፣ ቤቱ ፡ የተሠራበትን ፡ የጣራ ፡ የማገሩን ፡ እንጨት ፡ ይዞ ፡ ለመሄድ ፡ መብት ፡ አለው ። ፈቃድ ፡ ሳያገኝ ፡ ቤት ሠርቶ ፡ ወይንም ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ወደሌላ ፡ መንደር ፡ ለመዛወር ፡ ፈልጎ ፡ የሆነ ፡ እን ደሆነ ፡ የጣራ ፡ ማገሩ ፡ እንጨት ፡ ለርስተኛታት ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል ።[122] የአባ ቱን ፡ ቤት ፡ የሚወርሰው ፡ ልጅ ፡ ከመጀመሪያዋ ፡ ሚስት ፡ የተወለደው ፡ ነው ። “ምክንያቱም ፡ በቤቱ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነችው ፡ የመጀመሪያ ፡ ሚስት ፡ ስለሆነች ፡ ከሁለተኛዋ ፡ ሚስት ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ እናቱ ፡ ያልለፋችበትን ፡ እንዲያገኝ ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ስላልሆነ ፡ ነው ።”[123]

አዲስ ፡ የተጋቡ ፡ ሙሽሮች ፡ ለቤት ፡ መሥሪያ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ የሚያገኙት ፡ ለመጠባበቂያ ፡ ከተቀመጠው ፡ መሬት ፡ ሲሆን ፣ በውስጡም ፡ የርሻ ፡ መሬት ፣ ለመን ደረተኞች ፡ ያልታደለ ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታና ፡ ለአደን ፡ የተከለለ ፡ መሬት ፡ ይገኙበታል ። በባለርስተኞቹ ፡ ፈቃድ ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ በኪራይ ፡ መልክ ፡ የሚገኘውን ፡ መሬት ፡ ኪራይ ፡ መንደረተኞቹ ፡ የመከፋፈል ፡ መብት ፡ አላቸው ። በተጨማሪም ፡ ዋርየዳ ፡ ከተከናወነ ፡ በኋላ ፡ የሚመጡ ፡ አባሎች ፣ ለመጠባበቂያ ፡ ከተቀመጠው ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ የርሻ ፡ ማሳ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ አላቸው ።[124]

፪/ <u>በሣርና ፡ በእንጨት ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ መብት</u> ፤

በሰራዬ ፡ ውስጥ ፡ “ሣር ፡ እምን ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ እንደሚውልና ፡ ምን ፡ እንደሚ ደረግ ፡ የሚወሰነው ፡ በየመንደሩ ፡ (ወይንም ፡) ስለመንደሩ ፡ ሆነው ፡ በሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ነው ።”[125] በአንዳንድ ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፤ ከመ

119. ከዚያው ።
120. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፯ ።
121. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፯ ።
122. ከዚያው ።
123. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፲፯ ።
124. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፣ ገጽ ፡ ፭፯።
125. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ “ግጦሽን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡” በሚለው ፡ ሥር ።

ንደሩ ፡ ውጭ ፡ የሚገኙ ፡ ሰፋፊ ፡ ቦታዎች ፡ ለከብቶች ፡ ግጦሽ ፡ በመከለል ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆን ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ "የተከለከሉ ፡" እና "የተፈቀዱ ፡" በመባል ፡ ተከፋፍለው ፡ ይጠበቃሉ ።[126]

በነዚህ ፡ የግጦሽ ፡ መስኮች ፡ ላይ ፡ እንዲሠማሩ ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ የመንደሩ ፡ ከብቶች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

የዘርም ፡ ሆነ ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኙባቸው ፡ ቀበሌ ፡ ሁሉ ፡ ዛፎች ፡ በሁለት ክፍል ፡ ተመድበው ፡ ለየብቻቸው ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ተበጅቶላቸዋል ። ዛፎች ፡ ባለሀብትነታቸው ፡ የግል ፡ ወይም ፡ የጋርዮሽ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ለእርሻ ፡ ከተመደበለት ፡ ማሳው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚኖርበት ፡ አካባቢ ፡ ዛፍ ፡ ሊተክል ፡ ይችላል ፤ በዛፉም ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ። ስለዚህም ፡ ዛፉን ፡ ቆርጦ ፡ ለፈቀደው ፡ ማዋልና ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ እንዳይነኩት ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ "የጋርዮሽ ፡" በሆኑ ፡ ዛፎች ፡ ለመጠቀም ፡ መብት ፡ አለው ። እነዚህም ፡ ዛፎች ፡ "ከጫካ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡" የተፈጥሮ ፡ ጸጋዎች ፡ ናቸው ። ሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ በጫካ ፡ የሚገኝን ፡ ዛፍ ፡ ለመቁረጥ ፡ የጀመረ ፡ ሰው ፡ ዛፉን ፡ በሰላሣ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ቆርጦ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ መብት ፡ አለው ፤ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሊቆርጡትና ፡ በፈቀዱትም ፡ ሊያውሉት ፡ ይችላሉ ።[127] በአንዳንድ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የጋርዮሽ ፡ የሆኑ ፡ ዛፎችን ፡ ለመቁረጥ ፡ ፈቃድ ፡ መቀበል ፡ ያሻል ፤ (ይህ ፡ ለፎርማሊቲ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፤ የጠየቀ ፡ ሁሉ ፡ ይፈቀድለታል ።)[128] አንድን ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ለማሳነጽ ፡ ሲፈለግ ፡ ግን ፤ የማንንም ፡ ፈቃድ ፡ ሳይቀበሉ ፡ ዛፍን ፡ ቆርጦ ፡ መውሰድ ፡ ይቻላል ።[129]

### ፫/ ስለአውድማ

አውድማንና ፡ የእርሻ ፡ ዕቃን ፡ የሚመለከቱ ፡ የሰራዬና ፡[130] የሎጎ ፡ ጭዋ ፡[131] ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ድንጋጌዎች ፡ እጅግ ፡ ይመሳሰላሉ ።

የእርሻ ፡ መሣሪያዎች ፤ እንስሳትም ፡ ጭምር ፤ በሕብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ ፍጹም፡ የግል ፡ መብት ፡ ስር ፡ ይገኛሉ ። ሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ውስጥ ፡ የባለቤቱን ፡ ፈቃድ ፡ ሳይቀበል ፡ በእርሻ ፡ መሣሪያዎቹ ፡ የሚጠቀም ፡ ሰውና ፡ የተዋሰውንም ፡ ቀንበር ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የማይመልስ ፡ ሁሉ ፡ መቀጫ ፡ ይጣልበታል ።[132]

የአድከመ ፡ ምዕልግና ፡ የሎጎ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ መሬት ላይ ፡ የተበጀ ፡ አውድማን ፡ የሚገምቱት ፡ እንደባለቤቱ ፡ "የግል ፡ ገንዘብ" ነው ።

---

126. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፪-፳፫ ።
127. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፴፩-፴፪ ።
128. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፪ ።
129. ከዚያው ።
130. የሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰው ፤ "አውድማዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች" ፡ በሚለው ፡ ሥር ።
131. የሎጐ ፡ ጭዋ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፳፬ ፡ እና ፡ ፴ ።
132. ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፳፬ ።

በእንዲህ ፡ ያለው ፡ አውድማ ፡ ላይ ፡ እህሉን ፡ ሊወቃ ፡ የፈለገ ፡ ሁሉ ፡ የባለቤቱን ፡ ፈቃድ ፡ አስቀድሞ ፡ መቀበል ፡ ይገባዋል ።

በሰራዬ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ስር ፡ "የጋርዮሽ ፡ አውድማ ፡" የሚባልም ፡ አለ ፤ ሆኖም ይህ ፡ የሚታየው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ። በየምክንያቱ ፡ የተነሣ ፡ "የራሱ ፡" የሆነ ፡ አውድማ ፡ የሌለው ፡ ሁሉ ፡ መንደረተኞች ፡ በጋርዮሽ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ባበጁት ፡ አውድማ ፡ ላይ ፡ እህሉን ፡ ለመውቃት ፡ ይችላል ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ አውድማ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚገኘው ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ባልሆነ ፡ ኮረብታማ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ከላይ ፡ በመረመርናቸው ፡ ሰፍረው ፡ በእርሻ ፡ በሚተዳደሩ ፡ የጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ድርሻው ፡ የሆነውን ፡ የዘር ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ የሚያርሰው ፡ በራሱ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ። አንዳንዴ ፡ ግን ፤ በሌላው ፡ የመንግሥቱ ፡ ግዛት ፡ ክፍል ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ እርሻ ፤ አጨዳ ፤ ወይም ፡ ውቂያ ፡ ሲደርስበት ፡ የጐረቤቶቹንና ፡ የመንደረተኞቹን ፡ እርዳታ ፡ በደቦ ፡ መልክ ፡ መጠየቁ፡ አይቀርም ።[133]

የጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ በሌሎች ፡ የጋራ ፡ መሬቶች ፡ ዓይነት ፤ ማለት ፡ በመንገዶች ፤ በቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታዎች ፤ በጫካዎች ፡ እና ፡ በግጦሽ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ መርምረናል ፤ ካደረግነውም ፡ ምርመራ ፡ የየሰዉ ፡ አጠቃቀም ፡ "የግል ፡" መሆኑን ፡ ተገንዝበናል ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተገለጠው ፤ ከላይ ፡ በመረመርናቸው ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ በሚከተሉ ፡ የጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ "አባሎቹ ፡ በመሬት ፡ ሲጠቀሙ ፡ በጋርዮሽ ፡ ነው" ፡ የሚል ፡ የተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የጎብረ ፡ ሰብኡን ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ለመግለጥ ፡ ከሚገለገሉባቸው ፡ ስያሜዎች ፡ "ኮሙናል ፡ ሬጅም ፡" የሚለው ፡ ይገኝበታል ። --- "መሬት ፡ በጋርዮሽ ፡ አይታረስም ። እያንዳንዱ ቤት ፡ ሰብ ፡ ወይም ፡ አባል ፡ የራሱ ፡ የሆኑ ፡ ማሳዎች ፡ አሉት ፤ ያርሳቸዋልም ።"[134] በነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ "የጋራ ፡ (የተራድኦ ፡) እርሻ"ን ፡ የሚመስል ፡ ዝግጅት ፡ የሚታየው ፡ አባት ፤ እናትና ፡ (ብዙውን ፡ ጊዜ) ያላገቡ ፡ ልጆቻቸው ፡ በአባትየው ፡ መሪነት ፡ በሚያርሱት ፡ ማሳ ፡ ላይ ፡ ነው ።[135]

መ/ <u>ስለዘርና ፡ ስለመንደር ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ጠቃሚነት ፡ እና ፡ ጐጂነት ፡</u>[136]

"የጋርዮሽ ፡ መሬት" (ኮሙናል ፡ ላንድ ፡) በሚለው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከተደረሱት ፡ ጽሑፎች ፡ ብዙዎቹ ፡ ስለ ፡ ስሪቱ ፡ ጎጂነት ፡ አመዝነው ፡ ስለሚገኙ ፤ በነዚሁ ፡ እንጀምራለን ።

133. ይህ ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፤ ደራሲው ፡ (በሰራዬ ፡ ለኖረው) ፡ ለአቶ ፡ ዓለም ፡ ሰገድ ፡ ተስፋዬ፤ (በሎጐ ፡ ጭዋና ፡ በአክለ ፡ ጉዛይ ፡ ለኖረው) ፡ ለአቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ኃብተ ፡ ሥላሴና ፡ (በሐማሴን ፡ ለኖረው) ፡ ለአቶ ፡ ዑቅባ ፡ ሚካኤል ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። በተጨማሪም ፡ (በትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በእንደርታና ፡ በአድዋ ፡ ለኖረው) ፡ ለአቶ ፡ ዮሴፍ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥያቄ ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ። የሁሉም ፡ መልስ ፡ የማያወላውል ፡ ተመሳሳይ ፡ ነበር ። (ጥያቄዎቹ ፡ የቀረቡት ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷ ፡ ዓ- ም- ላይ ፡ ነበር ።)

134. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፱ ።

135. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ በተጠቀሰው ፡ ከገጽ ፡ ፶፮ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

136. ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በጠቅላላ ፡ ላይ ፡ አምኃ ፡ ጽዮን ፡ ዶሜኒኮ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፲ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ከገጽ ፡ ፴፯-፴፰ ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።

ከታች ፡ የምንመረምራቸው ፡ "ጎጂ ፡" ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊው ፡ ጥናት ፡ በየ ቦታው ፡ ተደርጎ ፡ ያልተገኙ ፡[137] እና ፡ ይበልጡንም ፡ ጊዜ ፡ የየደራሲውን ፡ ግምት ፡ ያዘሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ አንባቢ ፡ ሊገነዘበው ፡ ይገባል ። እርግጠኛ የሆነ ፡ መረጃ ፡ ስለሌለ ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ የምንዘረዝራቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ "ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡" ሲሉ ፡ በምንመረምራቸው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ሊገኙ ፡ ስለሚችሉት ፡ ነገሮች ፡ በግምት ፡ የሰነዘሩትን ፡ አስተያየት ፡ ነው ።

በጋርዮሽ ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ፡ ተብለው ፡ ከሚገመቱት ፡ ጐጂ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ቀደምትነት ፡ ይዞ ፡ የሚገኘው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ በይዞ ታው ፡ ላይ ፡ ዋስትና ፡ ማጣቱ ፡ ነው ።[138] ማሳ ፡ ይዞ ፡ ከሚተዳደር ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሌላው ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ አባል ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድርሻውን ፡ ጠይቆ ፡ ሊወስድ ፡ መቻሉ ፡ "የአሁኑ፡ ባለይዞታ--- ማሳውን ፡ ለማሻሻል ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ እንዳይወሰድ ፡ ያደርገ ዋል ።"[139]

አንዱ ፡ ሌላው ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረው ፡ ጐጂ ፡ ነገር ፡ የተቆራረጠ ፡ መሬት ፡[140] የመያዙ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህም ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ጥቅም ፡ በማያስገኝ ፡ ማሳ ፡ መጠ ቀምን ፡ ማስከተሉ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚከፋፈልበት ፡ ጊዜ ፡ የኤኮ ኖሚ ፡ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች ፡ መመሪያ ፡ አለመሆናቸውንና ፡ ሰነፉና ፡ ብርቱ ውም ፡ እኩል ፡ መጠቀማቸውን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ለመጥቀስ ፡ ይቻላል ።[141] በተጨማ ሪም "--- የአራሹ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ማሳውን ፡ አለማረሱ ---" እና ፡ ይህ ፡ በሚሆን በት ፡ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥም ፡ ሁሉ ፡ ይዞታን ፡ ለማሻሻል፡ ጥረት ፡ እንዳይደረግ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባም ።[142]

የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ የታየው ፡ ሌላ ፡ እጅግ ፡ አሳ ሳቢ ፡ የሆነው ፡ ችግር ፡ በመሬት ፡ ምክንያት ፡ ተነስተው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቀር ቡት ፡ ክሶች ፡ ቁጥር ፡ ከልክ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። እርግጥ ፡ ነው ፣ ይህ ፡ ችግር ፡ በየትም ፡ ያለ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተደረገው ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከሚነሱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስቱ ፡ ያህል ፡ መሬት ፡ ነክ ፡ እንደሆኑ ፡ ተገምቷል ።[143] የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ ተነስተው ፡ የሚገኙት ፡ መሬት ፡ ነክ ፡ ክርክሮች ፡ ግን ፡ ዓይነታቸው ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በመሬት ፡ ክፍያ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ሲሆኑ ፡" ---የከረረ ፡

---

137. "እነዚህ ፡ (ጐጂ ፡ ነገሮች) ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ባላቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ የቱን ያህል ፡ ተስፋፍተው ፡ እንደሚገኙ ፡ እርግጠኛው ፡ ስለማይታወቅ ፡ በግምት ፡ ብቻ ፡ የታለፈ ፡ መሆኑን ማመን ፡ ይገባል ።" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።) ፡ ላውረንስና ፡ ማን ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፻፶፲፭ ።
138. ከዚያው ።
139. ከዚያው ።
140. ደምሴ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፵፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷፩-፷፪ ።
141. አምባዬ ፡ ዘካርያስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፲፬-፲፭ ፡ ጋር ፡ ያወዳድ ሯል ።
142. ደምሴ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፵፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፷፩-፷፪ ።
143. ኤስ ፡ በፍ ፣ ኢ-ኪ-ቱ- ላንድ ሪፎርም ፡ ኢን ፡ ኢትዮፕያ ፤ አን ፡ ኢንትሮዳክሽን ፡ ቱ ፡ ካዳስትራል ፡ ሰር ቬይ ፡ ኤንድ ፡ ላንድ ፡ ሬጅስትሬሽን ፡ (፲፱ ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት) ፡ ገጽ ፡ ፲ ።

ጠብ ፡ ከሚያስነሱት ፡ ዋነኞቹ---" [144] ናቸው ። እነዚህ ፡ "---የከረሩና ፡ ቶሎ ፡ የማይቆረጡ ፡ በርስቲ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ የጠላትነት ፡ መነሾች--" [145] በጊዜው ፡ ኤርትራን ፡ ያስተዳድር ፡ የነበረውን ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ ከማሳሰባቸው ፡ የተነሣ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ አካባቢ ፡ መንግሥቱ ፡ ርስቲ ፡ የነበሩትን ፡ ቀበሌዎች ፡ ወደ ፡ ዴሳ ፡ ለመለወጥ ፡ ተገዶ ፡ ነበር ፤ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ቀላል ፡ መፍትሔ ነበር ።

በዚህ ፡ በዘልማድ ፡ "የጋርዮሽ ፡ ስሪት ፡" (ኮሙናል ፡ ቴንዮር ፡) በሚባለው ፡ ስሪት፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ሕዝብ ፡ ከሚያሳየው ፡ ተቃውሞ ፡ የተነሣ ፡ ማንኛውም ፡ የርስት፡ ምዝገባ ፡ ዓይነት ፡ እንዳይጀመር ፡ እንቅፋት ፡ እንደሆነ ፡ ተገምቷል ።[146] እንዲሁም ፡ "---የእርሻን ፡ ተግባር ፡ ከዘመኑ ፡ ወደኋላ ፡ በቀረ ፡ ደረጃ---" [147] እና ፡ "---ባነሰ ፡ የገንዘብ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ---" [148] ላይ ፡ እንዲቀር ፡ በማድረጉ ፡ ተቃውሞ ፡ ቀርቦበታል ።

በመጨረሻም ፡ ይህ ፡ እስካሁን ፡ የመረመርነው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፡ ዓይነት ፡ ሕዝቡን ፡ በአቋምና ፡ በኑሮ ፡ ደረጃ ፡ የሚያከፋፍል ፡ በመሆኑ ፡ ቅሬታን ፡ ሲያስከትል ፤ በእኩልነት ፡ ረገድ ፡ ተሽሎ ፡ የሚታየው ፡የግል ፡ ባለቤትነት ፡ ተመርጦ ፡ ይገኛል ።[149] "የጋርዮሽ ፡ ስሪት ፡ ወደ ፡ ግል ፡ ስሪት ፡ ሊለወጥ ፡ ይገባል ፡" የሚለውን ፡ ሀሳብ ፡ የሚደግፉ ፡ ሁሉ ፤ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ይህ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ በማስታወስ ፡ ሲጽናኑ ፡ ይታያሉ ።[150]

የዘርና ፡ የመንደር ፡ ስሪት ፡ ደጋፊዎች ፡ ጥቂት ፡ ይመስላሉ ፤ ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ሚስተር ፡ ናዴል ፡ የተባሉ ፡ ደራሲ ፡ ስለዚህ ፡ ስሪት ፡ ጠቃሚነት ፡ ሲያትቱ ፤ ርስቲና፡ ዴሳ ፡ "---በሀገራችን ፡ (በእንግሊዝ ፡ ሀገር) የሚገኙትን ፡ የግልና ፡ የጋርዮሽን ፡ ስሪት ፡ ባለጠግነትንና ፡ እኩልነትን ፡ (ሶሻሊዝም ፡ ወይም ፡ ኮሙኒዝምን ፡)---"[151] ይመስላሉ ፤ ሲሉ ፡ ጽፈዋል ። ሚስተር ፡ ናዴል ፡ አጠንክረው ፡ የሚያመለክቱት ፡ ዴሳ ፡ የሚባለው ፡ የመሬት ፡ ስሪት ፤ የመሬት ፡ ዓይነት ፡ "---እጅግ ፡ በሚለያይበት--" ቀበሌ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑንና ፡ የሚታየውም ፡ "የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ስሜት ፡ " "--ጊዜያዊ ይዞታ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የሚቀራረብ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ አባል ፡ ነውና ፡ ተከታዮቹን ፡ በማሰብ ፡ እንዲሠራ ፡ ያደርገዋል ፡" የሚለውን ፡ ክርክር ፡ ነው ።[152] ስለዚህ ፡ ከላይ ፡ እንደጠቀስነው ፡ ሚስተር ፡ ማንና ፡ ሚስተር ፡ ላውረንስ ፡ እንዳሉት ፡ ሳይሆን ፤ በሚስተር ፡ ናዴል ፡ አስተያየት ፡ "የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ስሜት" እጅግ ፡ ጠን

---

144. ዱንካንሰን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፩፻፵፫ ። በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ከሚቀርቡት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ የሚበልጡትና ፡ አስቸጋሪዎቹም ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ መሬትን ፡ የሚመለከቱ ፡ እንደነበሩ ፡ ሚስተር ፡ ዱንካንሰን ፡ በግምት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ አስተያየት ፡ ሰንዝረዋል ።
145. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከገጽ ፡ ፲፬ ።
146. ለክቡር ፡ አፈንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ- ም- ከቀረበ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ። መንገሻ ፡ ወርቅነህ ፤ አግራሪያን ፡ እስትራክቸር ፡ ኤንድ ፡ አግራሪያን ፡ ሪፎርም ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ (፲፱፻፷፩ ፡ ዓ- ም- ፤ ያልታተመ ፤ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ቤት ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፡) ፡ ከገጽ ፡ ፲፰ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።
147. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፴፯ ።
148. ከዚያው ።
149. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፲፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፬ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ።
150. ላውረንስና ፡ ማን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፩-፫፻፲፯ ፤ ሚስተር ፡ በፍ ፤ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተውን ፡ ሕዝብ ፡ በማስተማር ፤ ይህን ፡ ለውጥ ፡ ማፋጠን ፡ ይቻላል ፡ ሲሉ ፡ ተናግረዋል ። በፍ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፵፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ፡
151. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቊጥር ፡ ፳፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፩ ።
152. ከዚያው ።

ካራ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የዋስትናውን ፡ ችግር ፡ በማቃለል ፡ እያንዳንዱ ፡ ባለይዞታ ፡ የሌሎችን ፡ ጥቅም ፡ በማሰብ ፡ እንዲሠራ ፡ ያደርገዋል ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የኢትዮጵያው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ "የዘር ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ወደግል ፡ ስሪት ፡ ሊለወጥ ፡ ይገባዋል ፡" የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ የተቀበለው ፡ አይመስልም ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የተወሰደውን ፡ እርምጃ ፡ ዘግየት ፡ ብለን ፡ እንመለከተዋለን ። ስለምንመረምረው ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ጠቃሚነትና ፡ ጐጂነት ፡ ከላይ ፡ የተነጋገርንበት ፡ ምክንያት ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በተባለው ፡ ስሪት ፡ ጸንቶ ፡ መቆየት ፡ ቅሬታ ፡ የገባቸው ፡ መሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪

## ስለቤኒ ፡ አምር ፡ እና ፡ ስለደንከል ፡ ሕዝቦች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋምና ፡ የመሬት ፡ ስሪት ።

### ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ስለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋማቸው ፡-

በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እና ፡ እንዲሁም ፡ በጠቅላላው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኙት ፡ ክርስቲያን ፡ ስላልሆኑት ፡ ክፍሎች ፡ ያለው ፡ መረጃ ፡ እጅግ ፡ የተወሰነ፡ በመሆኑ ፤ በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የምናደርገው ፡ ምርመራ ፡ የቤኒ ፡ አምርንና ፡ የደንከል ፡ ሕዝቦችን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ይሆናል ፤ በደራሲውም ፡ አስተያየት ፡ እነዚህ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፶፱ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ያቀዳቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ሁኔታ ፡ ጥሩ ፡ አድርገው ፡ የሚያሳዩ ፡ ናቸው ።

ኤርትራ ፡ በእንግሊዝ ፡ አስተዳደር ፡ ስር ፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ (በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ. ም. አካባቢ) ፤ ቤኒ ፡ አምር ፡ "---በስተምዕራብና ፡ በደቡባዊ ፡ ምዕራብ ፡ እንዲያውም ፡ (በጠቅላላው) ፡ ኤርትራ ፡ ከሚገኙት ፡ ጐሳዎች ፡ በቁጥር ፡ የላቀ ፡ ነበር ። --- ጎሳውም ፡ ይገኝ ፡ የነበረው ፡ ከአቆርዳት ፡ በስተሰሜን ፤ በምዕራብና ፡ ደባቡዊ ፡ ምዕራብ ፡ ሆኖ ፤ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ በመስፋፋት ፡ ከሱዳን ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠልቆ ፡ (ይገባና) ፡ --- በምሥራቅ ፡ ወደ ፡ (ከረንና ፡ ሰራዬ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ይገኝ፡ነበር ፡) ---"[153] የደንከሌ ፡ ጐሳዎች ፡ ግን ፡ "ደንበኛ ፡ የቆላ ፡ ሰዎች ፡" በመሆን ፡ የኤርትራን ፡ ምሥራቃዊ ፡ ቆላዎች ፡ ይዘው ፡ ይገኙ ፡ ነበር ።[154]

የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ "ክፍልፋዮች ፡" ወይም ፡ "ቅርንጫፎች" እንደነበሩት ፡ ተነግሯል ።[155] እያንዳንዱ ፡ ክፍልፋይ ፡ የጐሳ ፡ አባልነቱን ፡ ቢያውቅም ፡ የሚጠራው ፡ በየራሱ ፡ ስም ፡ ነበር ። "የቤኒ ፡ አምርን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅርንጫፎች ፡ የሚያስተሳስሩአቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ሃይማኖት፤ ቋንቋ ፡ ተመሳሳይ ፡ ባህል ፡ ልማድና ፡ ካንድ ፡ ጐሳ ፡ መወለድ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ ስለተባለ ፡ እነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አስተሳስረውት ፡ ይገኛሉ ፤ በግልጽም ፡ የተያያዙ ፡ ናቸው ፤ ማለት ፡ አይደለም ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ለቅርንጫ

153. ብሪቲሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፯ ።

154. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፳፫ ።

155. ኤስ ፡ ናዴል ፤ "ኖትስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ቤኒ ፡ አምር ፡ ሶሳይቲ ፤" ሱዳን ፡ ኖትስ ፡ ኤንድ ፡ ሪኮርድስ ፤ ቮልዩም ፳፮ ፤ ፓርት ፡ ዋን ፤ (፲፱፻፵፭) ፡ ገጽ ፡ ፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰውን ፤ ገጽ ፡ ፯ ፤ ፳፫ ፡ እና ፡ ተከታዮቹን ፡ ይመለከቷል ፡ በተጠቀሰው ጽሑፍ ፡ መሠረት ፤ የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ሀያ ፡ አንድ ፡ ቅርንጫፎች ፡ አሉት ።

ፎች ፡ በሙሉ ፡ እውነት ፡ ሆነው ፡ አይገኙም ፤ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ በመደራረብ ፡ ግማ ሾቹ ፡ አንዳንዶቹን ፡ የጐሳውን ፡ ቅርንጫፎች ፡ አስተሳስረው ፡ ሲገኙ ፡ ግማሾቹ ፡ ደግሞ ፡ የቀሩትን ፡ አስተሳስረው ፡ ይገኛሉ ።”[156]

የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ የእስልምናን ፡ ሃይማኖት ፡[157] የሚከተል ፡ ሲሆን ፣ ቋንቋ ውም ፡ ትግሬ ፡ ወይም ፡ ቤጃ ፡[158] ነው ። ጥንት ፡ “ከመካከለኛው ፡ አባይ ፡” ፈልሶ ፡ መጥቶ ፡ በቤኒ ፡ አምር ፡ “ሀገር ፡” ይገኙ ፡ ከነበሩት ፡ ጥንታውያን ፡ ነዋሪዎች ፡ በማግ ባት ፣ ዘር ፡ ተክቶ ፡ ተወላጆቹም ፡ ያጋጠማቸውን ፡ ሁሉ ፡ በማሳመን ፡ ካስገበሩት ፡ ወገን ፡ ተወላጅ ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ ሰዎች ፡ መሪዎቹ ፡ ወይም ፡ አለቆቹ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።[159] ስሙን ፡ ለጐሳው ፡ ትቶ ፡ የሄደው ፡ ይህ ፡ “የመካከለኛው ፡ አባይ ፡” ሰው ፡ አምር ፡ ይባ ላል ።[160]

እያንዳንዱ ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ቅርንጫፍ ፡ አለቃና ፡ ጐበዝ ፡ ሲኖሩት ፡ እንደፖለ ቲካ ፡ አቋም ፡ የሚገመት ፡ ነው ። ጐሳው ፡ የሚተዳደረው ፡ ዲግላል ፡ በሚባል ፡ አጠቃ ላይ ፡ አለቃ ፡ ሲሆን ፡ ሹመቱም ፡ በውርስ ፡ የሚተላለፍ ፡ ነው ።

የቢኒ ፡ አምርና ፡ የደንከሌ ፡ ጐሳዎች ፡ የፖለቲካ ፡ አቋም ፡ የተመሠረተው ፡ በኅ ብረ ፡ ሰብኡ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ “የገዢዎች ፡ ወገንና ፡” “የተገዢዎች ፡ ወገን ፡” በሚለው ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ ነው ። በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ መሪዎቹ ፡ ናብታብ ፡ ተብለው ፡ ሲጠሩ ፡ ተገዥዎቹ ፡ ደግሞ ፡ የገዥዎቹ ፡ “አረብ ፡” ይባላሉ ፤ ---“ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ንዴስና ፡ የዚህ ፡ ወይም ፡ የዚያ ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ክፍል ፡ (ንብረቶ ች) ተብለው ፡ ይጠራሉ ።”[161] በደንከል ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ ገዢዎቹ ፡ አሲማራ ፡ (ቀይ ፡ ሰዎች) ፤ ተገዢዎቹ ፡ አዶይማራ ፡ (ነጮች ፡) ይባላሉ ።

በቀላሉ ፡ ሊገመት ፡ እንደሚቻለው ፣ በሁለቱም ፡ ጐሳዎች ፡ ውስጥ ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ኡን ፡ የመምራቱ ፡ መብት ፡ የሚገኘው ፡ በገዢዎቹ ፡ እጅ ፡ ሲሆን ፣ በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፣ የአምር ፡ ተወላጆች ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ ነን ፤ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ የሚገም ቱት ፡ እነዚሁ ፡ መሪዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ በገዢና ፡ በተ ገዢ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ምርምር ፡ የሚያሻው ፡ ይመስላል።

ከላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ተገዢዎች ፡ የሚገመቱት ፡ እንደ ፡ አምር ፡ ተወላጆች ፡ ሳይሆን ፡ እንደየባለጠጋው ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ ሚች ፡ “---ትቶት ፡ (እንደሚሄደው ፡)--- ንብረት---” በመቆጠር ፡ ሊወረሱ ፡[162] ወይም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ የመጀመሪያ ፡ ወንድ ፡ ልጅዋን ፡ ስት ወልድ ፡ ከአያትየው ፡ እንደስጦታ ፡ ሊሰጡ ፡[163] ይችላሉ ። የተገዢዎች ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ በተገዢነት ፡ ሲቀሩ ፣ ሴቶቹ ፡ በጋብቻ ፡ ለየባሎቻቸው ፡ ገዢዎች ፡ ተገዢ ፡ በመሆን ፡ ይተላለፋሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ተገዢዎች ፡ ባሮች ፡ እንዳልሆኑ ፡ ይገነዘቧል ፤

---

156. ከዚያው ።
157. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፬ ።
158. ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፮ ።
159. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፱፻፷፭ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፰ ።
160. ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፱ ።
161. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፯ ።
162. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፱፻፷፭ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲፰ ።
163. ከዚያው ።

ስለዚህም ፡ እንደባሪያ ፡ ሊሸጡ ፡ አይችሉም ።[164] ባሮች ፡ የሚባሉት ፡ ይበልጡኑ ፡ የጦር ፡ ምርኮኞች ፡ ናቸው ።

ተገዢው ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ዓመታዊ ፡ ግብር ፡[165] ለጌታው ፡ እንዲሰጥና ፡ ጌታውም ፡ ልጅ ፡ ሲወልድ ፡ መታያ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይገደዳል ። ጌታውም ፡ በበኩሉ ፡ ተገዢውን ፡ 'እንደ ፡ አባት ፡'[166] በመሆን ፡ ተገቢውን ፡ መከባከብ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ይገደዳል ። ስለዚህ ፡ "--- በጌታና ፡ በተገዢ ፡ መካከል ፡ የሚገኙት ፡ የባህልና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም ፡ ልዩነቶች ፡ በሁለቱ ፡ መኻል ፡ ኑሮአቸውን ፡ የሚያለያዩ ፡ እንቅፋቶች ፡ ሆነው ፡ አይገኙም ። እንዲያውም ፡ ተገዢው ፡ የጌታውን ፡ መከባከብና ፡ ከውጭ፡ ጠላት ፡ መከላከል ፡ መፈለጉና ፤ የገዢው ፡ አገልግሎትም ፡ ለጌታው ፡ ማስፈለጉ ፡ ሁለቱ ፡ ተባብረው ፡ በአንድነት ፡ እንዲኖሩ ፡ ያደርጋቸዋል ።"[167]

## <u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤</u>

<u>የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ግላዊ ፡ መብት ፡-</u>

እንደሌላው ፡ ዘላን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፤ የሚበዙት ፡ የቤኒ ፡ አምርና ፡ የደንከል ፡ ሰዎች፡ ሲተላለፍ ፡ በመጣላቸው ፡ የጐሳ ፡ መሬት ፡ ድንበራቸው ፡ ውስጥ ፡ ግጦሽ ፡ በመፈለግ ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ በመዘዋወር ፡ ይኖራሉ ። የሚያረቡዋቸውም ፡ ግመሎች ፡ ፍየሎች ፤ በጐችና ፡ ሌሎች ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ናቸው ።[168]

በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ ጌታና ፡ ተገዢ ፡ በግጦሽ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ አንድ ፡ ነው ። "የተገዢው ፡ የግጦሽ ፡ መብት ፡ ሙሉና ፡ ፍጹምም ፡ ነው ፤ መብቱ ፡ የተገኘው ፡ ጐሳው ፡ ወይም ፡ ነገዱ ፡ በአንድ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ሀብታም ፡ ካለው ፡ መሠረታዊ ፡ የንብረት ፡ መብት ፡ አይደለም ።"[169]

በደንከል ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ በግጦሽ ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገዢዎች ፡ ወይም ፡ "አርነት ፡" የወጡ ፡ ተገዢዎች ብቻ ናቸው ። "ተገዥ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከብቶች ፡ ሊኖሩት ፡ ይችላል ፤ የሚያስማራበት ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ ባለቤት ፡ ግን ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። መሬትና ፡ ነፃነት ፡ የለሽ ፡ በመሆን ፡ ተገዢዎቹ ፡ ከጌቶቻቸው ፡ ጋር ፡ ከቦታ ፡ ወደቦታ ፡ በመዘዋወርና ፡ ለገዢው ፡ 'ክፍል ፡' ሁሉ ፡ በመገበር ፡ የግጦሽ ፡ መብት ፡ ያገኛሉ ።"[170] ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ተገዢ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ ቀበሌ፡ በሚገባበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ገዢዎቹን ፡ ማስፈቀድና ፡ "---ለሚቆይበትም ፡ ጊዜ ፡ ለፖለቲካ ፡ ሥልጣናቸው ፡ መገበር ፡ ይኖርበታል ።"[171]

ሰፍሮ ፡ የሚኖርን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመለከቱ ፡ ጥያቄዎች ፤ በተለይም ፡ የእርሻ ፡ መሬትን ፡ የሚመለከቱ ፡ እንደ ፡ ውርስ ፤ የመሬት ፡ ሽያጭና ፡ ዝውውር ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ከላይ ፡ ከመረመርናቸው ፡ በሁለቱ ፡ ዘላን ፡ ጐሳዎች ፡ ውስጥ ፡ ቦታ ፡ እንደሌላቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

---

164. ከዚያው ።
165. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፳፬ ።
166. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፳፫ ።
167. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፴፭ ።
168. ከቤኒ ፡ አምር ፡ ክፍሎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሰፍረው ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፬ ።
169. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፴፪ ።
170. ብሪትሽ ፡ ሚሊታሪ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፫ ።
171. ከዚያው ።

በቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ ውስጥ ፡ "ከብትን ፡ አብሮ ፡ ማጋጥ ፡" ያልተለመደ ፡ መሆኑን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መግለጥ ፡ ያስፈልጋል ። "በየቦታው ፡ እጅግ ፡ በመበታተንና ፡ እያንዳንዱም ፡ የየራሱን ፡ ፍላጐት ፡ ለማርካት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ ለመያዝ ፡ በመሽቀዳደም ፡ ስለሚኖሩ ፤ እነዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ በአንድ ፡ ሥልጣን ፡ ስር ፡ ሊተዳደሩ ፡ አይችሉም ። እንዲያውም ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ጐሳ ፡ እንኳ፡ ከብቶችን ፡ በአንድነት ፡ ለግጦሽ ፡ አያሰማራም ። የጐሳው ፡ ክፍሎችና ፡ ዘመድ ፡ አዝማዶች በጣም ፡ የተራራቀ ፡ ግጦሽ ፡ ሊመርጡ ፡ ይችላሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችና ፡ እረኞች ብቻቸውን ከቦታ ፡ ወደቦታ ፡ ይዘዋወራሉ ። "(አንክሮው የደራሲው ፡ ነው ፡)[172] በጦርነት ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ ካልተገናኙ ፡ በተቀር ፡ አንዱ ፡ የቤኒ ፡ አምር ፡ ክፍልፋይ ፡ ሌሎቹ ፡ የጐሳው ፡ ክፍልፋዮች ፡ የት ፡ እንዳሉ ፡ እንደማያውቅ ፡ ሚስተር ፡ ናዴል ፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ይገልጣሉ ።[173]

## ክፍል ፪ ፤

## የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የሕብረት ፡ ስለሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የወሰናቸው ፡ ድንጋጌዎች ፤

"ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ የሰዎችን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲሁም ፡ በመካከላቸው ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ መሠረታውያን ፡ ሐሳቦች ፡ ለመግለጽ ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፤ ሕጉ ፡ ከወጣላቸው ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ የሚደርስ ፡ ፍላጐታቸውን ፡ ልምዳቸውን ፡ ወይም ፡ የተፈጥሮ ፡ ፍትሕን ፡ የሚጠብቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

እኛ ፡ ያቋቋምነው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ይህን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ በተለይም ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንና ፡ ለተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ በማሰብ ፡ ነው ።"

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ መግቢያ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤

በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ የኅብረ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ታቅዶ ፡ የነበረውን ፡ የጥንቱን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ አስቀድመን ፡ በመመርመር ፤ በመጨረሻ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለሚያስነሳቸው ፡ አንዳንድ ፡ ከባድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ለመነጋገር ፡ አንባቢውን ፡ እናዘጋጃለን ።

### ምዕራፍ ፡ ፫ ፡

### ስለጥንቱ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፤

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ እርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ የሚመለከተው ፡ የጥንቱ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በአምስት ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ የተከፋፈሉ ፡ ዘጠና ፡ ሦስት ፡ ቁጥሮች ፡ ነበሩት ። ይህን ፡ ረቂቅ ፡[174] በሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ ንዑስ ፡ አርእስቶች ፡ መመርመር ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

---

172. ከዚያው ።

173. ናዴል ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፶፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፲ ። ደራሲው ፡ ደንከሎችን ፡ የሚመለከት ፡ ተመሳሳይ ፡ ግልጥ ፡ ያለ ፡ አነጋገር ፡ አላጋጠመውም ። የመሬት ፡ ስሪታቸውን ፡ ተመልክቶ ፤ የግጦሽ ፡ "አጠቃቀማቸው" ፡ የግል ፡ ነው ፤ ማለቱ ፡ ትክክል ፡ ይመስላል ።

174. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ።

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ረቂቁ ፡ ስላስፈለገበት ፤

በአርቃቂው ፡ አስተያየት ፡ ሊወጣ ፡ በታቀደው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍል ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ መጨመር ፡ "አስፈላጊ ፡" ነበር ። "በመሬት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ የግል፡ ስሪት ፡ ሀብታም ፡ በሆነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ተስፋፍቶ ፡ ቢገኝም ፤ ሰፊ ፡ ያለ ፡ የሀገሪቱ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ የጋርዮሽ ፡ ስሪት ፡ በሚመስል ፡ መልክ ፡ ስር ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሁኔታውንም ፡ ስንመለከት ፡ ይህን ፡ መሬት ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ስሪት ፡ መሠረት ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ማድረግ ፡ አለመቻሉ ፡ አያጠራጥርም ።"[175] (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።)

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ እንደገለጥነው ፡ ሁሉ ፤ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የሚመለከታቸው ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ ነበር ። "የመጀመሪያዎቹ ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ በማይከተሉ ፤ በከብት ፡ እርባታ ፡ በሚተዳደሩ ፡ የዘላን ፡ ጐሳዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ክፍሎች ፡ ነበሩ ። ሁለተኛዎቹ ፡ ደግሞ ፡ በየመንደሩ ፡ ሰፍረው ፡ የሚገኙ ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነበሩ ። በመካከላቸው ፡ ልዩነት ፡ ቢኖርም ፡ በዚህ ፡ (የሕጉ ፡) ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጨመሩ ፡ ያቀድናቸውን ፡ ደንቦች ፡ ስንመለከት ፡ ሁቱም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ በአንድ ፡ (የሕጉ ፡) ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ሊተዳደሩ ፡ የማይችሉ ፡ መስለው ፡ አልታዩንም ።"[176]

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ዓላማዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ---"(አንደኛ) በጊዜው ፡ የነበሩትን ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ነፃነት ፡ ለማክበር ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ዓላማ ፡ እናክላለን ፤ የየክፍሉን ፡ አባሎች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ግልጥ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የመወሰን ፡ ፍላጐት ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ዓላማ ፡ እናክልበት ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ክፍሎችና ፡ በአሠራራቸው ፡ ላይ ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ቁጥጥር ፡ እንዲኖረው ፡ በማድረግ አንዳንድ ፡ የሚታዩባቸውን ፡ በመብት ፡ በሚገባ ፡ አለመጠቀምን ፡ የማስወገድ ፡ ዓላማ። በሰነድ ፡ ቁጥር ፡ ፶፩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከቁጥር ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፺፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ስር ፡ ያቀረብነውን ፡ የቁጥጥር ፡ ዘዴ ፡ ከነዚህ ፡ ከሦስት ፡ ሀሳቦች ፡ በሚገባ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ።" [177]

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማ ፤ ከኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ በተለይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ መሠረታውያን ፡ ዓላማዎች ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንዲሄድ ፡ በማድረግ ፡ ባህልን ፡ እንዳለ ፡ ለማቆየት ፡ እንደነበረ ፡[178] እዚህ ፡ ላይ ፡ አጠንክሮ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ።

---

175. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ፡ (ትርጉም) ።
176. ከዚያው ፡ (ትርጉም) ።
177. ከዚያው ፡ (ትርጉም) ።
178. ከሚከተለው ፡ መግለጫ ፡ እንደምንረዳው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ከነበራቸው ፡ ጠቅላላ፡ አስተሳሰብ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ አይደለም ። "ተቀራኝታ ፡ የምታኖራቸውን ፡ አንዳንድ ፡ መሠረታውያን ፡ የሆኑ ፡ የልማድ ፡ ደንቦችን ፡ በመጠበቅ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የሕዝቧን ፡ የአኗኗር ፡ ዘዴ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ አድሚን ፡ በፍጹም ፡ መለወጥ ፡ ትፈልጋለች ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፤ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ በተጣራ ፡ አኳኋን ፡ የተዘጋጀ ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ቅንጅት ፡ እንዲሆን ፡ ኢትዮጵያ ፡ አትመኝም ። ይልቁንም ፡ የሕብረ ፡ ሰቡን ፡ ጠቅላላ ፡ ለውጥ ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ እቅድ ፡ የያዘ ፡ እንዲሆን ፡ ስለምትመኝ ፤ ከሕጉ ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ እንዲመሠረት ፡ ለምትመኘው ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ አቋም ፡ ተስማሚ ፡ የሆኑ ፡ ደንቦችን ፡ ያዘለ እንዲሆን ፡ ትፈልጋለች ።" ፡ አር ፡ ዳቪድ ፡ "ኤሲቢል ፡ ኮድ ፡ ፎር ፡ ኢትዮጵያ ፤ ኮንሲዴሬሽንስ ፡ አን ፡ ዘ ኮዲፊኬሽን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ሎ ፡ ኢን ፡ አፍሪካን ፡ ካንትሪስ ፡" ቱሌን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፤ ቮል ፡ ፴፯ ፡ (፲፱፻፷፫) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፫ ።

## <u>ንዑስ ፡ ክፍል ፤ ፪ ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ስላጠቃለላቸው ፡ ጉዳዮች ፤</u>

"የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ቻርተር ፡ (የመተዳደሪያ ፡ ደንብ፡)" የተሰኘው ፡ የረቂቁ ፡ የመጀመሪያው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ (ከቁጥር ፡ ፩—፲፯) "--- በኅብረት ፡ ማልማት ፡"[179] የተባለውን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ ይደነግጋል ።

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ቻርተሮች ፡ (መተዳደሪያ ፡ ደንቦች) ሊወጡ ፡ የሚችሉበትን ፡ ሁኔታ ፡ በማሰብ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነበር ፤ የመጀመሪያው ፡ ደንብ ፡ <u>ማንኛውም ፡</u> አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ አባል ፡ ጥያቄ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ የሚዘጋጅ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ነበር ።[180] ይህም ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ ይኖርበት ፡ ነበር ። ሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ደግሞ ፡ የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ የሚገኙበት ፡ ጠ/ግዛት ፡ እንደራሴ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለነዚሁ ፡ ክፍሎች ፡ የሚያድለው ፡ ነበር ።[181] ይህም ፡ እንዲደረግ ፡ ታቅዶ ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብዕ ፡ አባል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ጠይቆ ፡ ሌሎቹ ፡ አባሎች ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ ማስፈጸም ፡ ሲያቅታቸው ፡ ነው ። በጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ የታደለው ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በኅብረት ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ ሊሻሻል ፡ ሲችል ፤ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ እጅ ፡ ከገባ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ ነበረበት ።

የያንዳንዱ ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፤ በመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፩፻፺፩ ፡ ሥር ፡ የተጠቀሱትን ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ ማስፈር ፡ ነበረበት ።[182] እዚህ ፡ ላይ ፡ ልንጠቅስ ፡ የምንወደው ፡ "የመሬት ፡ ማልማት ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸምና ፡ የኅብረት ፡ አጠቃቀም ፡ ዘዴ ፡" የሚል ፡ ርእስ ፡ ተሰጥቶት ፡ የነበረውን ፡ የረቂቁን ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ መሬት ፡ "እንደተፈጥሮ ፡ ሀብቱና ፡ እንደ ፡ የዓይነቱ ፡" በጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚውልበትን ፤ ሌላውም ፡ የሕብረ፡ሰብኡ ፡ ንብረት ፡ ለጋራ፡ ጥቅም ፡ የሚመደብበትንና ፡ አባሎችም ፡ ሥራ ፡ የሚከፋፈሉበትን ፡ ዘዴ ፡ እያንዳንዱ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በግልጽ ፡ ማመልከት ፡ ነበረበት ።[183]

ሌላው ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ደግሞ ፡ "በንብረት ፡ በኅብረት ፡ ስለመጠቀም ፡" የሚል ፡ ርእስ ፡ ተሰጥቶት ፡ የነበረው ፡ ቁጥር ፡ ነው ። በዚህም ፡ ቁጥር ፡

---

179. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፩ ። ይህን ፡ ሐረግ ፡ በሚከተለው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ እንመረምረዋለን ።

180. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፫ ።

181. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፬ ።

182. <u>"ቁጥር ፡ ሺ፩፻፺፩ ፡ በመተዳደሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፈው ፡ ቃል ።</u>
የኅብረት ፡ መተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ጉዳዮች ፡ በተለይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።
ሀ/ በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ዘመዶች ፤
ለ/ ፡ የኅብረቱ ፡ መብት ፡ የሚዘረጋባቸውን ፡ መሬቶች ፤
ሐ/ ኅብረቱ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ አኳኋንና ፡ ለኅብረቱም ፡ ወኪል ፡ ለመሆን ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፤
መ/ የኅብረቱ ፡ መሬቶች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሀብቶች ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደሚሠሩና ፡ እንደሚከፋፈሉ፤
ሠ/ የኅብረቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በመሻሻል ፡ የሚለዋወጥበትን ፡ አኳኋን ፤"

183. የረቂቁን ፡ የፈረንሣይኛ ፡ አነጋገር ፡ ከዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የእንግሊዘኛው ፡ ትርጉም ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፷፰ ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።

መሠረት ፡ ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ የተመደበው ፡ ንብረት  በጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚውልበትን ፡ ዘዴ ፡ ከንብረቱም ፡ የሚገኘው ፡ ፍሬና ፡ ገቢ ፡ ለአባሎቹ ፡ እንዴትና ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚከፋፈል ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ መተዳደርያ ፡ ደንብ ፡ መግለጽ ፡ ነበረበት ።[184]

ቁጥር ፡ ፲፱፻፺፭ ፡ በመጨረሻ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ሲወጣ ፡ ከዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የተ ገደፉት ፡ ሁለት ፡ ቁጥሮች ፡ አዲስ ፡ አባሎችን ፡ መቀበልን ፡ ነባሮችን ፡ ማስወጣትንና፡[185] መጠባበቂያ ፡ መሬቶችን ፡ ለይቶ ፡ ማኖርን ፡[186] የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ።

ከሁለቱ ፡ ዓይነት ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ አንዱም ፡ ሳይኖር ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ ደንቡ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ ድንጋጌ ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ ሳይሆን ፡ ሲቀር ፡ ወይንም ፡ ሕግን ፡ የሚቃረኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይዞ ፡ ሲገኝ ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ እና፡ ተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ተደርጐ ፡ ነበር ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ልንገነዘበው ፡ የሚገባን ፡ ነገር ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲኖር ፡ የተመረጠበት ፡ ምክንያት ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያለውን ፡ ክፍል ፡ አባሎች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ በግልጽ ፡ ለመወሰን ፡ መሆኑንና ፡ ይህም ፡ የረቂቁ ፡ አንዱ ፡ ዓላማ ፡ እንደነበረ ፡ ነው ።[187]

"የኅብረተ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡" የተሰኘው ፡ የረቂቁ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ (ከቁ ጥር ፡ ፲፰-፴፯) ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ የቤተ ፡ ሰቦች ፡ ሃላፊዎች ፡ ወይም ፡ ወኪ ሎቻቸው ፡ (አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሱና ፡ ከተባለው ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ኃላፊ ፡ ጋር ፡ የሚ ኖሩ ፡ መሆን ፡ ነበረባቸው ፡) የሚገኙበትን ፡ ጉባኤ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ "ከፍተኛው ፡ ክ ፍል ፡" ያደርገዋል ።[188] ጉባኤው ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ኃላፊ ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ብዛት ፡ ከግምት ፡ ሳይገባ ፡ አንድ ፡ ድምፅ ፡ ብቻ ፡ እንዲሰጠው ፡ ታቅዶ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የግድ ፡ ሊከ ተሉት ፡ የሚገባ ፡ ደንብ ፡ አልነበረም ። ስለዚህም ፡ ከተፈለገ ፡ እድሜአቸው ፡ ከአስራ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የሆኑና ፡ "በኅብረቱ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ" የሆኑ ፡ አባሎች ፡ በሙሉ ፡ የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ እንዲሆኑ ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ለመደ ንገግ ፡ ይቻል ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ በደንቡ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ የጉባኤው አባል ፡ ለሆነ ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ በስሩ ፡ የሚተዳደረውን ፡ የሰው ፡ ብዛት ፡ በመገ መት ፡ በዛ ፡ ያለ ፡ የድምጽ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻል ፡ ነበር ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ "---በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ አንዳንድ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ ሲባል ፡ የተደነገጉ ፡ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች---"[189] እንዲከበሩ ፡ ተደርጐ ፡ ነበር ። በነዚህም ፡ መሠረት ፡ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ምክንያት ፡ በአባሎች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ እንዲደረግ ፡ አይፈቀድም

---

184. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፲፬ ። ረቂቁን ፡ ስንመለከተው ፡ በቁ ጥር ፡ ፲፱፻፺፭ ፡ (መ) ፡ ሥር ፡ የተጠቀሰው ፡ "ሌሎች ፡ ሀብቶች" ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ በእርሻ ፡ ላይ ፡ ያልዋሉ ፡ ወይም ፡ ሊውሉ ፡ የማይችሉ ፡ (ለምሳሌ ፡ ደኖችና ፡ ግጦሽ) ፡ መሬቶችን ፡ ከማመልከቱ ፡ በስ ተቀር ፡ ሌላ ፡ የሚጨምረው ፡ ሀብት ፡ ያለ ፡ አይመስልም ።

185. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፲፭ ።

186. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፲፮ ።

187. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፫ ።

188. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፲፰—፲፱ ።

189. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፫ ። እነዚህ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ ተሻ ሽሎ ፡ በወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ ፵ ፡ ፵፪ ፡ እና ፡ ፵፰ ፡ ውስጥ ፡ ተመ ልክተው ፡ ይገኛሉ ።

ነበር ።[190] ማንኛውም ፡ ቤተሰብ ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ እንዳይወከል ፡ ማድረግ ፤ ወይም ደግሞ ፡ ወኪሉን ፡ እንደየፍላጎቱ ፡ የመምረጥ ፡ መብቱን ፡ መንፈግ ፡ አይቻልም ፡ ነበር ።[191]

በጠቅላላው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፤[192] የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ከፍተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለሚከተሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ለመወያየት ፡ በያመቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በተወሰኑ ፡ ቀኖች ፡[193] መሰብሰብ ፡ ነበረበት ። እንዚህም ፡ ጉዳዮች ፡ የመተዳደሪያውን ፡ ደንብ ፡ ማሻሻል ፤[194] አዲስ ፡ አባሎችን ፡ መቀበል ፤[195] ነባር ፡ አባሎችን ፡ ማስወጣት ፤[196] የኅብረቱን ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ መሾም ፤ መሻር ፡ መቆጣጠርና ፡[197] ኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ከሌላ ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ጋር ፡ ማዋሐድ ፤ ኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ማከፋፈልና ፡ ማፍረስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።[198] ውሳኔም ፡ የሚሰጠው ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፤[199] ሲሆን ፡ ይህም ፡ ውሳኔ ፡ ሕግን ፡ ወይም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የሚቃረን ፡ ሲሆን ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጉዳዩን ፡ ለፍ/ቤት ፡ በማመልከት ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያቀርብበት ፡ ይችል ፡ ነበር ።[200] ተቀዋሚው ፡ ባቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔው ፡ እንዲሻር ፡ ጠይቆ ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊሽረው ፡ አለበለዚያም ፡ የፍ/ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለጊዜው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ሊያግደው ፡ ይችል ፡ ነበር ።[201]

የረቂቁ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ (ከቁጥር ፡ ፴፮ - ፵፰) ስለ ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ይደነግጋል ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ለተነሳንበት ፡ ዓላማ ፡ አግባብ ፡ ያለውና ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ክፍል ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ጥሩ ፡ መረጃ ፡ የሚሆነን ፡ ቁጥር ፡ ፴፮ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ በቁጥጥሩ ፡ ሥር ፡ ባለ ፡ መሬት ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ ንብረቶቹ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የማንኛውንም ፡ የግል ፡ ባለንብረት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመስሉ ፡ ናቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የተባለው ፡ ክፍል ፡ የኅብረት ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ ለመሸጥ ፤ ለማስተላለፍ ፤ በመያዣ ፡ ወይንም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ፡ ነበር ። እነዚህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ ከእርሻ ፡ ሚኒስትር ፡ ፈቃድ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነበር።[202] እንዲሁም ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ መሬቶቹን ፡ ለእርሻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሌላ ፡ በተግባር ፡ ከማዋሉ ፡ በፊት ፡ ተመሳሳይ ፡ ፈቃድ ፡ ከሚኒስትሩ ፡ ማግኘት ፡ ነበረበት ።[203]

---

190. ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፳፩ ፡ (፪) ።
191. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፪ ፡ (፪) ።
192. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፪ ፡ (፪) ። እነዚህ ፡ በአስቸኳይ ፡ ጊዜ ፡ የሚጸኑ ፤ ከጠቅላላው ፡ ሕግ ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ።
193. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፪ ፡ (፩) ።
194. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፫ ።
195. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፭ ።
196. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፮ ።
197. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፳፯ ።
198. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፴፩—፴፫ ።
199. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፴፬ ።
200. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፴፭ ።
201. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፴፮ ።
202. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፴፯ ።
203. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፴፱ ።

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ከተደረገው ፡ የመ ብት ፡ ጥበቃ ፡ ጐላ ፡ብሎ ፡ የሚታየው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባልም ፡ ሆነ ፡ ማንኛውም ፡ የውጪ ፡ ሰው ፤ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ በይዞታው ፡ ስር ፡ በማድረግ ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ መሬትን ፡ ባለሀብትነትን ፡ በይርጋ ፡ ለማግኘት ፡ አለመቻሉ ነው ።[204]

በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፤ በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ውል ፡ እንዲዋዋል ፤ እንዲከስ ፡ ወይም ፡ እንዲከሰስ ፡ መብት ፡ ነበረው ።[205] ሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውኑበት ፡ ወቅት ፡ ለሚያደርሱት ፡ ጥፋት ፡ ኅብ ረቱ ፡ ኃላፊ ፡ እንዲሆንም ፡ ግዴታ ፡ ነበረበት ።[206] ይህ ፡ ኃላፊነት ፡ ሊመነጭ ፡ የሚ ችለው ፡ ሠራተኞቹም ፡ ሆነ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በማድረጋቸው ፡ ወይም ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባውን ፡ ባለማድረጋቸው ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ለሚያስከትሉት ፡ የማይገባ ፡ ብልጽግና ፡ ሁሉ ፡ ኃላፊ ፡ ሆኖ ፡ የሚጠየቅ ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ነበር ።[207]

ከዚህ ፡ ልንረዳ ፡ እንደምንችለው ፤ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ሦስት ፡ መሠ ረታዊ ፡ ዓላማ ፡ "የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ጥቅም ፡ ጊዜ ፡ ጠብቀው ፡ ለማትረፍ ፡ ከማይመለሱ ፡ ሰዎች ፡ ለመከላከል ፡ ነበር ።"[208] ይህ ፡ ክፍል ፡ የሌሎችን ፡ አገሮች ፡ የአሠራር ፡ ልምድ ፡ በመከተል ፡ ከተውጣጡት ፡ የረቂቁ፡ ክፍሎች ፡ አንዱ ፡ ነበር ። "በ፲፱፻፴ ፡ ዓመተ ፡ ምሀረቱ ፡ የሶቭየት ፡ ሩሲያ ፡ የእርሻ ፡ ሕግ ፡ ለመመራት ፡ ይቻላል ፡ ተብሎ ፡ ከተገመተ ፡ በኋላ ፡ ይህንኑ ፡ ሕግ ፡ በመከተል፡ የተጻፈው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኮልኮዝ ፡ የተባሉት ፡ አቋሞች ፡ እየተስ ፋፉ ፡ ስለሄዱ ፤ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የሶቭየት ፡ ሕግ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ባለመዋሉ ፡ ከጥ ቅም ፡ ውጭ ፡ ሆኗል ።"[209]

የረቂቁ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፡ (ከቁጥር ፡ ፵፱—፹፪) የሚመለከተው ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያሉትን ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ አባሎች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ነበር ።

ማንኛውም ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ባገባ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ነበረው ።[210] አንድ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ መብት ፡ ይዞ ፡ የሚቆየው ፡ የኅብረቱን ፡ አባልነት ፡ ይዞ ፡ እስከ ኖረ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[211] ከአንድ ፡ አባል ፡ ላይ ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታው ፡ ሊ ወሰድበት ፡ የሚችለው ፡ ንብረቱ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲለቀቅ ፡ በሚደረግ በት ፡ ጊዜና ፡ ይህንንም ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፡ የወሰነው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ተሟልቶ ፡ ሲገኝ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[212]

---

204. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵ ።
205. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵፩ ። ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፬ ፡ (፩) ፡ ጋር ፡ ያነጻጽሯል ።
206. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵፯ ፡ (፩) ።
207. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፵፯ ፡ (፪) ፡ እና ፡ ፫ ። ከፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፬ ፡ (፫) ጋር ፡ ያነጻጽ ሯል ።
208. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፬ ፤ ትርጉም ።
209. ከዚያው ፤ ትርጉም ።
210. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፶፩ ።
211. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፫ ፡ (፩) ።
212. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፫ ፡ (፪) ። በረቂቁ ፡ ቁጥሮች ፡ ፶፩—፶፫ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደር ፡ ታቅዶ ፡ የነበረውን ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ መብት ፤ በዝርዝር ፡ ማብራሪያው ፡ ውስጥ ፡ "የመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ መብት" ፡ (ድሯ ፡ ዳቢታሲዮን) ፡ የሚል ፡ ስያሜ ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ። ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀ ሰው ፤ ገጽ ፡ ፬ ። ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፫፻፶፫ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፡ ቍጥሮች ፡ ጋር ፡ ያነ ጻጽሯል ። እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ "በቤት ፡ ውስጥ ፡ የመኖር ፡ መብትን" ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

ለእርሻው ፡ የሚውለው ፡ የጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ መሬት ፡ በማሳ ፡ በማሳ ፡ በመከፋፈል ፡ ለያንዳንዱ ፡ አባል ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ ወይንም ፡ እንዲሁ ፡ እንዳለ ፡ በተራድዖ ፡ ሊታረስ ፡ ይችል ፡ ነበር ። ካልሆነም ፡ ደግሞ ፡ ለአንዱ ፡ ዓይነት ፡ መሬት ፡ "አንድ ፡ ዓይነት ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፤" ለሌላው ፡ ደግሞ ፡ የተለየ ፡ ዘዴ ፡ ሊበጅለት ፡ ይችል ፡ ነበር ። አንድ ፡ አባል ፡ የግሉ ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ሊሰጠው ፡ የሚችለው ፡ ከዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ላላነሰ ፡ ወይም ፡ በጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ በሚወሰን ፡ ከዚህ ፡ ለሚረዝም ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።[213]

የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፶፯ ፡ የአባሎችን ፡ "የእኩልነት ፡ መብት ፡" ሲያረጋግጥ ፡ ይህ፡ መብት ፡ ለእርሻ ፡ የሚሆን ፡ መሬት ፡ በሚከፋፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንዲከበር ፡ ይደነግግ ፡ ነበር ።[214] የያንዳንዱም ፡ ሰው ፡ ድርሻ ፡ እኩልነት ፡ የሚወሰነው ፤ የመሬቱን ፡ ዓይነት ፤ አቀማመጥ ፤ ጠቃሚነት ፤ ባለይዞታው ፡ መሬቱን ፡ በሚያርስበት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ጥቅም ፡ በሚያውልበት ፡ ጊዜ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ በማመዛዘን ፡ ነበር ።[215] ሁኔታው ፡ እየታየ ፡ ለአንድ ፡ አባል ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ማሳዎች ፡ ሊመድቡለት ፡ ይችሉ ፡ ነበር ።[216]

በጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ ንብረት ፡ "እንዲገለገልበትና ፡ እንዲጠቀምበት ፡ የግል ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ አባል ፡ ሁሉ ፤ አንድ ፡ ባለሀብት ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ሊያደርግ ፡ የተፈቀደለትን ፡ ማንኛውንም ፡ የአጠቃቀምና ፡ የግልጋሎት ፡ ሥራ ፡ ሊያከናውንበት ፡ ይችል ፡ (ነበር) ። "[217] በዚህም ፡ መሠረት ፡ የግል ፡ ባለሀብቶች ፡ ተጠያቂ ፡ ለሚሆኑበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ የጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባልም ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆን ፡ ነበር ።

አንድ ፡ አባል ፡ በራሱ ፡ ጥረት ፡ ዘርቶ ፡ ያመረተው ፡ ሰብል ፡ ፍጹም ፡ ባለንብረት ፡ እንዲሆን ፡ ታቅዶም ፡ ነበር ። ይህም ፡ የሚሆነው ፤ አባል ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ከምርቱ ፡ ከፍሎ ፡ ከሚሰ ፡ የማይበልጠውን ፡ በዋጋ ፡ ወይም፡ በችሮታ ፡ መልክ ፡ ለጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ ሊሰጥ ፡ አልተስማማ ፡ እንደሆነ ፡ ነበር ።[218]

የጎብረተ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ መሬትን ፡ በተራድዖ ፡ ለማረስ ፡ ወስኖ ፡ እንደሆነ ፤ የያንዳንዱን ፡ አባል ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ በግልጽ ፡ እንዲወስን ፡ ይገደድ ፡ ነበር ።[219] የተባለው ፡ ስብሰባ ፡ "---መሬትን ፡ በተራድዖ ፡ በማረስ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው፡ጥቅም፡በተቻለ፡መጠን፡ የየአባሉን ፡ መብት፡የሚያከብር፡እንዲሆን ፡ መደረግ ፡ ነበረበት ።"[220] መገንዘብ ፡ የሚኖርብን ፡ የመሬት ፡ አስተራረሱ ፡ ዘዴ ፡ እንዲወሰን ፡ ታቅዶ ፡ የነበረው ፡ በጎብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ እንደነበረ ፡ ነው ።

በተራድዖ ፡ ከታረሰ ፡ መሬት ፡ የሚገኘው ፡ ምርት ፤ በአባሎቹ ፡ መካከል ፡ የሚከፋፈለው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ። በመጀመሪያ ፤ ከግማሽ ፡ ሊበልጥ ፡ የማይችል ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ የምርቱ ፡ ክፍያ ፡ ለእርሻው ፡ ሥራ ፡ (ለምሳሌ ፡ ለእርሻ ፡ መሣሪያ ች ፡ መግዣ ፡) እና ፡ ለጎብረ ፡ ሰብኡም ፡ ተግባርን ፡ ማከናወኛ ፡ (ለምሳሌ ፡ የሥራ ፡

---

213. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፫ ።
214. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፬ ፡ (፪) ።
215. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፯ ።
216. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፶፱ ።
217. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷ ።
218. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷፪ ፡ እና ፡ ፷፫ ።
219. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷፬ ፡ (፩) ።
220. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፷፭ ፡ (፫) ።

አስኪያጆች ፡ ደመወዝ ፡ ለመክፈል ፡) የወጣውን ፡ ወጪ ፡ ለመሸፈን ፡ ለኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ይመደባል ።[221] ከዚህ ፡ የተረፈው ፡ ምርት ፡ በእርሻው ፡ ተከፋይ ፡ ለሆኑት ፡ አባሎች ፡ ይከፋፈላል ። የየአባሉም ፡ ድርሻ ፡ የሚወሰነው ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ በሚመዝን ፡ ዘዴ ፡ ወይም ፡ ካልተቻለ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ አባል ፡ በእርሻው ፡ ተካፋይ ፡ የሆነበትን ፡ ጊዜ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነበር ።[222] ሕብረ ፡ ሰብኡ ፡ ምርቱን ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ሲሸጥ ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜም ፤ እያንዳንዱ ፡ አባል ፡ ከሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ተገቢ ፡ ድርሻውን ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ።

የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ "መሬትን ፡ በተራድዖ ፡ ስለማረስ ፡" የተሰኘውን ፡ ደንብ ፡ ባረቀቁበት ፡ ጊዜ ፡ የ "ኮሎክዝ ፡ ሕግ ፡" የተባለውን ፡ የሩሲያን ፡ ሕግ ፡ መመሪያ ፡ አድርገው ፡ ተጠቅመውበት ፡ እንደነበረ ፡ ይናገራሉ ።[223]

የንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮችን ፡ ይመለከታሉ ። አንደኛው ፤ የኅብረቱ ፡ አባሎች ፡ ባንድ ፡ ለማንም ፡ ባልተሰጠ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ስላላቸው ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ነው ። መሠረታዊው ፡ ሕግ ፤ ማንኛውም ፡ አባል ፡ ቢሆን ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የመጠቀምና ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ አለው ፡ የሚለው ፡ ነው ።[224] በዚህም ፡ መሠረት ፤ ልማድ ፤ የመንግሥት ፡ ሕግና ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ደንቦች ፡ በሚፈቅዱት ፡ መሠረት ፡ ማንኛውም ፡ አባል ፡ ለግጦሽ ፡ በተመደበው ፡ የኅብረቱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ከብቶቹን ፡ ሊያሰማራ ፡ ከሚካውም ፡ ሥፍራ ፡ ለማገዶ ፡ የሚሆን ፡ እንጨት ፡ ሊለቅም ፡ መብት ፡ ነበረው ።[225] በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ከሚሠማሩት ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ከሚገኘው ፡ ቆዳ ፡ ከሩብ ፡ የማይበልጠውን ፡ ያህል ፡ የመካፈል ፡ መብት ፡ ሊኖረው ፡ ይችል ፡ ነበር ።

ሁለተኛው ፡ ይህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ በኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ጠቅላላ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያሏቸውን ፡ መብቶች ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ መብቶች ፡ የግል ፡ ነበሩ ፤ ማለትም ፤ የተሰጡት ፡ ለያንዳንዱ ፡ አባልና፡ አብረውትም ፡ ለሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[226] ሊሸጡ ፡ ወይም ፡ በመያዣነት ፡ ሊሰጡ ፡ አይችሉም ፤[227] ባለመብቶቹ ፡ የሞቱ ፡ እንደሆነ ፡ መብታቸው ፡ ከመሞታቸው ፡ በፊት ፡ አብረዋቸው ፡ ይኖሩ ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ይተላለፋሉ ፤[228] እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በሌሉ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ መብቶቹ ፡ ለማህበሩ ፡ ተመላሽ ፡ እንዲሆኑ ፡ ታቅዶ ፡ ነበር ።[229]

የመጨረሻ ፡ የሆነው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ (ከቁጥር ፡ ፹፫—፺፫) የሚመለከተው ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ቁጥጥር ፡ ነበር ። በያንዳንዱ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእ

221. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፳፫ ።
222. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፳፯ ።
223. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፵፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫—፰ ።
224. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፳፱ ።
225. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፴ ፡ እና ፡ ፴፩ ።
226. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፴፫ ።
227. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፴፬ ።
228. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፴፭ ፡ እና ፡ ፴፯ ።
229. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፴፯ ።

ርሻ ፡ መሬቶች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንዲከፈት ፡ እና ፡ ይህም ፡ ጽ/ቤት ፡ ከጠ/ ግዛቱ ፡ አስተዳደር ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ ነበር ። በየቦታው ፡ የሚገኙ ትን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶችን ፡ ለመምራትና ፡ ለማስተባበር ፡ አንድ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ክፍል ፡ በእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ሊቋቋም ፡ ታቅዶም ፡ ነበር ።[230]

የያንዳንዱ ፡ ጽ/ቤትም ፡ ተግባር ፡ በጠ/ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የኅብረት የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ መኖር ፡ ማረጋገጥና ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡም ፡ የልማት ፡ ሥራ ውን ፡ የሚያሻሽልበትን ፡ ዘዴ ፡ በመፈለግ ፡ መርዳት ፡ ነበር ።[231] በተጨማሪም ፡ ኅብረ ሰብኡ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ማግኘቱን ፡ ማረጋገጥ ፡ የነዚሁ ፡ ጽ/ቤቶች ፡ ተቀዳሚ ፡ ተግባር ፡ ነበር ።[232] አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ እንዲዘጋጅ ፡ ከጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባው ፡ በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ጊዜ ፡ አዘጋጅቶ ፡ መስጠት ፡ የተሳነው ፡ እንደሆነ ፤ ወይንም ፡ ኅብረቱ ፡ ደንብ ፡ እንዲ ሰጠው ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፤ ጽ/ቤቱ ፡ ጥያቄውን ፡ በመቀበል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተደንግጎ ፡ ነበር ። ይህም ፡ የሚሰጠው ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ የተዘጋጀ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[233]

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎችን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶቹ ፡ የሚቆጣጠሩት ፡ በጠቅላላ ፡ ስብሰባቸው ፡ በኩል ፡ ነበር። ተመልካች ፡ ለመላክ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፤ እያንዳንዱ ፡ ጽ/ቤት ፡ ጉባዔ ፡ ከመደረጉ ፡ አስቀድሞ ፡ ጉዳዩን ፡ እንዲ ያውቅ ፡ መደረግ ፡ ነበረበት ።[234] በተጨማሪም ፡ ጉባዔው ፡ ተሰብስቦ ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጠ በት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እስከሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ውሳኔውን ፡ ለጽ/ ቤቱ ፡ ማስታወቅ ፡ ነበረበት ። ይህም ፡ የሚደረገው ፡ ውሳኔው ፡ ለጽ/ቤቱ ፡ ይተላለ ፋል ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ ሲኖር ፡ ነው ።[235] ውሳኔው ፡ ሕግን ፡ ወይም ፡ ደንብን ፡ የሚፃ ረር ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፤ ጽ/ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ፍ/ቤት ፡ በመውሰድ ፡ መቃወሚያ ፡ የማቅ ረብ ፡ መብት ፡ ነበረው ።[236]

በመጨረሻም ፤ የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሕግን ፡ ሳይተላለፍ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእ ርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ ክፍሎች ፡ በሚገባ ፡ ለመቆጣጠር ፡ የሚያስችሉ ፡ ብሎ ፡ የሚገምታቸውን ፡ ደንቦችና ፡ እርምጃዎች ፡ በማዘጋጀት ፡ ለጽ/ቤቶቹ ፡ ለማስተላለፍ፡ አስፈላጊው ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ።[237]

## ክፍል ፡ ፫ ፤ ረቂቁ ፡ ስለምን ፡ ተቀባይ ፡ እንዳጣ ፤[238]

በመሠረቱ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ሳይቀበል ፡ የቀረ በት ፡ ምክንያት ፡ ሕዝቡ ፡ ሳያስበው ፡ የቀድሞ ፡ ልማዱን ፡ በፍጹም ፡ እርግፍ ፡ አድ

---

230. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፻፫ ።
231. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፻፬ ፡ (፪) ።
232. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፻፯ ።
233. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፻፯ ፡ እና ፡ ፻፰ ።
234. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፻፱ ።
235. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፺ ።
236. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፺፩ ።
237. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፺፪ ። ቍጥር ፡ ፺፫ ፡ ቅጣትን ፡ የሚወስን ፡ ነው ። ለጽ/ቤቱ ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚገባውን ፡ በረቂቁ ፡ የተመለከተውን ፡ ጉዳይ ፡ ሳያስታውቁ ፡ የሚቀሩ ፡ ዲሬክተሮች ፡ በወንጀለኛነት ፡ ይቀጣሉ ፤ ሲል ፡ ቍጥር ፡ ፺፫ ፡ ይደነግጋል ።
238. የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ያልተቀበለበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚያስረዳ ፡ ሰነድ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም ። የመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ መክ ፈቻ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ፤ "የሚከተለው ፡ ድንጋጌ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥ ር ፡ ፺፩ ፡ ፈንታ ፡ የሚተካ ፡ ነው ።" ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የመጀመሪያው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ፡ የምናመለክተው ፡ ሁሉ ፡ ከቃል ፡ ጥያቄ ፡ በተሰበሰበ ፡ መረጃ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

ርጐ ፡ እንዲተው ፡ የሚያደርግ ፡ መስሎ ፡ ስለታየው ፡ ነበር ። ረቂቁ ፡ ይህን ፡ ስሜት ፡ ሊፈጥር ፡ የቻለበት ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳይ ፡ ያዘለና ፡ በጣም ፡ ረጅም ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በጉባዔው ፡ ዘንድ ፡ የነበረው ፡ ስጋት ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የሚመለከታቸው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ የረቂቁን ፡ ዓላማ ፡ ለመረዳትና ፡ አዳዲሶቹን ፡ ሀሳቦችም ፡ ለመቀበል ፡ አይችሉ ፡ ይሆናል ፡ የሚለው ፡ ነበር ። ሕጉ ፡ ከመዘጋጀቱ ፡ በፊት ፡ የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ውሳኔ ፡ በሚያስተላልፉበት ፡ ጊዜ ፡ ይጠቀሙበት ፡ የነበረውን ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዓት ፡ በፍጹም ፡ እንዲለውጡ ፡ የሚያደርጓቸውን ፡ ስለ ፡ "ጉባዔ ፡" እና ፡ ስለ ፡ "እኩልነት" የተረቀቁትን ፡ ቁጥሮች ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደመረጃ ፡ መጥቀስ ፡ ይቻላል ። በልማድ ፡ መሠረት ፡ ጥቂት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተሰብስበው ፡ በመግባባት ፡ ውሳኔ ፡ እንደሚያስተላልፉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ውሳኔ ፡ በሚያስተላልፉበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፤ "አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ድምጽ ፡ ይኖረዋል ፡" ወይም ፡ "በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ይወሰናል ፡" በሚሉት ፡ መመሪት ፡ አለባቸው ፡ ብሎ ፡ ማወጅ ፤ ለተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ልማድም ፡ ሆነ ፡ ባህል ፡ ፍጹም ፡ እንግዳና ፡ ባዕድ ፡ ይሆናል ፤ የሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ሳይኖር ፡ አልቀረም ። ባጭሩ ፤ እንዲገለገልበት ፡ የታቀደው ፡ ሕዝብ ፡ ከረቂቁ ፡ እጅግ ፡ ወደኋላ ፡ የቀረ መስሎ ፡ ስለታየ ፤ ረቂቁ ፡ ተቀባይ ፡ ሳያገኝ ፡ ቀርቷል ።[239] ረቂቁ ፡ ተቀባይ ፡ እንዳያገኝ ፡ ሊያደርጉ ፡ የሚችሉ ፡ ሌሎች ፡ ምክንያቶችም ፡ አይጠፉም ።

በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፤ በያንዳንዱ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ሊቋቋሙ ፡ ታስበው፡ የነበሩትን ፡ ጽ/ቤቶች ፡ ማቋቋም ፡ ከባድ ፡ ወጪ ፡ ያስከትላል ፤ የሚል ፡ ፍርሐትም ፡ ኖሮ ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ መንግሥት ፡ አስፈላጊውን ፡ ገንዘብና ፡ የሰው ፡ ኃይል ፡ ለማቅረብ ፡ አልተዘጋጀ ፡ ይሆናል ።

ጉዳዩ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ ክፍሎች ፡ ብዙዎቹ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦቻቸውን ፡ ለመደንገግ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ሊወስድባቸው ፡ ስለሚችል ፤ ረቂቁ ፡ በተለይም ፡ ከክፍል ፡ ፪-፫ ፡ ያሉት ፤ ሳይታሰቡ ፡ በድንገት ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸው ፡ አይቀርም፤ የሚል ፡ ሌላ ፡ ፍርሃትም ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ፍርሃት ፤ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ በቂ ፡ ጊዜና ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ ጉልህ ፡ የሆኑ ፡ ከልማድ ፡ የራቁ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ከማዘሉ ፡ የሚመነጭ ፡ ነው ።

የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እግብ ፡ ሊያደርስ ፡ ያቀዳቸው ፡ ሁለት ፡ ዓላማዎችን ፡ መሆኑን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ፤ አንደኛ ፡ የልማድን ፡ ጉድለቶችን ፡ ሊያሟላ ፡ ሲሆን ፤ ቀደም ፡ ሲል ፡ እንደተገለጠው ፤ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በመመሪት ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ማሟያ ፡ እንዲሆኑ ፡ የታቀዱት ፡ ደንቦች ፡ ሊለወጡ ፡ ወይም ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዳይኖራቸው ፡ ሊደረጉ ፡ የማይችሉ ፤ ማንኛውም ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ሊያከብራቸው ፡ የሚገባ ፡ ነበሩ ። ሁለተኛም ፤ የራሳቸውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ለመደንገግ ፡ ለማይችሉ ፡ ማህበሮች ፡ ረቂቁ ፡ እንደመሸጋገሪያ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ እንዲችል ፡ ሆኖ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ረቂቁን ፡ ላለመቀበል ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ይሆናሉ ፤ ብሎ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ አያምንም ። እንዲያውም ፡ ረቂቁን ፡ ባለመቀበሉ ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ብልህ ፡ ከመሆን ፡ የራቀ ፡ መስሎ፡

239. ለክቡር ፡ አፈንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ ከቀረበ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተገኘ ። ክቡርነታቸው ፡ የፍትሐ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ አባል ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፤ የምክር ፡ ቤቶቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ላይ፡ ይነጋገሩ ፡ በነበሩበት ፡ ወቅት ፡ የሥራው ፡ ኃላፊ ፡ በመሆን ፡ ተገኝተው ፡ ነበር ።

ታይቶታል ። የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዲያስወግዳቸው ፡ የታቀዱትን ፡ ችግሮች ፡ ስንገምት ፣ ረቂቁ ፡ መጠነኛ ፡ ማሻሻያ ፡ ተደርጐበት ፡ ሊቀበሉት ፡ የሚቻል ፡ ይመስለናል ። ይህ ንንም ፡ የምንለው ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ምክንያቶችን ፡ ተመርኩዘን ፡ ነው ።

የመጀመሪያው ፡ የተመሠረተው ፡ በረቂቁ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ። ይህ ፡ ረቂቅ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ አቀነባብሮ ፡ እንዲይዝ ፡ የታቀደ ፡ ሲሆን ፣ በእር ግጥም ፡ እነዚህን ፡ የያዘ ፡ ነበር ። ለረቂቁ ፡ መነሻ ፣ መመሪያና ፡ የሀሳብ ፡ ምንጭ ፡ የሆ ኑት ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ የኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ነበሩ ። በመሠረቱ ፡ አርቃቂው ፡ ያበረከቱት ፡ አገልግሎት ፡ እነዚ ህን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ማቀነባበርንና ፡ የዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ መልክ ፡ ማስያዝን ፡ የሚ መለከት ፡ ነበር ። ቀደም ፡ ብለን ፡ እንዳመለከትነውም ፣ እነዚህን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጐች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ ሲባል ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ አንዳንድ ፡ ለውጦ ችን ፡ አድርጓል ። በዚህ ፡ ረገድም ፡ ቢሆን ፡ ረቂቁ ፡ አዲስ ፡ የሆኑ ፡ ሀሳቦችን ፡ አመጣ ፣ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ምክንያቱም ፡ ረቂቁ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋላቸው ፣ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በታወጀው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ የነበ ሩትን ፡ መሠረተ ፡ አሳቦች ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ስለዚህም ፡ ከሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ ልማድን ፡ የተከተለ ፡ ስለነበረ ፣ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በተሰማራው ፣ ባብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ በቀላሉ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኝ ፡ ነበረ ፡ ማለት ፡ ይቻላል ። ዘላን ፡ በሆነው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድም ፡ እንዲሁ ፡ ተቀባይነት ፡ ባላጣ ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ ከሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ደንቦች ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ እጅግ ፡ የተወሰኑ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። የረቂቁ ፡ የሚ በልጠው ፡ ክፍል ፣ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ የሚተዳደሩ ፡ ሰዎችን ፡ የሚመለከት ፡ ስለሆነ ፡ በከብት ፡ እርባታ ፡ ሥራ ፡ በሚተዳደሩ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚፈጠረውን ፡ አለመግ ባባት ፡ ለማስወገድ ፡ እምብዛም ፡ የሚረዳ ፡ አልነበረም ። እነዚህን ፡ የኋለኞችን ፡ሰዎ ች ፡ የሚመለከቱት ፡ የረቂቁ ፡ ደንቦች ፡ (ለምሳሌ ፤ ስለሣር ፡ የተደነገጉት፡) ማንኛውም ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ ሕዝብ ፡ ሊቀበላቸው ፡ የማይችሉ ፡ አልነበሩም ።

ዳግመኛም ፣ በሕጉ ፡ ሥር ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ታቅደው ፡ የነበሩት ፡ የኀብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ "አዲሱን ፡" የኑሮ ፡ ዘዴ ፡ እንዲቀበሉትና ፡ እንዲላመዱት ፡ ለማድረግ ፡ በተለይ ፡ የታቀዱ ፡ ዘዴዎች ፡ በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ ይገኙ ፡ ነበር ።

ከነዚህም ፡ ዘዴዎች ፡ አንዱ ፡ በቁጥር ፡ ፯ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ። አንድ ፡ አባል ፡ የመተዳደሪያ ፤ ደንብ ፡ በሚጠይቅበት ፡ ጊዜ ፡ ማህበሩ ፡ ይህንኑ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ተሰጥቶትታል ። እጅግ ፡ "ባሕል ፡ አክባሪ ፡" ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጥያቄ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታትም ፡ ላይቀርብ ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ማህበር ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቡን ፡ ለመደንገግ ፡ ከቻለ ፡ ደግሞ ፣ ደንቡ ፡ በሥራ ፡ ላይ፡ የሚውለው ፡ ማህበሩ ፡ "በቂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በገመተው"[240] ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ።

ሌላው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፣ የኀብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚሰጠውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ለማጥናት ፡ አግባብ ፡ ላላቸው ፡ ክፍሎች ፡ በቁ ጥር ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ "የማለማመጃ ፡" ጊዜዎች ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ ባይገኙ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጥ ፡ በማድረግ ፡ ረቂቁን ፡ ማሻሻል ፡ ይቻል ፡ ነበር ።

---

240. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፬ ።

በተጨማሪም ፡ የገንዘቡና ፡ የሰው ፡ ኃይሉ ፡ ጉዳይ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ሊሰ ጠው ፡ ባልተገባም ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ጽ/ቤቶች ፡ ማቋቋም ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ አልነበረም ። የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ ባለ ማውጣቱ ፡ ወይም ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተባለ ውን ፡ ደንብ ፡ ባለመስጠቱ ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ሳይኖረው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዲተዳደር ፡ ተወስኖ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ ጽ/ቤቱን ፡ የሚመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ ተሠርዘው ፤ የደንቦች ፡ ምንጭ ፡ ተደ ፈነ ፡ የሚል ፡ ፍርሃት ፡ ለጊዜው ፡ ሳይፈጠር ፡ ረቂቁን ፡ ለመቀበል ፡ ይቻል ፡ ነበር ።[241]

ረቂቁ ፡ በጉባኤው ፡ ዘንድ ፡ ሙሉ ፡ ተቀባይነት ፡ ሊያገኝ ፡ ያልቻለበት ፡ ምክን ያት ፡ ምናልባት ፡ አርቃቂው ፡ በፈረንሣይና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ ሲጠቀሙ ፡ ግልጽ ፡ ባልሆነ ፡ አገባብ ፡ በመሆኑና ፡ በቃላቱም ፡ መካከል ፡ አለመስማማት ፡ የሚ ታይ ፡ በመምሰሉ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ለምሳሌ ፡ ከረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፩ (ማለት ፡ ከፍ ትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፮፻፸፱ ፡ ጋር ፡ ከሚመሳሰለው ፡ ቁጥር) አንድ ፡ ሰው ፡ ሊረዳ ፡ የሚችለው ፤ መመሪያ ፡ የሚሰጥ ፡ አንድ ፡ ማዕከላዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያለበት ፡ የመስኮቦችን ፡ ኮልኮዝ ፡ የመሰለ ፡ የተራድዖ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ እንዲጀመር ፡ መታቀ ዱን ፡ ነው ።[242] አለፍ ፡ ይልና ፡ ደግሞ ፡ "በኅብረት፡ (በተራድዖ፡) ማልማትን ፡" ወይንም፡ ደግሞ ፡ "በግል ፡ ማልማት"ን ፡ የሚፈቅደው ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥር ፡ ፺፩ ፡ ይገኛል ። እን ግዲህ ፡ ቁጥር ፡ ፺፩ ፡ የቊጥር ፡ ፩ን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የሚቃረን ፡ መምሰሉ ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ምናልባትም ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረው ፤ ይህ ፡ በረቂቁ ፡ ቁጥሮች ፡ መካከል ፡ የሚታየው ፡ አለመግባባት ፡ የረቂቁን፡ ዓላማ ፡ በግልጽ ፡ ለማየት ፡ እንዳይችል ፡ ስላደረገው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ኮሚሲዮኑ ፡ ረቂቁን ፡ ሳይቀበል ፡ የቀረበት ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ፡ምክንያት ፡ ኖሮት፡ቢሆ ንም ፡ የረቂቁ ፡ ተቀባይ ፡ ማጣት ፡ ያልታሰበ ፡ ውጤት ፡ ያስከተለ ፡ ይመስላል ። በመጀመ ሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ሳይረዱ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፮፻፸፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ለማስተዳደር ፡ እንደታቀዱ ፡ ማወቁ ፡ በጣም ፡ አዳጋች ፡ ነው።

ጊዜ ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፤ ሕጉ ፡ የሚመለከታቸውም ፡ ክፍሎች ፡ የቁጥር ፡ ሺ፮፻፸፱ እና ፡ የሚከተሉትንም ፡ ቁጥሮች ፡ ዓላማ ፡ ሲረዱ ፤ ረቂቁን ፡ ተመልሶ ፡ ማየት ፡ አስፈ ላጊ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ። ይልቁንም ፡ ረቂቁ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፮፻፸፱እና፡ በሚከተሉት ፡ መሠረት ፡ ሊወጣ ፡ የታቀደው ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ጥሩ ፡ ሞዴል ፡ ሊሆን ፡ ስለሚችል ፤ ዓላማዎቹን ፡ ባጭሩ ፡ ቀጥሎ ፡ ማመልከት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

ከሕጉ ፡ "የረቀቀውን ፡" ክፍል ፡ ወደጐን ፡ ስንተወው ፤ ዓላማው ፡ እንደሚከተ ለው ፡ ይሆናል ። ማንኛውም ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያለው ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፤ የአባሎቹን ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመለከቱትን ፡ የራሱን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መልክ ፡ እንዲያወጣ ፡ ማድረግ ፤ ይህንን ም ፡ በሚያደርግበት ፡ ወቅት ፡ እስነዋሪ ፤ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ለእድገት ፡ ይጠቅማሉ ፡ ከሚባሉ ፡ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች ፡ ጋር ፡ የማይስማሙና ፡

241. ሌላው ፡ ምርጫ ፡ ደግሞ ፡ ረቂቁን ፡ ተቀብሎ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ማድረጉ ፡ ነበር ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ማስመዝገብን ፡ የሚመለከተውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ አንቀጽ ፡ ዐሥርን ፡ ያገደውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፷፫ን ፡ ይመለከቷል ።

242. ወደፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ ሁሉ ፤ በመጨረሻውም ፡ ሆነ ፡ በመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ "የኅብ ረት ፡ ሥራ ፡" ለሚለው ፡ ሐረግ ፡ ይህ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉሙ ፡ አይደለም ።

ተገቢ ፡ ያልሆኑትን ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ ለማስቀረት ፡ የታቀዱትን ፡ ግዳጅነት ፡ ያላቸ ውን ፡ ደንቦች ፡ ማክበር ፡ ይኖርበታል ።

የተባለው ፡ ክፍል ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ ለማውጣት ፡ የቻለ ፡ እንደሆነ ፡ (ቀደም ፡ ስንል ፡ የመረመርናቸው ፡ በእርሻ ፡ የሚተዳደሩት ፡ ክፍሎች ፡ በቀላሉ ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚችሉት ፡ ነው ።) ዘመናዊነት ፡ ጐላ ፡ ብሎ ፡ የሚታይባቸው ፤ በተለይም ፡ ጉባዔ ዎችንና ፡ የተራድዖ ፡ እርሻን ፡ ከሚመለከቱት ፡ የረቂቁ ፡ ቁጥሮች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ተፈ ጻሚነት ፡ አይኖራቸውም ። በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ ከንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪—፬ ፡ ያሉትም ፡ ተፈጻ ሚነት ፡ የሚኖራቸው ፡ የመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ አከራካሪ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ስለአ ንድ ፡ ጉዳይ ፡ ድንጋጌ ፡ ሳይኖረው ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ የተደነገገው ፡ ቁጥር ፡ ሕግን ፡ የሚቃረን ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ብቻ ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ የኅብረ ፡ ሰብአ ፡ ክፍል ፡ የራ ሱን ፡ ደንብ ፡ ሳያወጣ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ረቂቁ ፡ እንደጊዜያዊ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በመሆን ፡ ተፈጻሚነት ፡ ይኖረዋል ።

አንድ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ክፍል ፡ መሬቱን ፡ በኅብረት ፡ ለማልማት ፡ ቢሻ ፡ ነፃ ነት ፡ አለው ።[243] ማንኛውም ፡ ክፍል ፡ ቢሆን ፡ መሬቶችን ፡ በኅብረት ፡ (በተራድዖ) ፡ እንዲያለማ ፡ አይገደድም ። እንዲያውም ፡ መሬቶችን ፡ ሸንሽኖ ፡ ለአባሎቹ ፡ በማከፋ ፈል ፡ በግል ፡ እንዲለሙ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ። በመጨረሻም ፤ መሬቶችን ፡ በበለጠ፡ ለማልማት ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ እርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ የኅብረ ፡ ሰብአ ፡ ክፍል ፡ "ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡" በሚሠራ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ ይሆ ናል ። ይህ ፡ ጽ/ቤት ፡ የተባለው ፡ ክፍል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ማግኘቱን ፡ ለማረጋ ገጥ ፡ የተለየ ፡ ኃላፊነት ፡ ይጣልበታል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ስለታወጀው ፡ የመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡-

### ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለአቀማመጡ ፤

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ እርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ ክፍሎች ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፱—ሺ፭፻ ፤ የሚገኙት ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ "በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በኅብረት ፡ ስለመጠቀም ፡" በሚለው ፡ በአ ንቀጽ ፡ ፱ ፡ ሥር ፡ ነው ። ስለነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ ከተደነገገው ፡ ምዕራፍ ፡ ቀደም ፡ ብሎ፡ ስለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረትና ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ሀብ ቶች ፡ ስለማስለቀቅ ፡ የሚወስኑ ፡ ምዕራፎች ፡ ይገኛሉ ። ከተባለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተከታ ታይነት ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ሁለት ፡ "በኅብረት ፡ የመጠቀም ፡" ዘዴዎችን ፡ የሚመለከ ቱ ፡ ሁለት ፡ ምዕራፎች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህም ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ሥር ፡ የሚገኘው ፡ "በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡" እና ፡ በምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ሥር የሚገኘው ፡ "የከተማ ፡ ክልል ፡ የሆኑ ፡ ሥፍራዎች ፡" ናቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ አራቱ ፡ ምዕራፎች ፡ እነዚህ ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

---

243. ይህ ፡ እርምጃ ፡ የተራድዖ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወደፊት ፡ ሊጀመር ፡ እንዲችል ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ መሠ ረት ፡ ለመጣል ፡ መታቀዱ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

## ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ "የኅብረት ፡ ባለሀብትነት" በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሥር ፡ ስላለው ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፤

ስለ ፡ "ኅብረት ፡ ባለሀብትነት ፡" እስካሁን ፡ የተደረሰው ፡ ጽሑፍ ፡ አነስተኛ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የተማታና ፡ ያልተጣራ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የተለዩ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ዎችን ፡ ለመግለጽ ፡ በተወሰነ ፡ አገባብ ፡ ሕጉ ፡ የሚጠቀምባቸው ፡ ቃላት ፡ ምርጫ ፡ ሳይደረግ ፡ በዘፈቀደ ፤ የኅብረት ፡ (ኮሙናል ፡) ባለሀብትነትንም ፡ ለማስረዳት ፡ ከጥ ቅም ፡ ላይ ፡ ውለው ፡ ይገኛሉ ።

አስቀድመን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡[244] የግልና ፡ የኅብረት ፡ ባለሀ ብትነት ፡ ስላላቸው ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ባጭሩ ፡ ምርመራ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኅብረት ፡ (ኮሙናል ፡) ባለሀብትነት ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ ምርመራ ፡ እንመለሳለን ። "ትር ጓሜ ፡" የሚል ፡ አርእስት ፡ የተሰጠው ፡ ቁጥር ፡ ፲፪፻፬ ፡ ሀብትነትን ፡ "ሲተረጉም ፡" በግዙፍ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ከሁሉ ፡ የሰፋ ፡ መብት ፡ ነው ፡ ይለዋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከቁጥር ፡ ፲፪፻፬ ፡ የሀብትነትን ፡ መለኪያ ፡ ለማወቅ ፡ ባንችልም ፤ ቁጥር ፡ ፲፪፻፲፫ ይህ ንኑ ፡ ቃል ፡ ለባለሀብቱ ፡ በተሰጡት ፡ መብቶች ፡ መሠረት ፡ ተርጉሞት ፡ ይገኛል ። እነዚህም ፤ ባለሀብቱ ፡ በንብረቱ ፡ በመሰለው ፡ መንገድ ፡ ሊገለገልበት ፤ ሊጠቀምበ ትና ፡ ዋጋ ፡ ተቀብሎም ፡ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ ሳይቀበል ፡ በንብረቱ ፡ ሊያዝበት ፡ የመቻሉ ፡ መብት ፡ ናቸው ። በላያቸውም ፡ ገደብ ፡ ተደርጐባቸዋል ።[245] ስለዚህ ፤ በጠቅላላ ፡ አነ ጋገር ፡ ጥንትም ፡ የባለሀብቶች ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱትን ፡ ሦስት ፡ መብቶች ፡ ማለት ፤ የመገልገል ፤ የመጠቀምና ፡ የማዘዝን ፡ መብት ፤ ሕጉ ፡ አክብሮ ፡ ይገኛል ።

በተጨማሪም ፤ ሕጉ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነትን ፤ ማለትም ፡ ለአንድ ፡ ነገር ፡ ከአ ንድ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰዎች ፡ ባለሀብት ፡ የሚሆኑበትንም ፤ ሁኔታ ፡ ይደነግጋል ።[246] የጋራ ፡ ሀብትነትም ፤ ጊዜያዊ ፡ ወይም ፡ ምንጊዜም ፡ የማይከፋፈል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የመጀመሪያው ፡ ዓይነት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ከባለሀብቶቹ ፡ ፍላጐት ፡ በሚመ ነጭ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የሚመሠረት ፡ ነው ።[247] በሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ የጋራ ፡ ባለ ሀብትነት ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ ላይኖር ፡ ይችላል ።[248]

ጊዜያዊ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ምንጊዜም ፡ የማይከፋፈል ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት፡ ንብረቱ ፡ እንዲያገለግል ፡ በተመደበበት ፡ ዓላማ ፡ መሠረት ፡ በነፃ ፡ ሊገለገልበት ፡ ይች ላል ። በተጨማሪም ፡ እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ከንብረቱ ፡ የሚገኘውን ፡ ፍሬ፡ ለመካፈል ፡ መብት ፡ አለው ።[249] የጋራ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ፤ ለማስተላ ለፍ ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ለማስያዝ ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ የተመደበበትን ፡ አገልግሎት፡ ለመለወጥ ፡ ሲፈለግ ፡ ግን ፡ ጊዜያዊ ፡ የሆኑ ፡ የጋራ ፡ ባለንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ መስማ ማት ፡ አለባቸው ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ጊዜያዊ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ብቻ ፡ እንኳን ፡ ሀሳቡን ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደሆን ፡ ንብረቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ የተመ

---

244. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ፫ኛ ፡ መጽሐፍ ፤ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ እና ፡ ፲፩ ፡ እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው ።
245. በተለይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪፻፳፭ ፤ ፲፪፻፳፮ ፤ እና ፡ ፲፱፻፲ን ፡ ከነተከታዮቹ ፡ ያነጻጽሯል ።
246. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪፻፶፯ ፡ (፩) ።
247. ይህን ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪፻፶፰ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።
248. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪፻፸፯ ፤ ፲፪፻፸፰ ።
249. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪፻፷፪ ።

ደበበትን ፡ ዓላማ ፡ ለመለወጥ ፡ አይቻልም ፡፡[250] ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንጊዜም ፡ የማይከፋ ፈል ፡ ንብረት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ተመሳሳይ ፡ መብት ፡ የለውም ፡፡ ይህም ፡ የተደረገ በት ፡ የባለሀብትነቱን ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ፡፡

ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ አጠቃላይ ፡ መለያ፡ አለው ፤ ይኸውም ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ባለሀብትነታቸው ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ በሙላ ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡፡ ስለዚህም ፡ የያንዳንዱ ፡ ባለሀብት ፡ ድርሻ ፡ ግዙፍ ፡ በመሆን ፡ አይታ ይም ፤ አይዳሰስም ፡፡ "የያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለንብረት ፡ ድርሻ ፡ የንብረቱ ፡ ገሚስ ፤ ሲሶ ፤ ሩብ ፡ ወዘተ ፡ እየተባለ ፡ በሂሳብ ፡ ክፍልፋይ ፡ ይገለጣል ፡፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ንን ፡ ክፍልፋይ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ እንደሚታይ ፡ እንደሚዳሰስ ፡ አድርጎ ፤ 'ይኸውና፡ ከንብረቱ ፡ ከዚህ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፤' ብሎ ፡ ማመልከት ፡ አይቻልም ፡፡ እያንዳ ንዱ ፡ ክፍልፋይ ፡ በጠቅላላው ፡ በንብረቱና ፡ በእያንዳንዱ ፡ ቅንጣት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር፡ ነው ፡፡" (እንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ፡፡)[251] ስለዚህም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡[252] ስለያ ንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ድርሻ ፡ በሚደነግግበት ፡ ጊዜ ፡ ድርሻውን ፡ እንደማይ ታይ ፡ ረቂቅ ፡ መብትና ፡ በያንዳንዱም ፡ የሀብቱ ፡ ቅንጣት ፡ አካል ፡ ላይ ፡ እንደተመ ሠረተ ፡ በማድረግ ፡ ነው ፡፡

እዚህ ፡ ላይ ፡ አጥብቆ ፡ ማሳሰብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ለግል ፡ ባለንብረቶች ፡ የተሰ ጡት ፡ ሦስቱ ፡ ሥልጣኖች ፡ በሕጉ ፡ ሥር ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ እንዲካፈሏቸው ፡ መደ ረጉን ፡ ነው ፡፡ ሕጉ ፡ ከዚህም ፡ አልፎ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የሀብታቸውን ፡ የአስተዳ ደር ፡ ሥራ ፡ "በአንድነት ፡" "እንዲመሩት" ፡ ይደነግጋል ፡፡[253]

በክፍል ፡ አንድ ፡ የተመለከትናቸውን ፡ የጎሣ ፡ የዘር ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ መሬቶ ችን ፡ ሁኔታ ፡ ሕጉ ፡ በጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ ሥር ፡ አለመጨመሩ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ በነዚህ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ መብት ፡ ተቀብሎ ፡ አይ ታይምና ፡፡

ከጎሣ ፤ ከዘር ፡ ወይም ፡ ከመንደር ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ የግለ ፡ ሰብኡ ፡ አባሎች ፡ ሁሉ፡ የተወሰነ ፡ ድርሻ ፡ እንዳላቸውና ፡ በድርሻቸውም ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ በግል ፡ የመጠ ቀምና ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ እንዳላቸው ፡ ተመልክተናል ፡፡ እያንዳንዱ ፡ አባል ፡ የየ ራሱን ፡ ድርሻ ፡ እንደፈቀደ ፡ ሊያለማው ፤ ወይም ፡ ለግጦሽ ፡ የሚሆን ፡ ድርሻውን ፡ ባሻው ፡ መንገድ ፡ ሊጠቀምበት ፡ መቻሉንም ፡ ተገንዝበናል ፡፡ ማንኛውም ፡ የዚያ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ የሆነ ፡ ሌላ ፡ አባል ፡ ያቺን ፡ ቁራጭ ፡ መሬት ፡ ያለባለመብቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሊገለገልባት ፡ አይችልም ፡፡

ስለዚህ ፤ ሕጉ ፡ ስለጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ የሚወስናቸው ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፤ የመ ንደር ፡ ወይም ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ግዙፍ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በመከፋፈሉና ፡ እያንዳንዱም ፡ አባል ፡ በድርሻው ፡ ላይ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የግል ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ በመሰጠቱ ፡ ለተባለው ፡ ርስት ፡ አግባብ ፡ ሊኖራቸው ፡ አይችልም ፡፡

"አንድ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡" መሬቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እንኳ ፡ ጊዜያዊ ፡ የሆኑ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ካላቸው ፡ መብት ፡ እጅግ ፡ የተ

250. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፷፯ ፡፡
251. ጄ ፡ ካርቦኒዬ ፤ ድሮ ፡ ሲቪል ፡ ቶም ፡ ፪ ፡ ሌቢያንዜት ፡ ሌዝ ፡ ኦብሊጋሲዮን ፡ (፲፱፻፶፯) ፡ እ- ኤ- አ- ገጽ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ፡፡ (ትርጉም) ፡፡
252. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፶፱ ፤ ፲፪፻፷ ፡፡
253. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፷፩ ፡፡

ለየ ፡ ነው ። አንድ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሆነ ፡ መሬት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ ከተስማሙበት ፡ መሬቱን ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ሊያስተላልፍ ፡ መቻሉን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ተመልክተናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ ደንብ ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባ ሎች ፡ የሚሰጠው ፡ መብት ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ እምቢ ፡ የማለትን ፡ ነው ። ስለዚህም፡ ቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ አንድ ፡ ባዕድ ፡ ወደሆነ ፡ ሰው ፡ መሬታቸው ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ለማ ድረግ ፡ (ለምሳሌ ፡ በመግዛት) ፡ ባይፈቅዱ ፡ ወይም ፡ (አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንደሚሆነው ሁሉ) ፡ ባይችሉ ፡ ባለመሬቱን ፡ ከመሸጥ ፡ የሚያግደው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ ከሆነው ፡ ከማንኛውም ፡ ክፍያ ፡ ውስጥ ፡ አንዱም ፡ እንዳይሸጥ ፡ ወይም ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ለማድረግ ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሁኔታ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነትን ፡ ከሚመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ፡ ፍጹም ፡ የተለየ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ የጋራ ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ ስምምነት ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።[254] በሌላ ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ከተቃወመ ፡ የጋራ ፡ የሆነው ፡ ንብረት ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ሊተላለፍ ፡ አይችልም ።

በጋራ ፡ ባለሀብቶችና ፡ የመንደርና ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሆነ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የመብት ፡ ተመሳሳይነት ፡ እንደሚከተለው ፡ ሊጠቃለል ፡ ይች ላል ፤ ሁለቱም ፡ "ንብረታቸውን ፡" በመሸጥ ፡ ወይም ፡ በማስተላለፍ ፡ ረገድ ፡ ያላቸው፡ መብት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ሌላ ፡ የመብት ፡ ተመሳሳይነት ፡ የለም ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በዘር ፡ ወይም ፡ በመንደር ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ የኅብ ረት ፡ መሰል ፡ መብት ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ መመሪያ ፡ የምናገኘው ፡ ሕጉ ፡ ስለጋራ ፡ ባለ ሀብትነት ፡ ከሚደነግጋቸው ፡ ደንቦች ፡ ሳይሆን ፡ የ"መንደር ፡" እና ፡ የ"የጐሣ ፡" መሬቶችን ፡ ከሚመለከቱት ፡ ከ፲፬፻፹፱—፲፬፻፺፪ ፡ ካሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ነው ። በነዚ ህም ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ የዘር ፤ የጐሣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ መሬቶች ፡ ሁሉ ፡ "የኅ ብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ ክፍል ፡" የሚባል ፡ "ማኅበር ፡" የግል ፡ ንብረት ፡ ሆነው ፡ ይቆጠራሉ ። ይህም ፡ "ማኅበር ፡" የዘር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፡ ቀበሌ፡ "ቤተዘመድ" ፤ የመንደር ፡ ርስት ፡ በሚገኝበት ፤ "መንደር ፡" እና ፡ የጐሣ ፡ መሬት፡ በሚገኝበትም ፡ "ጐሣ ፡" እየተባለ ፡ የሚጠራ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የዘር ፤ የመንደር ፡ ወይም ፡ የጐሣ ፡ የሆኑ ፡ መሬቶችን ፡ "የኅብረት ፡"[255] ወይም ፡ የጋራ ፡[256] ሀብት ፡

254. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪፻፷፯ ።

255. "የኅብረት ፡ የርስት ፡ ስሪት" ፡ የሚያመለክተው ፡ "---አንድ ፡ የተወሰነ ፡ መሬት ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፤ በጐሣ ፤ ወይም ፡ በመንደር ፡ ባለሀብትነት ፡ ሥር ፡---" መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተገልጧል ። ሡይፉ ፡ ተክለማርያም ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፴፫ ። ይህ ፡ አተረጓጐም ፡ ግልጽና ፡ የተብራራ ፡ አይደለም ።

256. ነቢየ ፡ ልዑል ፡ ክፍሌና ፡ ሌሎቹ ፤ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ሲስተምስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኤንድ ፡ አናሊሲስ ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ሪፎርምስ ፡ አንደርቴክን ፡ (፲፱፻፷፯ ፡ እ- ኤ- አ- ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ፤ ገጽ ፡ ፱ ። በዚህ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ "ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይከፋፈሉ ፡ የመሬት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች" ፡ ናቸው ፡ ተብለዋል ። የዚህ ፡ አተረጓጐም ፡ አንድ ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ጉድለት ፤ "ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይከፋፈሉ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች" ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ በሕጉ ፡ ቃል ፡ ታስቦ ፡ ያልነበረ ፡ ትርጉም ፡ መስጠቱ ፡ ነው ። ከቍጥር ፡ ፲፪፻፷፯ ፡ ጋር ፡ ያነጻጽሯል ። የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይከፋፈል ፡ የጋራ ፡ ባለሀ ብትነትን ፡ ሲገልጹ ፤ የሚሰጧቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ የውሀ ፡ ጉድጓድን ፤ የመንገድንና ፡ የመቃብር ፡ ቦታ ዎችን ፡ ባለሀብትነት ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ በተፈጥሮአቸው ፡ ሊከፋፈሉ ፡ የማይችሉ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

ብሎ ፡ መጥቀስ ፡ ትክክል ፡ አይደለም ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሊኖረን ፡ የሚችለው ፡ ማንኛውም ፡ ጥርጣሬ ፡ በኅብረት ፡ እርሻ ፡ ባለሀብትነት ፡ (እና ፡ በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማህበር ፡) እና ፡ በጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ መካከል ፡ ያለውን ልዩነት ፡ ለመወሰንና ፡ ያልተብራራም ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ለማብራራት ፡ በታቀደው ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፶፯ ፡ (፪)፡ ሊወገድ ፡ ይችላል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፩፻፹፱ ፡ ሥር ፡ የተጠቀሱት ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ዝርዝር ፡ የተሟላ ፡ አለመሆኑን ፡ መጥቀስ ፡ ይገባል ። የዝርዝሩ ፡ ዓላማ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ለታቀዱት ፡ መሬቶች ፡ ምሳሌ ፡ ለመስጠት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በእንግሊዝኛው ፡ "ቪሌጅ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚገልጸው ፡ የመንደርን ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ነው ። ይህም ፡ አስተያየት ፡ "ደሽ ፡" በሚለው ፡ በአማርኛው ፡ ትርጓሜ ፡ የተደገፈ ፡ ነው ፤ "ጕልተ ፡" የሚለውም ፡ ቃል ፡ የሚያመለክተው ፡ በአንደኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የተመለከትናቸውን ፡ የከብት ፡ አርቢ ፡ ክፍሎች ፡ የጕልተ ፡ መሬት ፡ ስሪትን ፡ ነው ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ "ጕልተ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ ስሪትን ፡ አያጠቃልልም ።

ከሺ፩፻፹፱ ፡ እስከ ፡ ሺ፩፻፺፪ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ቁጥሮች ፡ በዘር ፡ ርስት ፡ ስሪት ፡ ስር ፡ የሚገኙ ፡ መሬቶችንም ፡ ይመለከታሉ ፡ የምንልበት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉን ። የዘር ፡ (አንዳንድ ፡ የዘር ፡ ሐረጎች ፡ በመቶ ፡ የሚቆጠሩ ፡ አባሎች ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላሉ ፤) የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ከመንደር ፡ ወይም ፡ ከጕልተ ፡ መሬቶች ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላሉ ፤ ምክንያቱም ፡ የዘር ፡ ርስትም ፡ እንደ ፡ መንደርና ፡ ጕልተ ፡ ርስት ፡ "የኅብረት ፡" ሀብትነትን ፡ አዝሎ ፡ ስለሚገኝ ፡ ነው ። ሁለተኛም ፤ ሕጉን ፡ ያረቀቁት ፡ ሊቅ ፤ የኅብረት ፡ ስለሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ የተረቀቀው ፡ ሕግ ፡ በየ"መንደሩ ፡" ለሚገኙት፡ ለትግሬና ፡ ለኤርትራ ፡ ሕዝቦች ፡[257] የታቀደ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ያትታሉ ። በእነዚህ ፡ ሁለት ፡ ጠ/ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ የመንደርና ፡ የዘር ፡ ስሪት ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ በየመንደሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ መገኘታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የዘር ፡ ርስትም ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፹፱—፩ሺ፩፻፺፪ ባለው ፡ ደንብ ፡ ስር ፡ የሚተዳደር ፡ ነው ። ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ አንድ ፡ የመጨረሻ ፡ ነገር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ የዘር ፡ ርስትን ፡ "በጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡" ስር ፡ ለማስተዳደር፡ እንደሚቻል ፡ የሚፈቅድ ፡ የሚመስለው ፡ የእንግሊዝኛው፡ ቁጥር፡ ፩ሺ፩፻፷፩ ፡ (፩)፡ ከሺ፩፻፹፱ ፡—፩ሺ፩፻፺፪ ፡ ያሉትን ፡ ቁጥሮች ፡ የሚቃረን ፡ መምሰሉ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ፡ ይህ ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ቁጥሩ ፡ ከአማርኛ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ሲተረጐም ፡ በተደረገ ፡ ስህተት ፡ ነው ።[258] በቁጥር ፡ ሺ፩፻፷፫ ፡ የአማርኛ ፡ ቅጂ ፡ ውስጥ ፡ "የጋራ ፡ ባለሀብ

---

አር ፡ ዳቪድ ፤ ከማንቴር ፡ ዱ ፡ ቴትር ፤ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ኮፕሪፕሪዬቴ ፤ ደልዩሱፍሩይ ፤ ኤ ፡ ዴዝ ፡ አትር ፡ ድሯሬል ፡ (ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፵፫) ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፵፰ ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ያልታተመ) ፡ (የማይገኝ) ፤ ገጽ ፡ ፩ ። ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፤ ከላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባሎች ፡ በመሬታቸው ፡ ላይ ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ እንዳላቸው ፡ ይናገራሉ ። ላውረንስ ፡ ኤንድ ፡ ማን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፱፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፰ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ልንገነዘበው ፡ የሚገባን ፡ ነገር ፡ መንደረተኞች ፡ በመንደራቸው ፡ መሬት ፤ ቤተ ፡ ዘመዶችም ፡ በቤተ ፡ ዘመዳቸው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ ለመግለጽ ፡ "የአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይ ፡" በሚል ፡ አነጋገር ፡ መገልገል ፡ ትክክለኛ ፡ አለመሆኑን ፡ ነው ። የአላባን ፡ ጥቅም ፡ ተቀባይን ፡ ቋሚ ፡ ጠባዮች ፡ ከቍጥር ፡ ሺ፫፻፱ ፡ (፩) ፡ እና ፡ ሺ፫፻፳፪ ፡ ይረዷል ።

257. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ።

258. የመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ከቍጥር ፡ ሺ፩፻፷፩ ፡ (፩) ፡ ሁለተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ ደንብ፡ አልነበረውም ። ግርማ ፡ ሥላሴ ፡ አርአያ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፹፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፬።

ትነት ፡” የሚለው ፡ ሐረግ ፡ አይገኝበትም ። ስለዚህ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቁጥር ፡ ሺ፩፻፷፰ ፡ ሊነበብ ፡ የሚገባው ፡ ለጉዳዩ ፡ በቀጥታ ፡ አግባብ ፡ ካላቸው ፡ ከቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፱ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፡ ጋር ፡ ነው ። ከሺ፬፻፹፱—ሺ፭፻ ፡ ያሉት ፡ ቁጥሮች ፡ የዘር ፡ ርስትንም ፡ የሚመለከቱ ፡ ሲሆን ፤ የዘር ፡ የሆነ ፡ መሬት ፡ “በጋራ ፡ ባለሀብት ነት ፡” ስር ፡ ሊተዳደር ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ አያመለክቱም ።

## <u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ እርሻ ፡ መሬት ፡ ስላላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፤</u>

በቁጥር ፡ ሺ፬፻፹፱—ሺ፭፻ ፡ ባሉት ፡ ሥር ፡ የተጠቀሱት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፤ የጐሣና ፡ የመንደር ፡ የእርሻ ፡ “ማኅበሮች ፡” ሕጋዊ ፡ ሰውነት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ? ሕጋዊ ፡ ሰውነታቸው ፡ እንደግል ፡ ማኅበሮች ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ “መንግሥታዊ ፡” አቋሞች ? የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ሙሴ ፡ ዳቪድ ፡ እንዳመለከቱት ፡ ሁሉ ፤ “በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ‘ሰው’ ፡ ወይም ፡ ‘ሰውነት’ ፡ ብለን ፡ ስንናገር ፡ እንደሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ [ናቸው] ፡ ለማለት ፡ ሳይሆን ፡ እንደሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ አላቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱ ፡ ከሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ መኖራቸውን ፡ ለመግለጥ ፡ ነው ።”[259]

እነዚህ ፡ “ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ሰዎች ፡” ሰብአዊ ፡ ፍጡራን ፡ ያሏቸውን ፡ መብቶችና፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደሌሏቸው ፡ መገንዘብ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። የሚሰጧቸው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ የተወሰኑና ፡ ለአቋማቸውና ፡ ለታቀዱበትም ፡ ዓላማ ፡ አስፈላጊ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የሚገመቱትን ፡ ብቻ ፡ ነው ።[260]

አንድ ፡ ከላይ ፡ እንደተጠቀሱት ፡ ያለ ፡ የእርሻ ፡ “ማህበር ፡” ያለውን ፡ ሕጋዊ፡ የሰውነት ፡ አቋም ፡ ለመወሰን ፤ የ“ማኅበሩን ፡” መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ መመልከትና፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ “የግል ፡” እና ፡ “ሕዝባዊ ፡” (መንግሥታዊ) ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስላሏቸው ፡ ማኅበሮች ፡ መመራመር ፡ ያሻል ።[261]

የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ከተሰጡዋቸው ፡ መብቶች ፡ ጐላ ፡ ብሎ ፡ የሚታየው ፡ የማኅበሩ ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ እንዳይወሰድ ፡[262] የሚያግደው ፡ ደንብ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ መብት ፡ ዝቅ ፡ ብለን ፡ በዝርዝር ፡ እንነጋገራለን ።

ከተባሉት ፡ ማህበሮች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፤ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ የሕብረት ፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለመያዝ ፡ አይችሉም ።[263] ለኅብረቱ ፡ መሬት ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ለማህበሩ ፡ አባሎች ፡ መተዳደሪያ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የኅብረቱ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች

---

259. አር ፡ ዳቪድ ፤ ኤክስፖዜ ፡ ዴ ፡ ሞቲፍ ፡ ኤ ፡ ኮማንቴር ፡ ዱ ፡ ቲትር ፤ ዴ ፡ ፔርሶን ፡ ሞራል ፡ ኤ ፡ ዴ ፡ ፓትርሚን ፡ ዳፌክታሲዮን ፤ (ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፴፯) ፤ ዶኩማ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ፴፯፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ያልታተመ )፡ (የማይገኝ) ፡ ገጽ ፡ ፬ ። (ትርጉም) ።
260. ከዚያው ።
261. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ ፬፻፺፫ ፡ እና ፡ ፬፻፬ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፤ እንደ ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸው ።
262. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፩ ፡ (፩) ።
263. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፩ ፡ (፪)ን ፡ ከሺ፬፻፺፩ ፡ (፩) ፡ ጋር ፡ በማናበብ ።

ንም ፡ ለመያዝ ፡ የሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ ተመሳሳይ ፡ ፈቃድ ፡ አስቀድሞ ፡ ማግኘት ፡ ያሻዋል ።[264] ከማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ተንቀሳቃሽም ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ የሕብረቱን ፡ ንብረት ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ የላቸውም ።[265]

የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባለው ፡ ማህበር ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ከተደረጉት ፡ ገደቦች ፡ በጣም ፡ጉልህ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ በቁጥር ፡ ሺ፬፻፫ ፡ (፪) ሥር ፡ የተመለከተው ፡ ነው ። አንድ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ማህበር ፡ <u>የራሱን ፡</u> መሬት ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ለመሸጥ ፤ ለማስተላለፍ ፤ መያዣ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችለው ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርን ፡ ፈቃድ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ፡ ነው ። ባለሀብቱ ፡ መሬቱን ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ በጥብቅ ፡ የሚወስነውን ፡ የዚህን ፡ ድንጋጌ ፡ ትርጉም ፡ በሚገባ ፡ መረዳት ፡ ይጠቅማል ። በተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ አንድ ፡ ማህበር ፡ የሚኒስቴሩን ፡ ፈቃድ ፡ ካላገኘ ፡ በቀር ፡ መሬቱን ፡ ከፋፍሎ ፡ <u>ለገዛ ፡</u> አባሎቹ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ እንዳይሸጥ ፡ ወይም ፡ (በዋጋም ፡ ሆነ ፡ ያለዋጋ) ፡ እንዳያስተላልፍ ፡ ይከለክለዋል ። ሚኒስቴሩ ፡ ለመፍቀድ ፡ ወይም ፡ ላለመፍቀድ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ገደብ ፡ ያልተበጀለት ፡ በመሆኑ ፤ ባንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተባሉት ፡ ማኅበሮች ፡ ፍላጐት ፡ በሚኒስቴሩ ፡ ፍላጐት ፡ መወሰኑ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፬፻፲፫ ፡ (፪) ከሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ የሚያስከትለው ፡ አንዱ ፡ ውጤት ፡ ማህበሮቹ ፡ ባንዳንድ ፡ ምክንያቶች ፡ የማይፈልጉትን ፡ መሬት ፡ ይዘው ፡ እንዲኖሩ ፡ ማስገደዱ ፡ ነው ።

ባገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ላይ ፡ ከተጣሉት ፡ ኃላፊነቶች ፡ መካከል ፤ የማህበሮችን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ የሚመለከቱት ፡ ከበድ ፡ ያሉ ፡ ሆነው ፡ ይታያሉ ። እያንዳንዱ ፡ ማህበር ፡ እንደየልማዱና ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ልማዱን ፡ የሚያሟላ ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ያስብበታል ።[266] ይህን ፡ ደንብ ፡ ማኅበሩ ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ከዓላማዎቹ ፡ አንዱ ፡ የሆነውን ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ ሚኒስቴሩ ፡ የተባለው ፡ ደንብ፡ በየጊዜው ፡ እንዲሻሻል ፡ ለማድረግ ፡ በተጨማሪ ፡ እንዲያስብበት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።[267]

እነሆ ፤ ባጭሩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፤ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ ረቂቅ ፡ አካል ፡ ፈጥሯል ፤ መብቶችን ፡ ሰጥቶታል ፤ ግዴታዎችንም ፡ ጥሎበታል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የአንዱን ፡ "ጥበቃ"ም ፡ ሰጥቶታል ።

ከላይ ፡ እንደተረዳነው ፡ የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሌሎች ፡ ማህበሮች ፡ ሁሉ ፡ ያሏቸው ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ይጐድላቸዋል ። ይኸውም ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ በተነሳሱ ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተመሠረቱ ፡ ማህበሮች ፡ አለመሆናቸው ፡ ነው ።[268] እንደተመለከትነው ፡ ሁሉ ፡ የተ

264. ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፭ ፡ (፩) ፡ ተቃራኒውን ፡ ደንብ ፡ በማግኘት ፡ (አኮንትራሪዮ ።)
265. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፭ ፡ (፫) ።
266. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺ ።
267. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፺፰ ፡ (፩) ።
268. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፬ ።

ባሉት ፡ ማህበሮች ፡ ተመሥርተው ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ የተደረገው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በአባሎቹ ፡ ውሳኔ ፡ አንድ ፡ የሕብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ ማህበር ፡[269] ሊፈርስ ፡ "የሕግ ፡ ሰውነቱንና ፡" ከዚህም ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ መብቶቹንም ፡ እንዲያጣ ፡ ሊደረግ ፡ አይችልም ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ውሳኔ ፡ በግልጽ ፡ ከሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አባሎች ፡ ለማኅበራቸው ፡ ያልሰጡትን ፡ መብት ፡ ሊገፉት ፡ አይችሉምና ።

እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፣ የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሕዝባዊ ፡ (መንግሥታዊ ፡) የሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ናቸው ፡ ሊባል ፡ ይቻላልን ?

እነዚህ ፡ ማህበሮች ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡ ናቸው፣ ለሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፡ አንድ ፡ ተቃውሞ ፣ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮች ፡[270] በሚገኙበት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ሊመሠረት ፡ የሚችል ፡ ነው ። ይህ ፡ ክፍል ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማህበሮችን ፡ አይጠቅስም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ እንደገለጡት ፡[271] በተባለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ዝርዝር ፣ ሕዝባዊ ፡ የሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ አይደለም ። ይህንንም ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፣ በተለይም ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፯ ፣ በቀላሉ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ።

በዚህም ፡ መሠረት ፣ በቁጥር ፫፻፺፬—፫፻፺፰ ፡ መሠረት ፡ ሕዝባዊ ፡ የሆነ ፡ የሕግ፡ ሰውነት ፡ ያልተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡ ወይም የሕዝብ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ ከሆኑና ፡ በአስተዳደር ፡ ሕግም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተለይ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እንዳላቸው ሊቆጠሩ ፡ ይችላሉ ።[272]

(በቁጥር ፡ ፫፻፺፭ ፡ ሥር ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ወደጐን ፡ ትተን) ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፬—፫፻፺፯ ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ብንመረምር፣ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ድርጅቶች ፡ ሁለት ፡ የተለየ ፡ ጠባይ ፡ ያሏቸው ፡ መሆኑን ፡ እንረዳለን ።

አንደኛ ፤ እነዚህ ፡ ድርጅቶች ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፣ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ቅርንጫፎች ፣ ወይም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጋር፡ የተያያዘ ፡ ሕዝባዊ ፡ ተግባር ፡ የሚያከናውኑ ፡ ናቸው ።

ሁለተኛ ፤ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ለተሰጣቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ የሚሰጠው ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የሕግ ፡ ቃል ፡ አማካይነት ፡ ነው ። ከቁጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ እና ፡ ከተከታዮቹ ፣ በተለይም ፡ ከቁጥር ፡ ፫፻፺፯ ፡ አነጋገር ፣ በግልጽ ፡ ሳይደነ

269. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፵፱ ፡ እና ፡ ፬፻፷ ።
270. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ።
271. ዳቪድ ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፶፰ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፬ ።
272. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፰ ።

ገግ ፤ ተዘዋዋሪ ፡ በሆነ ፡ የአተረጐጓም ፡ ዘዴ ፡ ለአንድ ፡ ድርጅት ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ተሰጥቷል ፤ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ትክክል ፡ አለመሆኑን ፡ እንገነዘባለን ።

ከላይ ፡ የተመለከትናቸው ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ ካሏቸው ፡ ሁለት ፡ ጠባዮች ፡ ጋር ፡ ስናስተያያቸው ፤ የሕብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያሏቸው ፡ ማህበሮች ፡ ሕዝባዊ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያሏቸው ፡ ድርጅቶች ፡ አይደሉም ። ምክንያቱም ፡ በቁጥር ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ሥር ፡ በተለይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ የመንግሥት ፡ የግዛት ፡ ክፍሎች ፤ በቁጥር ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ሥር ፡ ከተመለከቱት ፡ ሚኒስቴሮች ፤ ቁጥር ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አንዱ ፡ አይደሉምና ።

እዚህ ፡ ላይ ፤ እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ የሕዝብ ፡ "ድርጅቶች ፡" ፡ (ኢስታብሊሽመንትስ) ፡ ናቸውን ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ሊነሳ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ቃል ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ቀዋሚ ፡ የሆነ ፡[273] ትርጉም ፡ አልተገኘለትም ። (አርቃቂው ፡ ስለ ዚህ ፡ ቃል ፡ የተዉት ፡ ማስታወሻ ፡ የለም) ።[274] ይሁንና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እርግጠኛው ፡ የቃሉ ፡ ትርጉም ፡ ተጣርቶ ፡ ባይታወቅም ፡ "ድርጅት ፤" የሚባል ፡ አቋም ፡ ሁሉ ፡ ለጠቅላላው ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ አገልግሎት ፡ የሚያበረክት ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ስምምነት ፡ አለ ።[275]

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበሮች ፡ የሚያበረክቱት ፡ አንዳችም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የለም ። የተቋቋሙበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ ዘመናዊ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ ፍጹም ፡ የግል ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶችን ፡ በበለጠ ፡ ለማልማት ፡ እንዲቻል ፡ በማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ የተቋቋሙበት ፡ በልማድ ፡ "የቤተሰብ፡" "የጐሳ፡" እና ፡ "የመንደር ፡" ሀብት ፡ የነበረው ፡ የግል ፡ መሬት ፡ ባለሀብትነት ፡ ዘመናዊ ፡ መልክ፡ እንዲይዝ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበሮች ፡ በቁጥር ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ መሠረት ፡ "ድርጅቶች ፡" ናቸው ፤ የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ ብንቀበለው ፡ እንኳ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በግልጽ ፡ ስላልተሰጣቸው ፡ የሕዝብ ፡ ድርጅቶች ፡ ሊባሉ ፡ አይችሉም ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎች ፡ የሕዝብም ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ ድርጅት ፡ ናቸው ፡ ሊባሉ ፡ አይችሉም ። ስለዚህም ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፤ ከሌሎች፡ድርጅቶች ፡ የማይገጥሙ ፤ አንድ ፡ የተለየ ፡ ክፍል ፡ ያላቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በመሆን ፡ በአንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ሥር ፡ የሚተዳደሩ ፤ የመሬት ፡ ባለቤቶች ፡ ለመሆንና ፡ በስምምነትም ፡ ሆነ ፡ በክስ ፡ ላይ ፡ በእንደራሴዎች ፡ የመወከል ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

273. አ ፡ ማርቲን ፡ ፓኔቲዬ ፤ ኤሌማ ፡ ዳናሊዝ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ዴዜ ፡ ኤታብሊሰማ ፡ ፑብሊክ ፡ አንድሯ ፡ ፍራንሴ ፡ ኤት ፡ አን ፡ ድሯዝ ፡ አንግሌ ፡ (፲፱፻፷፯ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ፤ ከገጽ ፡ ፪—፳፫ ፤ "ኤታብሊሰማ ፡ ፑብሊክ" የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ የሚተነትኑትን ፡ እና ፡ አ ፡ ላውባዴር ፡ ትሬይቴ ፡ ኤሌማንቴር ፡ ደ ፡ ድሯት ፡ አድሚኒስትራቲፍ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ እ - ኤ - አ) ፤ ገጽ ፡ ፩፻፺፱—፩፻፷፯ን ፡ ያወዳድሯል ።

274. የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ "የሕዝብ ፡ ድርጅት" ፡ የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ በዝርዝር ፡ ማብራሪያቸው ፡ ውስጥ ፡ በመተርጐም ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ የለም ። ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ የተጠቀ
275. ሰው ። ማርቲን ፡ ፖኔቲየ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፫ ።

የተለየ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ በመሆን ፤ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ማኅበሮች ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ (፩) እንደተደነገገው ፡ ሁሉ ፡ በይርጋ ፡ መሬታቸውን ፡ ሊነጠቁ ፡ አይችሉም ።[276]

በዚህ ፡ ቁጥር ፡ በአማርኛው ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ድጋፍ ፡ ማግኘት ፡ ባይቻልም ፤ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በብዙ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፤[277] ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ (፩) የሚከለክለው ፡ አንድ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አባል ፡ በይዞታው ፡ ሥር ፡ የሚገኘውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፤ ሐረጌን ፡ መዝገቤ ፡ ልካፈል ፤ የሚል ፡ ሲመጣ ፡ በይርጋ ፡ እንዳያግደው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አንድ ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ በይዞታው ፡ የሚገኘውን ፡ የሌሎች ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ አስቀራለሁ ፡ በሚልበት ፡ ጊዜ ፡ አይደለም ፤ ይህ ፡ ተወላጅ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ የሌሎችን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ሊያስቀር ፡ ይችላል ፤ በማለት ፡ ወስነው ፡ ይገኛሉ ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ የተሳሳተ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እናምናለን ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ (፩) የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ተወላጅ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ ባለቤትነት ፡ በይርጋ ፡ ሊያገኝ ፡ እንደሚችል፡ ተደርጎ ፡ ከተተረጐመ ፤ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መሬቶችን ፡ ጭምር ፤ በይርጋ ፡ እንዳይዝ ፡ የሚከለክለውን ፡ ቁጥር፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩)ን ፡ በቀጥታ ፡ የሚቃረን ፡ ይሆናል ። እላይ ፡ የተሰነዘረው ፡ የቁጥር፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ (፩) ትርጉም ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ጠቅላላ ፡ መንፈስና ፡ ዓላማ ፡ የሚያፋልስ ፡ ነው ። ይህ ፡ ምዕራፍ ፡ የእንደዚህ ፡ ዓይነቶችን ፡ መሬቶች ፡ ባለቤትነት ፡ ግዙፍ ፡ ሰውነት ፡ ለሌለው ፡ ረቂቅ ፡ የሕግ ፡ ፍጡር ፡ በመስጠት ፡ መሬቶቹ ፡ በባዕድም ፡ ሆነ ፡ በተወላጅ ፡ በይርጋ ፡ እንዳይያዙበት ፡ የተለየ ፡ መከላከያ ፡ አድርጐለታል ።[278]

በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ (፩) ስር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ትክክለኛው ፡ ትርጉም ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩) የተመለከተውን ፡ ደንብ ፡ የሚያሟላና ፡ የሚደግፍ ፡ ነው ፤ የሚለው ፡ ይመስለናል ። ይህም ፡ የተባለበት ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አባልም ፡ ሆነ ፡ ባዕድ ፡ የሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድን ፡ ርስት ፡ በይርጋ ፡ ሊያስቀር ፡ አይችልም ፤ በማለቱና ፡ ቃላቱም ፡ በባዕድና ፡ በተወላጅ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ሳይፈጥሩ ፡ በደፈናው ፡ በሁለቱም፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ደንብ ፡ በመደንገጋቸው ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ይህ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ (፩) ስር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ የቤተዘመድን ፡ መሬት ፡ በሚነካ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩) ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ የሚለይ ፤ ደንቡንም ፡ የማይከተል ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ (፩) አንድ ፡ ባዕድ ፡ ሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድን ፡ ርስት ፡ ባለቤትነት ፡ በይርጋ ፡ ሊያስቀር ፡ እንደሚፈቅድ ፡ ተደርጐ ፡ ቢተረጐም ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩) ጋር ፡ አይፋለስም ፤ የሚል ፡ ክርክር ፡ ማቅረብ ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ።

---

276. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፫ ፡ (፩) ።

277. ለምሳሌ ፡ የከሳሽን ፡ ተፈራ ፡ ስብሐት ፡ ሕዝቅያስ ፡ ስብሐትንና ፡ የተከሳሽን ፡ ባሕታ ፡ ተስፋይንና ፡ ሌሎች ፡ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ) ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ዓ፡ ም፡ ) ፡ ጉዳይ ፤ ከኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፪ ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።

278. እዚህ ፡ ላይ ፡ አንባቢ ፡ እንዲያስተውለው ፡ የሚገባው ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የርሻ ፡ መሬቶችን ፡ ቤተ ፡ ዘመድም ፡ ሆነ ፡ ባዕድ ፡ በይርጋ ፡ ሊይዛቸው ፡ ያለመቻሉን ፡ በግል ፡ ይደነግግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ነው ። ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፵ ። የመጀመሪያው ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፳፰ ፡ ረቂቅ ፡ የተጠበቀውን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመስል ፡ እንዳልነበረው ፡ ስናስታውስ ፤ ለመጨረሻው ፡ ረቂቅ ፡ ተመሳሳይ ፡ ቍጥር ፡ አለመጨመሩ ፤ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ ሊያሰጠው ፡ አይችልም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ ትክክል ፡ አይደለም ። "ስለጠቅላላ ፡ ጉዳይ ፡ የሚ ወስነውን ፡ ሕግ ፡ ስለተለየ ፡ ጉዳይ ፡ የሚወስነውን ፡ ሕግ ፡ ይገዛዋል ፡" የሚለውን ፡ የሕግ ፡ መተርጐሚያ ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ ተከትለን ፤ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩) ይልቅ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) የበላይነት ፡ አለው ፡ ለማለት ፡ ሁለቱም ፡ ቁጥሮች ፡ በተመሳ ሳይ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ቢሆኑም ፤ የአንዱ ፡ ቁጥር ፡ አፈጻጸም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ውጤት ፡ ሲያደርስ ፡ የሌላው ፡ ቁጥር ፡ አፈጻጸም ፡ ደግሞ ፡ ወደተለየ ፡ ውጤት ፡ እንደ ሚያደርስ ፡ ማስረዳት ፡ ይኖርብናል ።

ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻል ፡ አይመስለንም ። ምክንያቱም ፡ እላይ ፡ እንዳሳየነው፡ ሁሉ ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ አጻጻፍና ፡ የቋንቋ ፡ አገባብ ፤ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) የሚከለክለው ፡ ተወላጅ ፡ ብቻ ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይ ርጋ ፡ እንዳይዝ ፡ ነው ፤ ለሚለው ፡ አስተያየት ፡ ድጋፍ ፡ ሊሆን ፡ ስለማይችል ፡ ነው። "ቃል ፡ በቃል ፡" ሲነበብ ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ሥር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ተወላጅም ፡ ባዕድም ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ እንዳይዙ ፡ ይከለክላል ። ስለዚህ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ (፩) እና ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ሥር ፡ በተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ መሀል ፡ አንዳችም ፡ የቃል ፡ አለመስማማት ፡ የለም ።[279]

በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ስር ፡ በተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ "በተወላጅ ፡ ብቻ ፡" የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ ማስገባትና ፡ ባዕድ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይ ርጋ ፡ እንዲይዝ ፡ ማድረግ ፤ የተለመደውን ፤ "ሕጉ ፡ ራሱ ፡ ልዩነት ፡ በማይፈጥር በት ፡ ጊዜ ፡ (በትርጉም ፡) ምንም ፡ ልዩነት ፡ መፍጠር ፡ አይገባም ፡" የሚለውን ፡ የሕግ ቃላት ፡ መተርጐሚያ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ መጣስ ፡ ይሆናል ።[280] ሕጉ ፤ ማለትም ፡ በቁ ጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ሥር ፡ የተጠበቀው ፡ ሁኔታ ፤ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ስለመያዝ ፡ በባዕድና ፡ በተወላጆች ፡ መሀል ፡ አንዳችም ፡ ልዩነት ፡ አይፈጥርም ። ስለዚ ህም ፡ ባዕድም ፡ ተወላጅም ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) መሠረት ፡ የተወላጆችን ፡ መሬት ፡ በይርጋ ፡ ለመያዝ ፡ አይችሉም ፡ ወደሚል ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ መድረስ ፡ ግድ ፡ ይሆንብናል ።

## ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፤ መሬትን ፡ "በተራድዖ ፡" እና ፡ በ"ግል" ፡ ለማልማት ፡ ስለተደነገጉት ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስለሚለሙበት ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፹፱ ፤ ፩ሺ፩፻፺፩ ፡ (መ) ፤ ፩ሺ፩፻፺፪ ፡ እና ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ መሀከል ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ ስለሚታየው ፡ የቃል ፡ አለመስማማት ፡ እንመራመራለን ። አስቀድመን ፡ መሬትን ፡ "በኅብረት ፡ ማልማት ፡ (መሥራት)" ፡ ማለት ፡ ምን ፡ እንደ ሆነ ፡ እንመለከታለን ። የመጀመሪያውን ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅና ፡ ከላይ ፡ በክፍል ፡ ፩ ፡ የተ መለከትናቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ክፍሎች ፡ ልማድ ፡ በመመልከት ፤ የሕጉ ፡ ትርጉም ፡ ሊሆን ፡ በማይችል ፡ አገላለጽ ፡ መጀመር ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ይታየናል ።

"በኅብረት ፡ ማልማት ፡" (ኤክስፕሏይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡) የሚለው ፡ የፈረንሣ

---

279. እርግጥ ፡ አለመስማማት ፡ ያለው ፡ ሊደነገግ ፡ በተፈለገውና ፡ በቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ (፩) ፡ ግልጽ ፡ ቃላት ፡ መሠረት ፡ በተደነገገው ፡ መካከል ፡ መሆኑን ፡ ይገነዘቧል ።

280. ኤም ፡ ፕላኒዮልና ፡ ጂ ፡ ሪፔር ፤ ትሪቲስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ (፲፩ኛ ፡ እትም ፤ ፲፱፻፴፰ ፡ እ-ኤ-አ ትርጉም ፤ ሉዊዚያና ፡ እስቴት ፡ ሎው ፡ ኢንስቲቲውት ፤ ፲፱፻፶፱ ፡ እ- ኤ- አ-) ፤ ቮል- ፩ ፤ ክፍል ፡ አንድ ፤ ቍጥር ፡ ፪፻፳፬ ፡ ኤ ።

ይኛው ፡ ሐረግ ፡ በአንድ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሪፖርት ፡ ውስጥ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተተርጉሞ ፡ ይገኛል ።[281]

"መሬትን ፡ በኅብረት ፡ ስለማልማት ፡" (ኤክስፕሏይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡) አንድን ፡ በይዞታ ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ማሳ ፡ ከብዙ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ በተውጣጡ ፡ ሰዎች ፡ ማሳረስ ፤ ማንኛውም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ቢሆን ፡ በኅብረት ፡ (በተራድዖ ፡) ከሚታረሰው ፡ መሬት ፡ ጠቅላላ ፡ ስፋት ፡ ውስጥ ፡ በማንኛውም ፡ ማሳ ፡ ላይ ፡ ዘላቂ ፡ መብትም ፡ ሆነ ፡ ኃላፊነት ፡ የሌለው ፡ ሲሆንና ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ በእጅ ፡ የሚሠራውን ፡ ሁሉ ፡ በሚያከናውኑት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ የቀጣሪና ፡ የተቀጣሪ ፡ ሳይሆን ፤ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሚታሰብለት ፡ ዋጋ ፡ የሚለካው ፡ በሚያበረክተው ፡ የጉልበት ፡ መዋጮ ፡ ዓይነት ፡ ወይም ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።" (አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።)

"ኤክስፕላይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ ትርጉም ፡ እንደሌለው ፡ በቀላሉ ፡ የምንረዳው ፤ ሕጉ ፡ "የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንብረትን" ፡ "ንብረት ፡ ማስለቀቅን" ፡ "የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበርን ፡" እና ፡ "የከተማ ፡ ቀበሌዎችን ፡" ሁሉ ፡ "ኤክስፕሏይታሲዮን ፡ ኮሌክቲቭ፡" (የኅብረት ፡ ልማት ፡) በማለት ፡ በኅብረት ፡ የመጠቀሚያ ፡ ዘዴዎች ፡ አድርጎ ፡ በመቍጠሩ ፡ ነው ።[282] እነዚህ ፡ ከላይ ፡ የዘረዘርናቸው ፡ ዘዴዎች ፡ ሁሉ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አስተሳሰብ ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ "የንብረት ፡ ማልማት ፡" ዘዴ ፡ ውስጥ ፡ ሊመደቡ፡ የሚችሉ ፡ አይደሉም ።

በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፹፱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ "በኅብረት ፡ መሠራት ፡" የሚለው ፡ የአማርኛው ፡ ሐረግ ፤ በተራድዖ ፡ ማረስ ፡ ወይም ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮች እንደሚገኘው ፡ በአንድ ፡ ሰፈ ፡ በሆነ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ አቋም ፡ "---ዋና ፡ መሪ ፡ ፡ሥር ፡ ---"[283] እንደሚካሄደው ፡ የመሬት ፡ አስተራረስ ፡ ዘዴ ፡ ያለ ፡ አለመሆኑን ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፩ ፡ (መ) ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፺፯ ፡ እና ፡ ፩ሺ፩፻፺፯ ፡ መካከል ፡ ከሚታየው ፡ አለመስማማት ፡ ልንረዳ ፡ እንችላለን ።

በመጀመሪያው ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ሐረጎች ፡ "ኤክስፕሏይቴ ፡ ሴሎን ፡ አን ፡ ሞድ ፡ ኮሌክቲቭ ፡" (የሕብረት ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ መጠቀም) ፡[284] "ዩዛዥኤ ፡ ገዮዱሳን ፡ ኧን ፡ ኮሙን ፡" (በጋራ ፡ መጠቀምና ፡ መገልገል)[285] ፤ "አሎቲስማ ፡ ፕራቫቲፍ ፡ አ ፡ ቤኔፊስ ፡ ዴ ማምበር" ፡ (አባል ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ የተሰጠ ፡ የግል ፡ ድርሻ)[286] ፤ "ኩልቱርዝ ፡ ኧን ኮሙን ፡" (የተራድዖ ፡ እርሻ)[287] ፡ የሚሉት ፡ ናቸው ።

281. ኤፍ ፣ ኤ ፣ ኦ ፣ አይ ፣ ኤል ፣ ኦ ፣ እና ፡ ዩ ፡ ኤ ፡ ኤን ፣ ፕሮግሬስ ፡ ኢን ፡ ላንድ ፡ ሪፎርም ፣ ፎርዝ ፡ ሪፖርት ፣ (፲፱፻፷፯) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፷፯ ።
282. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፵፯ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ። በተለይም ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፵፱ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ፡ የሚገኙበት ፡ የአንቀጽ ፡ ዘጠኝ ፡ አርዕስት ፡ "በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቶች ፡ በኅብረት ፡ ስለመጠቀም ፡" ማለቱን ፡ በሚገባ ፡ ይገነዘቧል ።
283. ኤፍ ፡ ኤ ፡ ኦ ፡ እና ፡ ዩ ፡ ኤን ፡ አፍሪካን ፡ አግሪካልቸራል ፡ ዴቬሎፕሜንት ፤ ሪፍሌክሽንስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሚጀር ፡ ላይንስ ፡ ኦፍ ፡ አድቫንስ ፡ ኤንድ ፡ ዘ ፡ ባርየርስ ፡ ቱ ፡ ፕሮግሬስ ፤ ፩ሺ፱፻፷፯ ፡ እ.ኤ.አ. ገጽ ፡ ፺፱ ።
284. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ቍጥር ፡ ፩ ።
285. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፷፱ ፤ (ለምሳሌ) ።
286. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፶፬ ፤ (ለምሳሌ) ።
287. ከዚያው ፡ ቍጥር ፡ ፷፬ ፤ (ይህንኑ ፡ አርእስት ፡ አዝሎ ፡ ይገኛል ።)

የመጀመሪያው ፡ ሐረግ ፡ አንድ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ አባል ፡ የኅብረት ፡ በሆነው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ማለትም ፡ በሚታረስ ፡ መሬት ፤ በግጦሽና ፡ በቤት ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፤ ያለውን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ። የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፤ የኅብረት ፡ በሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ "የኅብረት ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ መጠቀም" ፡ በሚለው ፡ ላላ ፡ ባለው ፡ ሐረግ ፡ ተገልጧል ፡ ማለት ፡ ነው ።

"በጋራ ፡ መጠቀምና ፡ መገልገል ፡" የሚለው ፡ ሁለተኛው ፡ ሐረግ ፡ የሚያመለክተው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለእርሻ ፡ በማይውል ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ነው።

"የግል ፡ እርሻ" ፡ እና ፡ "የተራድኦ ፡ እርሻ" ፡ የሚሉት ፡ ቃላት ፡ የሚያመለክቱት ፡ የእርሻውን ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ "የተራድዖ ፡ እርሻ" ፡ የሚያመለክተው፡ በማኅበሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ አመራር ፡ ስር ፡ የሚካሄደውን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ሲሆን ፤ ተቃራኒውም ፡ በግል ፡ የሚካሄድ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ ፡ ሥር ፡ "በኅብረት ፡ መሠራት ፡" የሚለው ፡ አጭር ፡ ሐረግ ፡ የሚገልጸው ፡ የእርሻ ፡ ዘዴን ፡ ሳይሆን ፡ አንድ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ የኅብረት ፡ በሆነው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ መሆኑን፡ ይገነዘቧል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ (መ) ስር ፡ የታቀዱት ፡ "የአሠራር፡ ሁኔታ" ፡ ምርጫዎች ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ ሥር ፡ ተተንትነዋል ። በእርሻ ፡ ላይ ፡ ለሚውል ፡ መሬት ፡ የሚያገለግሉት ፡ "የአሠራር ፡ ሁኔታ ፡" ምርጫዎች ፡ የ"ተራድዖ" ፡ እና ፡ የ"ግል" ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ከቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ (፪) ለመረዳት ፡ ይቻላል ።

"የአሠራሩ ፡ ሁኔታ ፡" የተራድዖ ፡ እርሻ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፤ ይኸው ፡ ዘዴ ፡ በማኅበሩ ፡ መተዳደሩያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ በግልጽ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።[288] በተጨማሪም ፡ የማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ በኅብረቱ ፡ መሬቶች ፤ በግጦሽ ፡ መስኮችና ፡ ደኖችም ፡ ጭምር ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ በግልጽ ፡ መወሰን ፡ ይኖርባቸዋል ።[289]

ነገር ፡ ግን ፡ "የአሠራሩ ፡ ሁኔታ" ፡ የግል ፡ እርሻ ፡ ሲሆን ፡ የማኅበሩ ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ በግልጽ ፡ ማመልከትና ፡[290] በማንኛውም ፡ የኅብረት ፡ በሆነ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አባሎች ፡ ያላቸውን ፡ መብትና ፡ እንዲሁም ፡ ቀድሞ ፡ የተደረጉ ፡ የመሬት ፡ ክፍያ ፡ ድልድሎች ፡ የሚሻሻሉበትን ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ መወሰን ፡ ያስፈልገዋል ።[291] የተራድኦ ፡ እርሻ ፡ በሚካሄድበት ፡ ቦታ ፤ ይህን ፡ የመሬት ፡ ማከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ መጥቀስ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ አንባቢ ፡ እንዲገነዘበው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገር ፤ የሕጉን ፡ ረቂቅ፡ ለተመለከተና ፡ በመረመርናቸውም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ የግጦሽ ፡ መስክም ፡ ሆነ ፡ ለእንጨት ፡ የሚሆን ፡ ጫካ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ተቆርሶ ፡ የማይሰጥ፡

288. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ (፩) ።
289. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ (፪) ።
290. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ (፩) ።
291. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ (፫) ።

መሆኑን ፡ ላስታውስ ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ (መ) ፡ እና ፡ በከፊል ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፯፡ እና ፡ ፩ሺ፱፻፺፯ ፡ የተዘረዘሩት ፡ "የአሠራሩ ፡ ሁኔታዎች ፡" የእርሻ ፡ መሬትን ፡ እንጂ ፡ ለምሳሌ ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ አጠቃቀምን ፡ አለመመልከታቸውን ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ (መ) ፡ በእርሻ ፡ ላይ ፡ የሚውልንና ፡ የማይውልን ፡ መሬት ፡ የሚያ ጠቃልል ፡ ሲሆን ፤ ስለኋለኛው ፡ የመሬት ፡ ዓይነት ፡ ያቀደውም ፤ ለምሳሌ ፡ በአባሎች ፡ በግጦሽ ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ሊጣሉ ፡ የሚችሉትን ፡ ገደቦች ፡ ነው ።[292] እን ግዲህ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፯ ፡ እና ፡ ፩ሺ፱፻፺፯ ፡ ደግሞ ፡ የእርሻ ፡ መሬትን ፡ የሚመለከተ ውን ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ (መ) ን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ደንብ ፡ ለማሟላት ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ አቋምና ፡ ቁጥጥር ፤</u>

በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፤ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ስላ ላቸው ፡ ክፍሎች ፡ አቋም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምን ፡ እንደደነገገና ፤ ከተደራጁም፡ በኋላ ፡ ስለሚደረግባቸው ፡ ቁጥጥር ፡ የወሰነውን ፡ እንመለከታለን ።

የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ አቋም ፡ ለጊዜው ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በባሕል ፡ ስር ፡ የሚ ተዳደር ፡ ነው ፤ በመተዳደሪያ ፡ ደንባቸው ፡ ውስጥ ፡ (ለምሳሌ ፡ ያህል) ፡ "ለአስተዳደ ራቸው" ፡ አላፊ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ዘርዝረው ፡ እንዲያመለክቱ ፡ አልተገደዱም ።[293] እላይ ፡ እንዳየነውም ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ እንዲያወጡ ፡ ለማድረግ ፡ "እንዲያስብበት" ፡[294] እና ፡ ከዚያም ፡ የኅ ብረቱን ፡ የኤኮኖሚ ፡ እድገት ፡ ለማሻሻል ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተመሠረ ተበትን ፡ የፍትኅንና ፡ የሞራልን ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳቦች ፡ በመከተል ፡ ከነገሩ ፡ አካባቢ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ የኅብረቱ ፡ ልማዶች ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ለማድረግ ፡[295] እንዲሁ ፡ እንዲያስብበት ፡ ተደርጓል ።

ቀደም ፡ ሲንልም ፡ ያመለከትናቸው ፡ የማኅበሮቹ ፡ "ወኪሎች ፡"[296] በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያላቸው ፡ ሥራና ፡ ጥቅም ፡ እጅግ ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ማመን ፡ ይገባል ። ብዙዎች ፡ ማኅበሮች ፡ የራሳቸውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ ያወጣሉ ፡ ቢባልም ፡እንኳ፡ አሁን ፡ የሰነዘርነው ፡ አስተያየት ፡ እውነተኛነት ፡ አይለወጥም ። ይህ ፡ የተባለበ ትም ፡ ምክንያት ፡ ወኪሎችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ የታቀዱት ፡ የተራድዖ ፡ እርሻን ፡ ለሚከተሉ ፡ ግዴታ ፡ ሊገባላቸው ፡ መብትም ፡ ሊገ ኝላቸው ፡ ለሚችሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ስለሆነ ፤ ነው ።

---

292. በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የታቀደው ፡ የአሠራር ፡ "ዘዴ" ፡ ይህ ፡ ነበር ። ዳቪድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ እና ፡ ፫፩ ።

293. በቍጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ (ሐ) ፡ ሥር ፡ የታቀዱት ፡ "አስተዳዳሪዎች" ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፤ በክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተናቸዋል ።

294. አገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ እስካሁን ፡ ምን ፡ እንደሰራ ፡ ለማወቅ ፡ አቶ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል፡ ከበደ ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አነጋግረው ፡ ነበር ። ኃ/ ሚካኤል ፡ ከበደ ፡ <u>ዘ ፡ ኢምፓ ክት ፡ ኦፍ ፡ ላንድ ፡ ቴኒየር ፡ ኦን ፡ ላንድ ፡ ዶዜጅ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ</u> ፡ (የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨ ርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፤ ያልታተመ) ፡ ገጽ ፡ ፲ ፤ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፰ ፡ ሥር ።

295. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፰ ፡ (፩) ። ከበድ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ መመሪያን ፡ ለመግለጥ ፡ የገቡ ፡ እንጂ ፡ የተወሰነ ፡ ትርጉም ፡ የላቸውም ።

296. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፩ ፡ (ሐ) ፡ እና ፡ ፩ሺ፱፻፺፱ ።

ስለዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ በተራድዖ ፡ ካላረሱ ፡ በስተቀር ፣ ወኪሎችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕጐች ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ሊኖረው ፡ የሚችል ፡ ድርጅት ፡ በሌለበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ ጥቅም ፡ አይሰጡም ።

አንድ ፡ ማኅበር ፡ መሬቶችን ፡ በተራድዖ ፡ ለማሳረስ ፡ ሲወስንና ፡ ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ወኪሎች ፡ ሲመርጥ ፣ ወኪሎቹ ፡ ለፈጸሙት ፡ አድራጎት ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ ተሟልተው ፡ ሲገኙ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ኣላፊነት ፡ ይኖርበታል ፤ እነዚህም ፡ (፩) ወኪሎቹ ፡ የሠሯቸው ፡ ወይም ፡ ሳይፈጽሟቸው ፡ የቀሩት ፡ ተግባሮች ፡ ግዴታዎች ፡ ሲሆኑና ፣ (፪) አላፊነትንም ፡ አስከትለው ፡ እንደሆን ፡ ነው ።[297] እንደዚሁም ፡ ወኪሎቹ ፡ ከፈጸሙት ፡ ተግባር ፡ የተነሳ ፡ ማኅበሩ ፡ ያለአግባብ ፡ በልጽጎ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆን ፡ በሕግ ፡ ይጠየቃል ፤ ብልጽግናው ፡ የተገኘው ፡ ከሥልጣን፡ ውጪ ፡ በተፈጸመ ፡ ሥራ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ለውጥ ፡ አያመጣም ፤ ማኅበሩ ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ አቋም ፡ በልማድ ፡ የሚተዳደር ፡ ቢሆንም ፣ ቁጥጥራቸው ፡ ግን ፡ በሚገባ ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ተደንግጐ ፡ ይገኛል ።

አንደኛ ፤ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ የግል ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ እንዲኖራቸው ፡ ጥረት ፡ ሲያደርግ ፣ ልማዳቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ መልክ ፡ እንዲሆን ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ የሚሻሻልበትን ፡ መንገድ ፡ አጥንቶ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ። የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ እንደገለጡት ፣ "(የነዚህ ፡ ማኅበሮች ፣) የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ የታቀዱት ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ መንገድ ፡ አጥንቶ ፡ ሊያሻሽላቸው ፡ እንደሚችል ፡ ሆነው ፡ ነው ።"[298] እንግዲህ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተጽዕኖ ፡ ይበልጥ ፡ የሚታየው ፣ ልማድ ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውልበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ተጨማሪ ፡ የሚሆኑ ፡ ደንቦች ፡ ሲያወጣ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ "ተጨማሪ ፡ ደንቦች ፡" በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆናቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው ፤ ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ እያደገ ፣ ትምህርትና ፡ እውቀትም፡ እየተስፋፋ ፡ ሲሄድ ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ ስለሚገኝና ፣ በልማድም ፡ ብዙ ፡ ጉድለት ፡ ሊታይበት ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ተጨማሪ ፡ ደንቦች ፡ ሊመለከቱ ፡ የሚችሉት ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ መብትን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፣ የማኅበሮችን ፡ መሠረታዊ ፡ አቋምና ፡ ከጊዜው ፡ ፍልስፍናና ፡ እምነትም ፡ ጋር ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡንም ፡ የአስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

ስለዚህም ፣ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ "የሕግ ፡ አማካሪ ፡" በመሆን ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲኖራቸውና፡ ሲያስፈልግም ፡ እንዲሻሻል ፡ የሚያደርግላቸው ፡ ስለሆነ ፡ ተጽዕኖው ፡ ታላቅ ፡ ነው።

በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተደነነገው ፡ ሌላው ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ ዘዴ፡ በተባሉት ፡ ማኅበሮች ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ገደብ ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ ልማድ ፡ ቢኖርም ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴርን ፡ ካላስፈቀደ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ መሬቶቹን ፡ ለመሸጥ ፣ ለሌላ ፡ ለማስተላለፍ ፣ በዕዳ ፡ ለማስያዝ ፡ ወይም ፡ ለወለድ ፡ አግድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።[299] እንዲሁም ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡

297. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፶፯ ፤ በቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፶፰ ፡ (፫) ።
298. ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫ ።
299. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፶፫ ፡ (፩) ።

የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የኅብረት ፡ የሆነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለማስከበር ፡ ሲፈልጉ ፡ አስቀድመው ፡ ማስፈቀድ ፡ አለባቸው ።[300]

ሦስተኛው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፡ ለዳኞች ፡ አቤቱታ ፡ ስለማቅረብ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱፡ እና ፡ ፩ሺ፫፻፪ ፡ በተዘረዘረው ፡ መሠረት ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ባላቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ የተጣለው ፡ የቁጥጥር ፡ ዘዴ ፡ ነው ። የኋለኛው ፡ ቁጥር ፡ አርእስት፡ "ፀጥታን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነገሮች ፡" ቢሆንም ፡ የመጀመሪያው ፡ ቁጥር ፡ ቅጥያ ፡ መሆኑ ግልጽ ፡ ነው ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱ ፡ መሠረት ፣ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ "የኅብረቱ ፡ ፍላጐት" ፡ ተቆርቋሪ ፡ እንደሆነ ፡ ተደርጐ ፡ እንዲገመት ፡ ተደንግጓል ። በተባሉት ፡ ማኅበሮች ፡ አጠገብ ፡ በመገኘት ፡ የዕለት ፡ ተግባራቸውን ፡ ሲያከናውኑ ፡ ሊመለከት ፡ የሚችለው፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፣ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይልቅ ፡ የተሻሻለ ፡ ቁጥጥር ፡ ለማድረግ ፡ መቻሉ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በማኅበሩ ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ የሚያገባው ፡ በመሆኑ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በተሰጠው ፡ የአቤቱታ ፡ መብት ፡ በመጠቀም ፡ ቁጥጥር ፡ ለማድረግም ፡ ይችላል ።[301] በቁጥር ፡ ፩ሺ፫፻፪ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ባይነገርም ፡ ማኅበሩ ፡[302] ወይም ፡ ወኪሎቹ ፡[303] ባሳለፏቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችለው ፡ አቤቱታ ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በኅብረቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ገደብ ፡ ሊደረግበት ፡ ይችላል ። የማኅበሩ ፡ ወኪሎች ፡ የሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ "ከሥልጣን ፡ በላይ ፡ የሆነ" ፡ ወይም ፡ "የሥነ ፡ ሥርዓትንና ፡ የፍትኀን ፡ ነገር ፡ በመተላለፍ ፡ የተሰጠ ፡" ማለት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ በአእምሮ ፡ ለመገመት ፡ አስቸጋሪ ፡ እንደመሆኑ ፡ ሁሉ ፡[304] ገደብ ፡ ሊደረግለት ፡ የሚቻል ፡ ወይም ፡ የማይቻል ፡ አቤቱታ ፡ እንዴት ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ ለመገመት ፡ አዳጋች ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ በአጥጋቢ ፡ ሁኔታ ፡ ሊመለሱ ፡ የሚችሉት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በፍርድ ፡ መልክ ፡ በሚወስኑበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፣ ክርክር ፡ በቀረበበትም ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ከመስጠታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ውሳኔውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የነገሩንም ፡ አዝማሚያና ፡ ሁኔታ ፡ በሚገባ ፡ መመልከት ፡ አለባቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ ዘዴዎች ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ትርጉም ፡ ያለውና ፡ ጠበቅ ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ የሚታየውም ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱፡ ስር፡ የተጠቀሰው ፣ በተለይም ፡ ማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ሰው ፡ ሊያቀርበው ፡ የሚችለው ፡ አቤቱታ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ አባል ፡ ማኅበሩ ፡ ያስተላለፈውን ፡ ውሳኔ ፡ ተቃውሞ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ሲችል ፡ አቤቱታውን ፡ ያላቀረበ ፡ እንደሆነ ፣ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አቤቱታውን ፡ ያቀርብለታል ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ያዳግታል ። ይልቁንም ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጁ ፣ ሌሎች ፡ እሱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ጉዳዮች ፡ መኖራቸውን ፡ ስለምናውቅ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ አቤቱታዎች ፡ ለማቅረብ ፡ እምብዛም ፡ የሚያስብበት ፡ መስሎ ፡ አይታየንም ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የተባለውን ፡ አቤቱታ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሕጉ ፣ ማለትም ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱ ፣ የማያስገድደው ፡ መሆኑንና ፡ የአቤቱታ ፡ ማቅረቡም ፡ ጉዳይ ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የግል ፡ ምርጫ ፡ እንደሆነ ፡ መገንዘብ ፡ ይገባናል ።

---

300. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፰ ፡ (፪) ።
301. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱ ።
302. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱ ፡ (፩) ።
303. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፱ ፡ (፪) ።
304. ከዚያው ።

የአንድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፶፱ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ አቤቱታ ፡ ሲያቀርብ ፣ ውሳኔው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ምንጊዜም ፡ ሊከበሩ ፡ ከሚገባቸው ፡ ሊታለፉ ፡ ከማይችሉ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቃላት ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጐች ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ መሆናቸውን ፡ መግለጥና ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብም ፡ ዝግጁ ፡ መሆን ፡ ይኖርበታል ። ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ለመጣሱ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ይመስላል ። ሆኖም ፡ ሊከበሩ ፡ የሚገባቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቃላት ፡ ለመጣሳቸው ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ተጣሱ ፡ የሚላቸው ፡ የሕግ ፡ ቃላት ፡ ምንጊዜም ፡ መከበር ፡ ያለባቸው ፡ መሆናቸውን ፡ አስቀድሞ ፡ ማሳየት ፡ አለበት ።

ከሺ፱፻፷፱—ሺ፳፻፪ ፡ ባሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ሥር ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ላለው ፡ ክፍል ፡ አባሎች ፡ የተሰጡትን ፡ መብቶች ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ በይግባኝ ፡ ባይ ፡ በወ/ወለተ ፡ ሥላሴ ፡ ገብረ ፡ መድኅንና ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ በባላም/ገብረ ፡ ኪዳን ፡ አብርሃ ፡[305] መሀከል ፡ በቀረበው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ ባጭሩ ፡ ገልጿቸዋል ። አንድ ፡ አባል ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ቢፈልግ ፡ ክሱን ፡ በይግባኙ ፡ ድንጋጌ ፣ ማለትም ፣ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፶፱ ፡ ላይ ፡ መመሥረት ፡ ይኖርበታል ፤ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቷል ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፶፱ ፡ ላይ ፡ ያልተመሠረተ ፡ በመሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቷል ።[306] ከጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ለመረዳት ፡ የሚቻለው ፣ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፷፪ ፡ የግድ ፡ መከበር ፡ ካለባቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ መሆኑን ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ቁጥር ፡ ሲጣስ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፷፱ ፡ (፩) ፡ ሥር ፡ የተመለከተውን ፡ የይግባኝ ፡ መብት ፡ ያሳጣል ። በዚህም ፡ መሠረት ፣ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ከአባሎቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹ ፡ የተለየ ፡ ሃይማኖት ፡ ይከተላሉ ፣ በማለት ፡ የመሬት ፡ ክፍያ ፡ ቢከለክላቸው ፣ ውሳኔው ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ በሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ በአባሎች ፡ መሀከል ፡ ልዩነት ፡ እንዳያደርጉ፡ ሲል ፡ የሚደነግገውን ፡ ቁጥር ሺ፱፻፷፪ትን ፡ የሚቃረን ፡ ይሆናል ። እንደ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድም ፣ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ በቁጥር ፡ ሺ፱፻፷፱ ፡ (፩) መሠረት ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

ቁጥር ፡ ሺ፱፻፷፪ን ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መተርጐም ፡ ትክክል ፡ አይመስልም ። ምክንያቱም ፡ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፶፱ ፡ (፩)ን ፡ ለሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ቁጥር ፡ ሺ፱፻፷፪ ፡

305. የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ወ/ወለተ ፡ ሥላሴ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ መልስ ፡ ሰጭና ፡ የባላም ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፡ አብርሃ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፶፱ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፴፩/፶፱ ፡ ያልታተመ) ፡ ጉዳይ ።

306. በይግባኝ ፡ ባይ ፡ በአረጋዊ ፡ ናይዝጊና ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ በአረጋ ፡ መንክር ፡ (ጠ- ን- ነ- ፍ- ፡ ቤት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፲፩/፶፱) ፡ (ያልታተመ) ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ተመሳሳይ ፡ ውሳኔ ፡ ተሰጥቷል ። በዚህና ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በተጠቀሰው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመራርና ፡ ውሳኔ ፡ እጅግ ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ።
በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፣ በክቡር ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ መዛግብት ፡ እንዲመረምር ተፈቅዶለት ፡ ነበር ። ከሺ፱፻፶፰—ሺ፱፻፶፱ ፡ ዓ- ም- የተከፈቱትን ፡ ፋይሎች ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፣ ከቁጥር ፡ ሺ፱፻፷፱ - ሺ፳፻፪ ፡ ያሉት ፡ ደንቦች ፡ የተጠቀሱባቸው ፡ ሦስት ፡ ጉዳዮች ፡ አጋጥመውታል ። በሦስቱም ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ የተመራበት ፡ ሐሳብና ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ከላይ ፡ ባጭሩ ፡ ተገልጾአል ። ሦስተኛው ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ሳይጠቀስ ፡ የታለፈበት ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቀሩት ፡ በሁለቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የታከለውን ፡ ሐሳብና ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ እዚህኛውም ፡ ላይ ፡ መልሶ ፡ ስለሚጠቀሰውና ፡ አዲስ ፡ ነገርም ፡ ስላልጨመረ ፡ ነው ።

አግባብ ፡ የሚኖረው ፡ ተቃውሞ ፡ የቀረበበት ፡ ውሳኔ ፡ በቁጥር ሺ፬፻፶፮ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ፡ መሠረት ፡ በተደነገገ ፡ ወይም ፡ በሚደነገግ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምሮ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

የቁጥር ፡ ሺ፬፻፷፪ን ፡ ድንጋጌ ፡ ጠቃሚነት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ማጋነን ፡ የሚቻል ፡ አይመስልም ። የዚህ ፡ ቁጥር ፡ ዓላማ ፡ በክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ የመረመርናቸውን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡን ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም ፡ ለመደምሰስ ፡ ነው ። ይህ ፡ አቋም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዘመናዊ ፤ መሠረታውያን ፡ ሀሳቦች ፡ የሚፃረር ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በቁጥር ፡ ሺ፬፻፷፪ ፡ መሠረት ፡ ልማድ ፡ ወይም ፡ ልማድን ፡ አቀናብሮ ፡ የያዘ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ጥንትም ፡ መብት ፡ ያልነበራቸውን ፡ ሰዎች ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ከሆኑት ፡ “ሰዎች” ፡ ወይም ፡ “ቤተ ፡ ዘመዶች” ፡ ነጥሎ ፡ ሊለያቸው፡ አይችልም ።[307] በተጨማሪም ፡ እነዚህ ፡ አባሎች ፡ ማኅበሩን ፡ ከማስተዳደርና ፡ ለማኅበሩም ፡ ወኪል ፡ ከመሆን ፡ የሚያግዳቸው ፡ አይኖርም ፤ (ሁለቱም ፡ ተግባሮች ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፶፮ ፡ (ሐ) ሥር ፡ ዘላቂ ፡ መልክ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ይገኛል ። ) ከሁሉም ፡ የሚበልጠው ፡ መከላከያቸው ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ተከፋፍለው ፡ የሚደለደሉት ፡ በዘር ፤ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ በመመራት ፡ አለመሆኑ ፡ ነው ።[308] እዚህ ፡ ላይ ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ መሬትን ፡ የማከፋፈል ፡ “አኳኋን” ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ በአንዳንድ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶችና ፡ በመንደሮች ፡ ዘንድ ፡ መሬት ፡ ከመታደሉ ፡ በፊት ፡ የሚደረገውን ፡ የዕጣ ፡ ማውጣት ፡ ሁኔታንም ፡ ጭምር ፡ ማመልከቱን ፡ ነው ።

ከላይ ፡ ባመለከትናቸው ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ቁጥር ፡ ሺ፬፻፷፪ ፡ ዘመናዊና ፡ በክፍል ፡ አንድ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከትናቸው ፡ ልማዳዊ ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍሎችም ፡ ውስጥ ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዘልማድ ፡ ተቀዳሚ ፡ በሆነው ፡ እንዲያውም ፡ ምትክ፡ በማይገኝለት ፡ መተዳደሪያቸው ፡ ላይ ፡ መሠረታዊ ፡ የሆኑ ፡ መብቶችን ፡ ተነፍገው ፡ ለነበሩት ፡ ወገኖች ፡ <u>የእኩልነት ፡ መብት ፡ የሚያረጋግጥ</u> ፡ ቁጥር ፡ ነው ። “በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለኑሮው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መብቶቹንና ፡ ግዴታዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ያለችግር ፡ እንዲገባው ፡ ለማድረግ ፡ አቅደን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ቃላቶች ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ እንዲዘጋጁ ፡ አድርገናል ። ” ፡ ቀ-ኃ-ሥ ፤ መግቢያ ፤ <u>የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ</u> ፤

## <u>ክፍል ፡ ፫ ፡ መደምደሚያና ፡ አስተያየት</u> ፤

### <u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ መደምደሚያ</u> ፤

ለመደምደሚያ ፡ ያህል ፡ “የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የርሻ ፡ መሬቶች ፡” በሚለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መሠረተ ፡ ሀሳቦች ፡ በአጭሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ እናጠቃልላለን ።

---

307. ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፮ ፡ (ሀ)ንና ፡ ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፪ን ፡ ባንድነት ፡ በማንበብ ።
308. ቍጥር ፡ ሺ፬፻፶፮ ፡ (መ)ንና ፡ ሺ፬፻፶፪ትን ፡ በማጣመር ፡

በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፤ የኅብረት ፡ (የደ ሽ) ፡ የሆኑ ፡ እንደጐሣ ፣ ቤተሰብ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብትነት፡ ለአንድ ፡ "የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሉት ፡ ክፍል" ፡ ለተባለ ፡ ማኅበ ራዊ ፡ አካል ፡ ተሰጥቷል ። ይህም ፡ "ማኅበር" ፡ ቤተሰብ ፤ መንደር ፤ ወይም ፡ ጐሣ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የሕግ ፡ ሰውነት ፡ ስላለውም ፤ ለአባሎቹ ፡ ከተሰጡት ፡ የተለዩ ፤ የራሱ ፡ የሆኑ ፡ የግል ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ አሉት ።

ስለዚህ ፡ ጥንት ፡ የዘር ፡ ወይም ፡ የመንደርንና ፡ የጐሣን ፡ የርስት ፡ ስሪት ፡ ለመግ ለጥ ፡ እንጠቀምበት ፡ የነበረው ፡ "የኅብረት ፡ ባለቤትነት" ፡ የሚለው ፡ ስያሜ ፡ በሕጉ ፡ ሥር ፡ ጊዜው ፡ ያለፈበት ፡ ይመስላል ። የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያ ሉት ፡ የኅብረ ፡ ሰብኡ ፡ ክፍል ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ የግል ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚያሳዩትን ፡ ጠባይ ፣ ማለት ፡ በአባሎች ፡ መፈጠርና ፡ መብትም ፡ መሰጠትን ፣ ባለማሳየቱ ፡ ነው ። በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፣ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ማኅበሮች ፡ በሕግ ፡ ተፈጥረው ፡ በአባሎቻቸው ፡ ላይ ፡ የተጫኑ ፡ ቢሆኑም ፡ የሕዝብ ፡ ድርጅቶች ፡ አይደሉም ፤ ምክንያቱም ፡ አንዳችም ፡ ለሕዝብ ፡ የሚ ሆኑ ፡ አገልግሎት ፡ ስለማያበረክቱና ፡ ይኸንንም ፡ የመሰለ ፡ "የሕግ ፡ ሰውነት" ፡ በሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ቃል ፡ ስላልተሰጣቸው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፣ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎች ፡ ከሌሎች ፡ ማኅበሮች ፡ የማይገጥም ፣ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የተለየ ፡ ክፍል ፡ እንዳላቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ። የሕግ ፡ ፍጡራን ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠንም ፣ በአባሎቻቸው ፡ ፈቃድ ፡ ሊፈርሱና ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብታቸውን ፡ ሊነፈጉ ፡ አይችሉም ።

አንዳንድ ፡ ጥንታውያን ፡ የሆኑ ፣ የቤተ ፡ ሰብ ፣ የመንደርና ፡ የጐሣ ፡ አባሎችን ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ የሚያስተዳድሩ ፡ በባሕልና በልማድ ፡ ያልተረጋገጡ ፡ ደንቦ ችን ፡ ለማጣራት ፡ ያህል ፡ አባሎቹ ፡ የራሳቸውን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ በዝርዝር ፡ የሚ ገልጡበት፡የመተዳደሪያ ፡ ደንብ፡እንዲያወጡ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ይፈቅድላቸ ዋል ። ይህም ፡ ሲደረግ ፡ በተለይ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፩ ፡ ሥር ፡ የተዘረዘሩትን ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ውስጥ ፡ በግልጥ ፡ ማመልከትና ፡ ደንቡም ፡ ሲጻፍ ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመከተል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ይሁንና ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ "ማኅበሮች" ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ የራሳቸውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያወጣሉ ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ የሚያዳ ግት ፡ በመሆኑና ፡ በአሁኑም ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚወ ተውት ፡ ድርጅት ፡ ባለ ፡ መኖሩ ፣ የፍ/ብሔሩ ፡ ሕግ ፣ በቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፺፪ ፡ አማካይ ነት ፣ በልማድ ፡ ውስጥ ፡ ሊገኙ ፡ የሚችሉትን ፡ የማይገቡ ፡ ደንቦች ፣ በተለይም ፡ የማኅበሩን ፡ የዕለት ፡ ኑሮ ፡ አስተዳደር ፡ የሚመለከቱትን ፤ እንዲወገዱ ፡ አድርጓል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ከማውጣቱ ፡ በፊት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ አቋምና ፡ ድርጅት ፡ እንደሚኖረው ፡ ለማወቅ ፡ ቢያዳግትም ፣ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ በማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ መካከል ፡ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ፡ ደረጃ ፡ አቋም ፡ መሠረት ፣ ከማኅበሩ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ማንም ፡ እንዳይወገድ ፡ ሕጉ፡ ዋስትና ፡ ይሰጣል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ሕጉ ፡ ከልማድ ፡ ከተለየ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ አስተዋውቆናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

በሕጉ ፡ ሥር ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎች ፣ ማለት ፡ የተራድዖና ፡ የግል ፡ እርሻ ፡ ዘዴዎች ፡ ታቅደዋል ። አንድ ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች፡ያሉት ፡ ክፍል፡ የፈለገውን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ሊመርጥ ፡ ይችላል ፤ ይሁንና ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡

ውስጥ ፡ የመረጠውን ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ በግልጽ ፡ ማስፈር ፡ አለበት ። በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፬ ፡ እና ፡ ፩ሺ፱፻፺፬ ፡ ሀ/ ሥር ፡ ለነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ የተሰጡት ፡ መብቶች ፡ ለተራድዖ ፡ እርሻ ፡ ሥራ ፡ እንዳያመቹ ፡ ተደርገው ፡ የተመረጡ ፡ ይመስላሉ ።

በመሠረቱ ፤ ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ የቁጥጥር፡ ዘዴ ፡ ተደርጐባቸዋል ። አንደኛው ፡ በሥልጣናቸው ፡ ላይ ፡ የተጣለው ፡ ገደብ ፡ ነው ። ቁጥሮች ፡ ፩ሺ፱፻፺፫ ፡ (፪) ፤ ፩ሺ፱፻፺፭ ፡ ሀ/ ፤ ፩ሺ፱፻፺፯ ፤ እና ፡ ፩ሺ፰፻ን ፡ ይመለከቷል ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፱ ፡ መሠረት ፡ በአቤቱታ ፡ መልክ ፡ የተጣለው ፡ ገደብ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለቱ ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ ዘዴዎች ፡ ይበልጥ ፡ ጠቃሚውና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውልም ፡ የሚችለው ፡ ሁለተኛው ፡ የአቤቱታው ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ማኅበሮች ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ እስኪያወጡና ፡ በሚገባም ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ እስኪችሉ ፡ ድረስ ፡ በሕጉ ፡ የተደረገው ፡ ምርጫ ፡ በኢኮኖሚ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፤ ሊደረግ ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መፍረድ ፡ አይቻልም ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የሕግ ፡ አውጪውን ፡ ሁለት ፡ ተቃራኒ ፡ ዓላማዎች ፤ ማለትም ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ማኅበሮቹ ፡ ባሕልና ፡ ልማዳቸውን ፡ ጠብቀው ፡ እንዲኖሩ ፡ የሚለውን ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ እንዲያገኙ ፡ የሚለውን ፤ ማስተዋል ፡ ይገባዋል ።

የቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መኖር ፡ ዋናው ፡ ውጤት፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ በጣም ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መሬት ፡ ከተራዎቹ ፡ የሕጉ ፡ ክፍል ፡ ደንቦች ፡ ክልል ፡ ውጪ ፡ ማድረጉ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የመረመርናቸው ፤ ሕግ ፡ አውጭው ፡ አቅዷቸው ፡ የነበሩትን ፡ ክፍሎች ፡ ሊያስረዱ ፡ የሚችሉትን ፡ በኤርትራ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ የሚገኙትን ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸውን ፡ ክፍሎች ፡ ብቻ ፡ ቢሆንም ፤ በቤገምድር ፤ ጐጃም ፤ ሸዋና ፡ ወሎ ፡ የሚገኙ ፡ የዘር ፡ ርስት ፡ የሚባል ፡ ስሪት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ሥር ፡ የሚተዳደሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ልንገልጥ ፡ እንወዳለን ። በነዚህም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ረቂቅ ፡ ለሆነ ፡ የሕግ ፡ ፍጡር ፡ ተሰጥቷል ።

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ አስተያየት ፤</u>

የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ቁጥሮች ፡ ለብዙዎች ፤ በተለይም ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ እንዲያስፈጽሟቸው ፡ ለታቀዱት ፤ ሰዎች ፤ አንዳችም ፡ ትርጉም ፡ አይሰጡም ። እንዲያውም ፡ አንድ ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ። የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደፊት ፡ የገፉትንና ፡ የተብራራ ፤ በጽሑፍ ፡ የሰፈረ ፡ የባሕል ፡ ሕግ ፡ ያላቸውን ፡ ክፍሎች ፡ እንኳን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲያወጡ ፡ ያላደረገበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ የቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፹፱ን ፡ እና ፡ የተታዮቹን ፡ ቁጥሮች ፡ ትርጉምና፡ ዓላማ ፡ በሚገባ ፡ ባለመረዳት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።[309]

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ ያቀደውን ፡ ዓላማና ፡ የደነገገውንም ፡ ለማስረዳት ፡ በመሞከር ፡ የዚህ፡ ጽሑፍ ፡ አንባቢው ፡ ሕግን ፡ የማይመለከቱ ፡ ጽሑፎችን ፡ እንዲመለከት ፡ ደራሲው ፡ አስገድዶታል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡

309. ወይም ፡ አስፈላጊው ፡ ገንዘብና ፡ የሰው ፡ ኃይል ፡ ስላልተሟላለት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

እንብቦ ፤ ተረድቶ ፡ ይጠቀምበታል ፡ ብለን ፡ ብንገምትም ፡ እንኳን ፤ ጽሑፉን ፡ በቀላሉ ፡ ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲው ፡ ሲያዘጋጅ ፡ በአማርኛው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቃል ፡ እምብዛም ፡ አለመመራቱን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መግለጥ ፡ ይገባዋል ፤ ይህም ፡ የሆነበት ፡ የአማርኛው ፡ ቃል ፡ እንደእንግሊዝኛው ፡ ቅጂ ፡ ግልጽ ፡ ባለመሆኑና ፡ በተራድዖ ፡ የሚታረሱ ፡ እርሻዎች ፡ የተቋቋሙ ፡ አስመስሎ ፡ ስለሚደነግግ ፡ ነው ።

በተመረመረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ችግሮች ፡ በመመልከት ፤ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ እንዲሻሻሉ ፡ አስተያየት ፡ እናቀርባለን ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚከተሉት ፡ እርምጃዎች ፡ መወሰድ ፡ ይኖርባቸዋል ።

፩/ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሕጉ ፡ እንዲሻሻል ፡ ተቀዳሚ ፡ እርምጃ ፡ መውሰድና ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ያለውን ፡ ኃላፊነት ፡ ሥራው ፡ ሊመለከተው ፡ ለሚገባ ፡ በአሁኑ ፡ የመንግሥት ፡ አቋም ፡ ሥር ፡ ተገቢ ፡ ለሆነው ፡ ሌላ ፡ ሚኒስቴር፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ ማስተላለፍ ፡ ይገባዋል ።

፪/ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻልን ፡ የሚመለከት ፡ እቅድ ፡ እንዲያካሄድ ፡ የመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴርን ፡ የመረጠው ፡ ስለሆነ ፡[310] የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎች ፡ በዚሁ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥር ፡ ቢተዳደሩ ፡ መልካም ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በሚሻሻልበት ፡ ጊዜ ፡ በአሁኑ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፷፰ ፡ እና ፡ ፩ሺ፩፻፺፫ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተግባሮች ፡ በመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲያከናውኑ ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

፫/ የመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ አሁን ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር፡ ላይ ፡ የተጣለውን ፡ ግዴታ ፡ ለማከናወን ፡ ተስማሚ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ እርሻ ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከተው ፡ የሕጉ ፡ ክፍል ፡ ሲታወጅ ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፡ እቅድ ፡ በመሆኑና ፡ አንድ ፡ ዓይነት፡ የተለየ ፡ የግል ፡ የመሬት ፡ ይዞታን ፡ ለማስተዋወቅ ፡ የተወሰደ ፡ ጊዜያዊ ፡ እርምጃ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

፬/ ምንም ፡ እንኳን ፤ በክፍል ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከትነው ፤ በልማድ ፡ በተያዘው «በኅብረት ፡ ስሪት ፡» ቅንጅት ፡ ሥር ፡ ብዙ ፡ ጐጂ ፡ ነገሮች ፡ መኖራቸው፡ ባይካድም ፤ የሕጉ ፡ ምርጫ ፡ በመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ በሚገባ ፡ ሊታወቅ ፡ ይገባል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ተቃራኒና ፡ ተደራራቢ ፡ የሆኑ ፡ ፖሊሲዎችን ፡ ከመከተል ፡ ለመዳን ፡ የሕጉን ፡ አርቃቂ ፡ ማስታወሻዎች ፡ በሚገባ ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል ።

፭/ የመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ መዝገብ ፡ በማዘጋጀት ፡ ረገድ ፡ የተጣለበትን ፡ ኃላፊነት ፡[311] ለማሟላት ፡ የኅብ

310. የሚኒስትሮች ፡ (ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ አወሳሰን) ፡ ማሻሻያ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ትእዛዝ ፤ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ፤ ቍጥር ፡ ፲፰ ፤ ትእዛዝ ፡ ፵፮ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፤ ቍጥር ፡ ፳፫ ።

311. ከዚያው ፤ ቍጥር ፡ ፲፰ ፡ (ረ) ።

ረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶችን ፡ በሚመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ምዕራፍ ፡ በሚገባ ፡ ለመጠቀም ፡ ይችላል ። እላይ ፡ እንዳሳየነው ፡ የቤተሰብ ፣ የጕሳና ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ ባለቤትነት ፡ ግዙፍነት ፡ ለሌላው ፡ የሕግ ፡ ፍጡር ፡ ስለተሰጠ ፡ ይህን ፡ በቀላሉ ፡ እንደባለቤት ፡ ለመመዝገብ ፡ ይቻ ላል ። ስለዚህም ፡ ሚኒስቴሩ ፡ የቤተሰቡን ፣ የጕሣውን ፡ ወይም ፡ የመንደሩን ፡ መሬት፡ስም ፡ ብቻ ፡ ከመዘገበ ፡ በኋላ ፡ የየክፍሉን ፡ አባሎች ፡ ማንነት ፡ ለየማ ኅበሩ ፡ ሊተወው ፡ ይችላል ። የነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ አባሎች ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ መሬቶችን ፡ ለመመዝገብ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

፮/ በሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ውስጥ ፡ የመሬት ፡ ይዞታን ፡ በመላ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግ ሥት ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማ ፡ ተደርጎ ፡ ታቅዷል ።[312] የመሬትም ፡ ይዞታ ፡ የሚያ መራው ፡ እላይ ፡ እንዳየነው ፡ ተስፋፍቶ ፡ ወደሚገኘው ፡ ወደግል ፡ ይዞታ ፡ ነው ። የኅብረት ፡ ስሪት ፡ ወደግል ፡ ስሪት ፡ መለወጡ ፡ አይቀርም ፤ ሕጉም ፡ በተባለው ፡ ስሪት ፡ ሥር ፡ ያሉትን ፡ መሬቶች ፡ ባለሀብትነት ፡ በመጀመሪያ ፡ ግዙፍነት ፡ ለሌላው ፡ አንድ ፡ ግለኛ ፡ ለሆነ ፡ የሕግ ፡ አካል ፡ በመስጠት ፡ መስ መሩን ፡ ወደግል ፡ ይዞታ ፡ እንዲያመራ ፡ አድርጓል ፤ የሚለውን ፡ አስተሳሰብ ፡ ከተቀበልን ፤ ለዚሁ ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፡ አላፊ ፡ ይሁን ፡ ስንል ፡ ያሳስ ብነው ፡ ሚኒስቴር ፤ የሚከተሉትን ፡ እርምጃዎች ፡ መውሰድ ፡ አለበት ።

፯/ ሚኒስቴሩ ፤ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ ያሏቸው ፡ ክፍሎች ፡ የመተዳደ ሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ እንዲያወጡ ፡ መገፋፋት ፡ ይኖርበታል ። እንደዚህ ፡ ካልተደ ረገ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የተወሰዱት ፡ እርምጃዎች ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትርጉም ፡ አይሮራቸውም ።

፰/ ሚኒስቴሩ ፤ ሙሴ ፡ ዳቪድ ፡ ያረቀቁትን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ሞዴል፡ ለማሳየት ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፹፱ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡ ቁጥሮች ፡ በሚመለከቱዋ ቸው ፡ ቀበሌዎች ፡ ውስጥ ፡ በቀላሉ ፡ አባዝቶ ፡ ለተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ማደል ፡ ይችላል ።

፱/ የዚህ ፡ "የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ረቂቅ" ፡ መታደል ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ ጉዳዩ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ስለ ፡ "አዲሱ" ፡ የኑሮ ፡ ስልታቸው ፡ ለማስረ ዳትና ፡ በተለይም ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ በሚያወጡበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ፡ ምሳሌ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የሚችሉትን ፡ መመሪያ ፡ ለመስጠት ፡ ነው ።

፲/ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ረቂቆች ፡ ከታደሉና ፡ ማኅበሮችም ፡ በሚገባ ፡ ጉዳዩ ፡ እንዲገባቸው ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፤ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ የየራሳቸውን ፡ የመተዳ ደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዲያወጡ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ሊወክሏቸው ፡ የሚችሉ ሰዎችን ፡ መርጠው ፡ ከመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ እንዲወጣ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ሊጠየቁ ፡ ይችላሉ ።

፲፩/ ሕጉ ፡ በሌላ ፡ ረገድ ፡ በሚሻሻልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ሌሎች ፡ ነገሮችን ፡ አለ መዘንጋት ፡ ይገባል ። እነሱም ፡ ሕጉ ፡ የተጠቀመባቸውን ፡ ዕንስ ፡ ሐሳቦች ፡

312. የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፤ ሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ የልማት ፡ ፕላን ፡ (፲፱፻፶፭ - ፲፱፻፶፱) ፤ ገጽ ፡ ፫፻፳፯—፫፻፳፱ ። ከላውረንስና ፡ ማን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፩ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ።

ግልጽ ፡ የማድረግና ፡ ከመጀመሪያው ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅም ፡ አንዳንድ ፡ ድንጋ ጌዎችን ፡ መልሶ ፡ የመውሰድ ፡ ናቸው ።

፲፪/ ማድረግ ፡ ከሚቻለው ፡ ውስጥ ፤ በቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺፱ ፡ ሥር ፡ የሚገኙትን ፤ እስከዛሬ ፡ ያለመስማማት ፡ ምክንያት ፡ ሊሆኑ ፡ ይችሉ ፡ የነበሩትንና ፡ ወደፊትም ፡ የሚችሉትን ፡ "መሠራታቸው" ፡ "የሚሠሩ" ፡ የሚሉትን ፡ ቃላት ፡ ጨርሶ ፡ ማውጣትና ፡ "መያዛቸው" ፤ "የሚያዙ" ፡ በሚሉት ፡ ቃላት፡ ተክቶ ፡ የቁጥሩን ፡ ስሜት ፡ እንዳለ ፡ ማቆየት ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ ፱፻፺፱ ፡ "ሀብትነታቸው ፡ የኅብረት ፡ የሆኑ ፡ (የደሽ) ፡ እንደ ፡ የጐጣ ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች ፡ በኅብረት ፡ መያዛቸው ፡ የኅብረቱን ፡ ባሕልና ፡ ልማድ ፡ የተከተለ ፡ መስሎ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረት ፡ የሚያዙ ፡ ይሆናሉ ።" ብሎ ፡ ሊነበብ ፡ ይችላል ። የሕግ ፡ አውጭውም ፡ ፍላጐት ፡ ይኸው ፡ ነበር ።

፲፫/ በመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ ትጉህ ፡ መሪነት ፡ ሥር ፡ እንኳን፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፺ ፡ በቅርቡ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ላይውል ፡ ስለሚችል ፡ የመጀመ ሪያው ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንደገና ፡ ተጠንቶ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ቁጥሮች ፡ እንዲገቡና ፡ አሁን ፡ ያሉት ፡ ቁጥሮችም ፡ የተሟላ ፡ ትርጉም ፡ እንዲኖራቸው ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ።

፲፬/ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ ስብሰባ ፡ ለመጀመር ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ የአ ባሎቹ ፡ ቁጥር ፡ እና ፡ ስለውሳኔ ፡ አወሳሰድ ፡ ዘዴ ፡ የተደነገጉትን ፡ በመተው ፤ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አባሎች ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ቁጥሮች ፡ በፍ ትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ማስገባት ፡ ይቻላል ። እነዚህ ፡ የሚቀሩበትም ፡ ምክንያት ፡ የተባሉት ፡ ክፍሎች ፡ በዘልማድ ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጡ ፡ በጥቂቶች ፡ ሽማ ግሌዎች ፡ አማካይነት ፡ በመሆኑና ፡ ፎርማሊቲም ፡ ስለማያበዙ ፡ ነው ። የተራ ድዖ ፡ እርሻን ፡ የሚመለከቱትን ፡ የረቂቁን ፡ ደንቦችም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ጨምሮ፡ ማስገባት ፡ ይቻላል ፤ ይህም ፡ ሌላ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ መኖሩን ፡ ለማሳወቅ ፡ ከመርዳቱም ፡ በላይ ፡ ወደፊት ፡ ሊጀመር ፡ ለሚችል ፤ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ በስተሰሜን ፡ ለሚገኙ ፡ በተፈጥሮ ፡ ጸጋ ፡ ላልታደሉ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ሰፊ ፡ ጥቅም ፡ ለሚያስገኝ ፤ የተራድዖ ፡ የእርሻ ፡ እቅድ ፡ ጽኑ ፡ መሠ ረት ፡ ይሆናል ።

፲፭/ ሕጉን ፡ አሻሽሎ ፡ የኅብረት ፡ የሆነ ፡ የእርሻ ፡ መሬት ፡ ያላቸው ፡ ክፍሎች ፡ ሁሉ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ እንዲያወጡ ፡ ለማስገደድም ፡ ይቻላል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ እርምጃ ፡ በደራሲው ፡ አስተያየት ፡ ሊወሰድ ፡ የሚገባው ፡ ሌላ፡ ሊወሰድ ፡ የሚችል ፡ እርምጃ ፡ የሌለ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለበት ። አለበ ለዚያ ፡ ግን ፡ ሊከተሉት ፡ የማይቻል ፡ ከብዙዎች ፡ ክፍሎች ፡ አቅም ፡ በላይ ፡ በመሆኑ ፤ ሕግ ፡ መጣስንና ፡ አለማክበርን ፡ ማስከተሉ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ። ከላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ እርምጃዎች ፡ አሁኑን ፡ ሊወሰዱ ፡ የሚገባቸውና ፡ ሊወ ሰዱ ፡ የሚችሉም ፡ መሆናቸውን ፡ እናምንበታለን ።